# መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ ዖፅ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ስሙ ፡ ኢዮብ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ያም ፡ ሰው ፡ ፍጹምና ፡ ቅን ፥ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፥ ከክፋትም ፡ የራቀ ፡ ነበረ ።

2 ፤ ሰባትም ፡ ወንዶች ፡ ሦስትም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ተወልደውለት ፡ ነበር ።

3 ፤ ሀብቱም ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፥ ሦስት ፡ ሺሕም ፡ ግመሎች ፥ ዐምስት ፡ መቶም ፡ ጥማድ ፡ በሬ ፥ ዐምስት ፡ መቶም ፡ እንስት ፡ አህያዎች ፡ ነበረ ፥ እጅግ ፡ ብዙም ፡ ባሪያዎች ፡ ነበሩት ፤ ያም ፡ ሰው ፡ በምሥራቅ ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ታላቅ ፡ ነበረ ።

4 ፤ ወንዶች ፡ ልጆቹም ፡ ኼደው ፡ በየተራ ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ቤት ፡ ግብዣ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፤ ሦስቱ ፡ እኅቶቻቸውም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ይበሉና ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ እነርሱ ፡ ልከው ፡ ይጠሯቸው ፡ ነበር ።

5 ፤ የግብዣውም ፡ ቀኖች ፡ ባለፉ ፡ ጊዜ ፡ ኢዮብ ፦ ምናልባት ፡ ልጆቼ ፡ በድለው ፥ እግዚአብሔርንም ፡ በልባቸው ፡ ሰድበው ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ ይልክና ፡ ይቀድሳቸው ፡ ነበር ፤ ኢዮብም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ እንደ ፡ ቍጥራቸውም ፡ ኹሉ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ። እንዲሁ ፡ ኢዮብ ፡ ኹልጊዜ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።

6 ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የአምላክ ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመቆም ፡ መጡ ፥ ሰይጣንም ፡ ደግሞ ፡ በመካከላቸው ፡ መጣ ።

7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ ከወዴት ፡ መጣኽ ፧ አለው ። ሰይጣንም ፦ ምድርን ፡ ኹሉ ፡ ዞርኋት ፥ በርሷም ፡ ተመላለስኹ ፡ ብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መለሰ ።

8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ በእውኑ ፡ ባሪያዬን ፡ ኢዮብን ፡ ተመለከትኸውን ፧ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ፍጹምና ፡ ቅን ፥ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፥ ከክፋትም ፡ የራቀ ፡ ሰው ፡ የለም ፡ አለው ።

9 ፤ ሰይጣንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፦ በእውኑ ፡ ኢዮብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ በከንቱ ፡ ነውን ፧

10 ፤ ርሱንና ፡ ቤቱን ፡ በዙሪያውም ፡ ያሉትን ፡ ኹሉ ፡ አላጠርኽለትምን ፧ የእጆቹን ፡ ሥራ ፡ ባርከኽለታል ፥ ከብቱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በዝቷል ።

11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እጅኽን ፡ ዘርግተኽ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ዳብስ ፤ በእውነት ፡ በፊትኽ ፡ ይሰድብኻል ።

12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ እንሆ ፥ ለርሱ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ በእጅኽ ፡ ነው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በርሱ ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ አትዘርጋ ፡ አለው ። ሰይጣንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወጣ ።

13 ፤ አንድ ፡ ቀንም ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የኢዮብ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በታላቅ ፡ ወንድማቸው ፡ ቤት ፡ ይበሉና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጡ ፡ ነበር ።

14 ፤ መልክተኛም ፡ ወደ ፡ ኢዮብ ፡ መጥቶ ፦ በሬዎች ፡ ዕርሻ ፡ ያርሱ ፥ በአጠገባቸውም ፡ አህያዎች ፡ ይሰማሩ ፡ ነበር ፤

15 ፤ የሳባም ፡ ሰዎች ፡ አደጋ ፡ ጣሉ ፥ ወሰዷቸውም ፥ ብላቴናዎቹንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ገደሉ ፤ እኔም ፡ እነግርኽ ፡ ዘንድ ፡ ብቻዬን ፡ አመለጥኹ ፡ አለው ።

16 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ሌላ ፡ መጥቶ ፦ የእግዚአብሔር ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወደቀች ፥ በጎቹንም ፡ አቃጠለች ፥ ጠባቂዎችንም ፡ በላች ፤ እኔም ፡ እነግርኽ ፡ ዘንድ ፡ ብቻዬን ፡ አመለጥኹ ፡ አለው ።

17 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ሌላ ፡ መጥቶ ፦ ከለዳውያን ፡ በሦስት ፡ ረድፍ ፡ ተከፍለው ፡ በግመሎች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጣሉ ፥ ወሰዷቸውም ፥ ብላቴናዎቹንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ገደሉ ፤ እኔም ፡ እነግርኽ ፡ ዘንድ ፡ ብቻዬን ፡ አመለጥኹ ፡



www.ethiopianorthodox.org

አለው ።

18 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ሌላ ፡ መጥቶ ፦ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችኽ ፡ በታላቅ ፡ ወንድማቸው ፡ ቤት ፡ ይበሉና ፡
የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጡ ፡ ነበር ፤

19 ፤ እንሆም ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ መጥቶ ፡ የቤቱን ፡ አራቱን ፡ ማእዘን ፡ መታው ፥ በብላቴናዎቹም ፡ ላይ ፡
ወደቀ ፥ ሞቱም ፤ እኔም ፡ እነግርኽ ፡ ዘንድ ፡ ብቻዬን ፡ አመለጥኹ ፡ አለው ።

20 ፤ ኢዮብም ፡ ተነሣ ፡ መጐናጸፊያውንም ፡ ቀደደ ፥ ራሱንም ፡ ተላጨ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ ተደፍቶ ፡ ሰገደ ፤

21 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ዕራቍቴን ፡ ከእናቴ ፡ ማሕፀን ፡ ወጥቻለኹ ፥ ዕራቍቴንም ፡ ወደዚያ ፡
እመለሳለኹ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰጠ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ነሣ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ።

22 ፤ በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ኢዮብ ፡ አልበደለም ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ስንፍናን ፡ አልሰጠም ።

__________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የአምላክ ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመቆም ፡ መጡ ፥ ሰይጣን ፡
ደግሞ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመቆም ፡ በመካከላቸው ፡ መጣ ።

2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ ከወዴት ፡ መጣኽ ፧ አለው ። ሰይጣንም ፦ በምድር ፡ ላይ ፡ ዞርኹ ፥ በርሷም ፡
ተመላለስኹ ፡ ብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መለሰ ።

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ በእውኑ ፡ ባሪያዬን ፡ ኢዮብን ፡ ተመለከትኸውን ፧ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡
ፍጹምና ፡ ቅን ፥ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፥ ከክፋትም ፡ የራቀ ፡ ሰው ፡ የለም ፤ በከንቱም ፡ አጠፋው ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ብታንቀሳቅሰኝ ፥ እስከ ፡ አኹን ፡ ፍጹምነቱን ፡ ይዟል ።

4 ፤ ሰይጣንም ፡ መልሶ ፡ እግዚአብሔርን ፦ ቍርበት ፡ ስለ ፡ ቍርበት ፡ ነው ፤ ሰው ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ሕይወቱ ፡
ይሰጣል ።

5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አኹን ፡ እጅኽን ፡ ዘርግተኽ ፡ ዐጥንቱንና ፡ ሥጋውን ፡ ዳብስ ፤ በእውነት ፡ በፊትኽ ፡ ይሰድብኻል ፡
አለው ።

6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ ሕይወቱን ፡ ተወው ፡ እንጂ ፥ እንሆ ፥ ርሱ ፡ በእጅኽ ፡ ነው ፡ አለው ።

7 ፤ ሰይጣንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወጣ ፥ ኢዮብንም ፡ ከእግሩ ፡ ጫማ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዐናቱ ፡ ድረስ ፡ በክፉ ፡
ቍስል ፡ መታው ።

8 ፤ ሥጋውንም ፡ ይፍቅበት ፡ ዘንድ ፡ ገል ፡ ወሰደ ፥ በዐመድም ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ።

9 ፤ ሚስቱም ፦ እስከ ፡ አኹን ፡ ፍጹምነትኽን ፡ ይዘኻልን ፧ እግዚአብሔርን ፡ ስደብና ፡ሙት ፡ አለችው ።

(የሚቀጥለው ፡ ከግሪክ ፡ የተጨመረ ፡ ነው) ፡

ዳግመኛ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ ደጅ ፡ እጠናዋለኹ ፤ ዳግመኛም ፡ መከራውን ፡ እታገሠዋለኹ ፥ የቀድሞ ፡
ኑሮዬንም ፡ ተስፋ ፡ አደርገዋለኹ ፡ ትላለኽን ፧ አለችው ። እንደዚህሳ ፡ እንዳትል ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፥ እንሆ ፥ ስም ፡
አጠራርኽ ፡ ጠፋ ፤ ሴቶች ፡ ልጆቼና ፡ ወንዶች ፡ ልጆቼም ፡ ሞቱ ፡ እኔስ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ሳረግዝ ፡ ሳምጥ ፡ ስወልድ ፡
ሳይረቡኝ ፡ ሳይጠቅሙኝ ፡ በከንቱ ፡ ደከምኹ ፡ አለች ። አንተም ፡ በመግል ፡ ተውጠኽ ፡ በትል ፡ ተከበኽ ፡
ትኖራለኽ ፤ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ ስትዛብር ፡ ታድራለኽ ። እኔ ፡ ግን ፡ እየዞርኹ ፡ እቀላውጣለኹ ። ከአንዱ ፡ አገር ፡ ወደ ፡
አንዱ ፡ አገር ፡ ከአንዱ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቤት ፡ እኼዳለኹ ፤ ከድካሜ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ካለ ፡ ከችግሬም ፡ ዐርፍ ፡
ዘንድ ፡ ከጧት ፡ ዠምሮ ፡ ፀሓይ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ እጠብቃለኹ ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማይገባ ፡ ቃል ፡
ተናግረኸው ፡ ሙት ፡ አለች ።

10 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ አንቺ ፡ ከሰነፎች ፡ ሴቶች ፡ እንደ ፡ አንዲቱ ፡ ተናገርሽ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መልካሙን ፡
ተቀበልን ፥ ክፉ ፡ ነገርንስ ፡ አንቀበልምን ፧ አላት ። በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ኢዮብ ፡ በከንፈሩ ፡ አልበደለም ።



www.ethiopianorthodox.org

11 ፤ ሦስቱም ፡ የኢዮብ ፡ ወዳጆች ፡ ይህን ፡ የደረሰበትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ሰምተው ፡ ከየአገራቸው ፡
መጡ ፤ እነርሱም ፡ ቴማናዊው ፡ ኤልፋዝ ፥ ሹሐዊው ፡ በልዳዶስ ፥ ነዕማታዊው ፡ ሶፋር ፡ ነበሩ ። እነርሱም ፡
ሊያዝኑለትና ፡ ሊያጽናኑት ፡ በአንድነት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ለመምጣት ፡ ተስማሙ ።

12 ፤ ከሩቅም ፡ ኾነው ፡ ዐይናቸውን ፡ ባነሡ ፡ ጊዜ ፡ አላወቁትም ፤ ድምፃቸውንም ፡ አሰምተው ፡
አለቀሱ ፤ እያንዳንዳቸውም ፡ መጐናጸፊያቸውን ፡ ቀደዱ ፥ ወደ ፡ ላይም ፡ ወደ ፡ ራሳቸው ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነሰነሱ ።

13 ፤ ሰባት ፡ ቀንና ፡ ሰባት ፡ ሌሊትም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ፤ ሕመሙም ፡ እጅግ ፡ እንደ ፡ በዛ ፡
አይተዋልና ፥ ከነርሱ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ የሚናገረው ፡ አልነበረም ።

## ____________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ ከዚያም ፡ በ፡ኋላ ፡ ኢዮብ ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ የተወለደበትን ፡ ቀን ፡ ረገመ ።

2 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦

3 ፤ ያ ፡ የተወለድ፡ኹበት ፡ ቀን ፡ ይጥፋ ፥

ያም ፦ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተፀነሰ ፡ የተባለበት ፡ ሌሊት ።

4 ፤ ያ ፡ ቀን ፡ ጨለማ ፡ ይኹን ፤

እግዚአብሔር ፡ ከላይ ፡ አይመልከተው ፥

ብርሃንም ፡ አይብራበት ።

5 ፤ ጨለማና ፡ የሞት ፡ ጥላ ፡ የራሳቸው ፡ ገንዘብ ፡ ያድርጉት ፤

ዳመናም ፡ ይረፍበት ፤

የቀን ፡ ጨለማ ፡ ኹሉ ፡ ያስፈራው ።

6 ፤ ያን ፡ ሌሊት ፡ ጨለማ ፡ ይያዘው ፤

በዓመቱ ፡ ቀኖች ፡ መካከል ፡ ደስ ፡ አይበለው ፤

በወሮች ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ አይቈጠር ።

7 ፤ እንሆ ፥ ያ ፡ ሌሊት ፡ መካን ፡ ይኹን ፤

እልልታ ፡ አይግባበት ።

8 ፤ ሌዋታንን ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ የተዘጋጁ ፡

ቀኑን ፡ የሚረግሙ ፡ ይርገሙት ።

9 ፤ አጥቢያ ፡ ኮከቦች ፡ ይጨልሙ ፤

ብርሃንን ፡ ቢጠባበቅ ፡ አያግኘው ፥

የንጋትንም ፡ ቅንድብ ፡ አይይ ፤

10 ፤ የእናቴን ፡ ማሕፀን ፡ ደጅ ፡ አልዘጋምና ፥

መከራንም ፡ ከዐይኔ ፡ አልሰወረምና ።

11 ፤ በማሕፀን ፡ ሳለኹ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልሞትኹም ፧

ከሆድስ ፡ በወጣኹ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኜ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልጠፋኹም ፧

12 ፤ ጕልበቶች ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተቀበሉኝ ፧



www.ethiopianorthodox.org

ጡትስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ጠባኹ ፨

13 ፤ አኹን ፡ ተኝቼ ፡ ዝም ፡ ባልኹ ፡ ነበር ፤

አንቀላፍቼ ፡ ባረፍኹ ፡ ነበር ፤

14 ፤ የፈረሰውን ፡ ለራሳቸው ፡ ከሚሠሩት ፡

ከምድር ፡ ነገሥታትና ፡ መካሮች ፡ ጋራ ፥

15 ፤ ወይም ፡ ቤታቸውን ፡ ብር ፡ ከሞሉ ፡

ወርቅም ፡ ካላቸው ፡ መኳንንት ፡ ጋራ ፥

16 ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ተቀበረ ፡ ጭንጋፍ ፥

ብርሃንም ፡ እንዳላዩ ፡ ሕፃናት ፡ በኾንኹ ፡ ነበር ።

17 ፤ ክፉዎች ፡ በዚያ ፡ መናደዳቸውን ፡ ይተዋሉ ፤

በዚያም ፡ ደካማዎች ፡ ያርፋሉ ።

18 ፤ በዚያ ፡ ግዞተኛዎች ፡ በአንድነት ፡ ተዘልለው ፡ ተቀምጠዋል ፤

የአስጨናቂውን ፡ ድምፅ ፡ አይሰሙም ።

19 ፤ ታናሽና ፡ ታላቅ ፡ በዚያ ፡ አሉ ፤

ባሪያም ፡ ከጌታው ፡ ነጻ ፡ ወጥቷል ።

20 ፤ በመከራ ፡ ላሉት ፡ ብርሃን ፥

ነፍሳቸው ፡ መራራ ፡ ለኾነችባቸው ፥

21 ፤ የተሰወረ ፡ ሀብትን ፡ ከሚቈፍሩ ፡ ይልቅ ፡

ሞትን ፡ ለሚጠብቁ ፡ ለማያገኙትም ፥

22 ፤ መቃብርን ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡

በእልልታ ፡ ደስ ፡ ለሚላቸው ፥ ሐሤትንም ፡ ለሚያደርጉ ፡

ሕይወት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተሰጠ ፨

23 ፤ መንገዱ ፡ ለተሰወረበት ፡ ሰው ፥

እግዚአብሔርም ፡ በዐጥር ፡ ላጠረው ፡

ብርሃን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተሰጠ ፨

24 ፤ ከእንጀራዬ ፡ በፊት ፡ ልቅሶዬ ፡ መጥቷልና ፥

ጩኸቴም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ፈስሷል ።

25 ፤ የፈራኹት ፡ ነገር ፡ መጥቶብኛልና ፥

የደነገጥኹበትም ፡ ደርሶብኛል ።

26 ፤ ተዘልዬ ፡ አልተቀመጥኹም ፥ አልተማመንኹም ፥ አላረፍኹም ፤

ነገር ፡ ግን ፡ መከራ ፡ መጣብኝ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ምዕራፍ ፡ 4 ።



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ ቴማናዊውም ፡ ኤልፋዝ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ ቢሞክር ፡ ትቀየማለኽን ፧

ቃልንስ ፡ ከመናገር ፡ ሊቀር ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፧

3 ፤ እንሆ ፥ አንተ ፡ ብዙዎችን ፡ ታስተምር ፡ ነበር ፥

የደከሙትንም ፡ እጆች ፡ ታበረታ ፡ ነበር ፥

4 ፤ ቃልኽ ፡ የሚሰናከለውን ፡ ያስነሣ ፡ ነበር ፥

አንተም ፡ የሚብረከረከውን ፡ ጕልበት ፡ ታጸና ፡ ነበር ።

5 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ መጥቷል ፥ አንተም ፡ ደከምኽ ፤

ደርሶብኻል ፥ አንተም ፡ ተቸገርኽ ።

6 ፤ አምላክኽን ፡ መፍራትኽ ፡ መጽናናትኽ ፥

የቅንነትኽም ፡ መንገድ ፡ ተስፋኽ ፡ አይደለምን ፧

7 ፤ እባክኽ ፡ ዐስብ ፥ ንጹሕ ፡ ኾኖ ፡ የጠፋ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ከልበ ፡ ቅንስ ፡ የተደመሰሰ ፡ ማን ፡ ነው ፧

8 ፤ እኔ ፡ እንዳየኹ ፥ ኀጢአትን ፡ የሚያርሱ ፥

መከራንም ፡ የሚዘሩ ፡ ይህንኑ ፡ ያጭዳሉ ።

9 ፤ በእግዚአብሔር ፡ እስትንፋስ ፡ ይጠፋሉ ፥

በቍጣውም ፡ መንፈስ ፡ ያልቃሉ ።

10 ፤ የአንበሳ ፡ ጩኸት ፥ የጫኪ ፡ አንበሳ ፡ ድምፅ ፥

የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ ጥርስ ፡ ተሰባበረ ።

11 ፤ አሮጌ ፡ አንበሳ ፡ አደን ፡ በማጣት ፡ ይሞታል ፥

የአንበሳዪቱም ፡ ግልገሎች ፡ ይበተናሉ ።

12 ፤ ለኔም ፡ በምስጢር ፡ ቃል ፡ መጣልኝ ፥

ጆሮዬም ፡ ሹክሹክታውን ፡ ሰማች ።

13 ፤ በሌሊት ፡ ሕልም ፡ ዐሳብ ፡ ሲነሣ ፥

የከበደም ፡ እንቅልፍ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፥

14 ፤ ዐጥንቴን ፡ ኹሉ ፡ ያናወጡ ፡

ድንጋጤና ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ወደቁብኝ ።

15 ፤ መንፈስም ፡ በፊቴ ፡ ዐለፈ ፤

የሥጋዬ ፡ ጠጕር ፡ ቆመ ።

16 ፤ ርሱም ፡ ቆመ ፥ መልኩን ፡ ግን ፡ ለመለየት ፡ አልቻልኹም ፥

ምሳሌም ፡ በዐይኔ ፡ ፊት ፡ ነበረ ፤

የዝምታ ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

17 ፤ በእውኑ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጻድቅ ፡ ሊኾን ፥



www.ethiopianorthodox.org

ወይስ ፡ ሰው ፡ በፈጣሪው ፡ ፊት ፡ ሊነጻ ፡ ይችላልን ፨

18 ፤ እንሆ ፥ በባሪያዎቹ ፡ አይታመንም ፤

መላእክቱንም ፡ ስንፍና ፡ ይከሳቸዋል ፤

19 ፤ ይልቁንስ ፡ በጭቃ ፡ ቤት ፡ የሚኖሩ ፥

መሠረታቸው ፡ በትቢያ ፡ ውስጥ ፡ የኾነ ፥

ከብል ፡ በፊት ፡ የሚጨፈለቁ ፡ እንዴት ፡ ይኾኑ ፨

20 ፤ በጧትና ፡ በማታ ፡ መካከል ፡ ይሰባበራሉ ፤

ማንም ፡ ሳያስብ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጠፋሉ ።

21 ፤ ገመዳቸው ፡ የተነቀለ ፡ አይደለምን ፨

አለጥበብም ፡ ይሞታሉ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ምዕራፍ ፡ 5 ።

1 ፤ አኹንም ፡ ጥራ ፤ የሚመልስልኽ ፡ አለን ፨

ከቅዱሳንስ ፡ ወደ ፡ ማናቸው ፡ ትዞራለኽ ፨

2 ፤ ሰነፉን ፡ ሰው ፡ ቍጣ ፡ ይገድለዋል ፥

ሰነፉንም ፡ ቅንአት ፡ ያጠፋዋል ።

3 ፤ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ሥር ፡ ሰዶ ፡ አየኹት ፥

ድንገትም ፡ መኖሪያውን ፡ ረገምኹ ።

4 ፤ ልጆቹም ፡ ከደኅንነት ፡ ርቀዋል ፥

በበርም ፡ ውስጥ ፡ ተረግጠዋል ፥

የሚታደጋቸውም ፡ የለም ።

5 ፤ የሰበሰበውንም ፡ ራብተኛ ፡ ይበላዋል ፥

ከሾኽም ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ ያወጣዋል ፤

የተጠማ ፡ ሀብታቸውን ፡ ዋጠ ።

6 ፤ ችግር ፡ ከትቢያ ፡ አይመጣም ፥

መከራም ፡ ከመሬት ፡ አይበቅልም ፤

7 ፤ የአሞራ ፡ ግልገሎች ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እየበረሩ ፡ ከፍ ፡ እንዲሉ ፥

ሰው ፡ እንዲሁ ፡ ለመከራ ፡ ተወልዷል ።

8 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እለምን ፡ ነበር ፥

ነገሬንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቀርብ ፡ ነበር ።

9 ፤ የማይመረመረውን ፡ ታላቅ ፡ ነገርና ፡

የማይቈጠረውን ፡ ተኣምራት ፡ ያደርጋል ።

10 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ዝናብን ፡ ይሰጣል ፥



www.ethiopianorthodox.org

በዕርሻም ፡ ላይ ፡ ውሃ ፡ ይልካል ።

11 ፤ የተዋረዱትን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ያወጣል ፥

ሐዘንተኛዎችንም ፡ ለደኅንነት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋቸዋል ።

12 ፤ እጃቸውም ፡ ምክራቸውን ፡ እንዳይፈጽም ፡

የተንኰለኛዎችን ፡ ዐሳብ ፡ ከንቱ ፡ ያደርገዋል ።

13 ፤ ጠቢባንን ፡ በተንኰላቸው ፡ ይይዛቸዋል ፤

የጠማማዎችንም ፡ ምክር ፡ ይዘረዝራል ።

14 ፤ በቀን ፡ ጨለማን ፡ ያገኛሉ ፥

በቀትርም ፡ ጊዜ ፡ በሌሊት ፡ እንዳሉ ፡ ይርመሰመሳሉ ።

15 ፤ ድኻውንም ፡ ከአፋቸው ፡ ሰይፍ ፡

ከኀያሉም ፡ እጅ ፡ ያድነዋል ።

16 ፤ ለምስኪኑም ፡ ተስፋ ፡ አለው ፤

ክፋት ፡ ግን ፡ አፏን ፡ ትዘጋለች ።

17 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ የሚገሥጸው ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤

ስለዚህ ፡ ኹሉን ፡ የሚችለውን ፡ የአምላክን ፡ ተግሣጽ ፡ አትናቅ ።

18 ፤ ርሱ ፡ ይሰብራል ፥ ይጠግንማል ፤

ያቈስላል ፥ እጆቹም ፡ ይፈውሳሉ ።

19 ፤ በስድስት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ያድንኻል ፥

በሰባትም ፡ ውስጥ ፡ ክፋት ፡ አትነካኽም ።

20 ፤ በራብ ፡ ጊዜ ፡ ከሞት ፥

በሰልፍም ፡ ከሰይፍ ፡ እጅ ፡ ያድንኻል ።

21 ፤ ከምላስ ፡ ጅራፍ ፡ ትሰወራለኽ ፤

ጥፋትም ፡ ሲመጣ ፡ አትፈራም ።

22 ፤ በጥፋትና ፡ በራብ ፡ ላይ ፡ ትሥቃለኽ ፤

ከምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊትም ፡ አትፈራም ፤

23 ፤ ቃል ፡ ኪዳንኽ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ድንጋይ ፡ ጋራ ፡ ይኾናልና ፤

የምድረ ፡ በዳም ፡ አራዊት ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይስማማሉና ።

24 ፤ ድንኳንኽም ፡ በሰላም ፡ እንዲኾን ፡ ታውቃለኽ ፤

በረትኽን ፡ ትጐበኛለኽ ፡ አንዳችም ፡ አይጐድልብኽም ።

25 ፤ ዘርኽም ፡ ታላቅ ፡ እንዲኾን ፥

ትውልድኽም ፡ እንደምድር ፡ ሣር ፡ እንዲኾን ፡ ታውቃለኽ ።

26 ፤ በወራቱ ፡ የእኽሉ ፡ ነዶ ፡ ወደ ፡ ዐውድማ ፡ እንዲገባ ፥

በረዥም ፡ ዕድሜ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ትገባለኽ ።



www.ethiopianorthodox.org

27 ፤ እንሆ ፥ ይህችን ፡ መረመርን ፥ የሰማነውም ፡ ይህ ፡ ነው ፤

አንተ ፡ ግን ፡ አንዳች ፡ ሠርተኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለራስኽ ፡ ዕወቀው ።

______________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 6 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ።

2 ፤ ትካዜዬ ፡ ምነው ፡ በተመዘነ ፡ ኖሮ!

መከራዬም ፡ ኹሉ ፡ ምነው ፡ በሚዛን ፡ ላይ ፡ በተደረገ ፡ ኖሮ!

3 ፤ ከባሕር ፡ አሸዋ ፡ ይልቅ ፡ ይከብድ ፡ ነበርና ፤

ስለዚህ ፡ ቃሌ ፡ ደፋር ፡ ኾኗል ።

4 ፤ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ የአምላክ ፡ ፍላጻ ፡ በሥጋዬ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፥

መርዙንም ፡ ነፍሴ ፡ ትጠጣለች ፤

የእግዚአብሔር ፡ ድንጋጤ ፡ በላዬ ፡ ተሰልፏል ።

5 ፤ በእውኑ ፡ የሜዳ ፡ አህያ ፡ ሣር ፡ ሳለው ፡ ይጮኻልን ፧

ወይስ ፡ በሬ ፡ ገለባ ፡ ሳለው ፡ ይጮኻልን ፧

6 ፤ የማይጣፍጥስ ፡ ነገር ፡ ያለጨው ፡ ይበላልን ፧

ወይስ ፡ የዕንቍላል ፡ ውሃ ፡ ይጥማልን ፧

7 ፤ ሰውነቴ ፡ ትነካው ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለችው ፤

እንደሚያስጸይፍ ፡ መብል ፡ ኾነብኝ ።

8 ፤ ልመናዬ ፡ ምነው ፡ በደረሰልኝ!

እግዚአብሔርም ፡ ምኞቴን ፡ ምነው ፡ በሰጠኝ!

9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያደቀኝ ፡ ዘንድ ፡

እጁንም ፡ ለቆ ፡ ያጠፋኝ ፡ ዘንድ ፡ ወዶ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ!

10 ፤ መጽናናት ፡ በኾነልኝ ፡ ነበር ፤

በማይራራ ፡ ሕመም ፡ ሐሤት ፡ ባደረግኹ ፡ ነበር ፥

የቅዱሱን ፡ ቃል ፡ አልካድኹምና ።

11 ፤ እጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ጕልበቴ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

እታገሥም ፡ ዘንድ ፡ ፍጻሜዬ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

12 ፤ ጕልበቴ ፡ የድንጋይ ፡ ጕልበት ፡ ነውን ፧

ሥጋዬስ ፡ እንደ ፡ ናስ ፡ ነውን ፧

13 ፤ በእውኑ ፡ ረድኤት ፡ በእኔ ፡ እንደሌለ ፡

ጥበብም ፡ ኹሉ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተባረረ ፡ አይደለምን ፧

14 ፤ ኹሉን ፡ የሚችለውን ፡ የአምላክን ፡ መፍራት ፡

ለሚተው ፥ ለመዛል ፡ ለቀረበው ፡ ስንኳ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ወዳጁ ፡ ቸርነትን ፡ ሊያሳይ ፡ ይጎባል ።

15 ፤ ወንድሞቼ ፡ እንደ ፡ ፈፋ ፥

እንደሚያልፍ ፡ ፈፋ ፡ ሐሰተኛዎች ፡ ኾኑብኝ ።

16 ፤ ከበረዶ ፡ የተነሣ ፡ ደፈረሱ ፥

ዐመዳይም ፡ ተሰወረባቸው ፤

17 ፤ ፀሓይ ፡ በተኰሰች ፡ ጊዜ ፡ ይደርቃሉ ፤

በሙቀትም ፡ ጊዜ ፡ ከስፍራቸው ፡ ይጠፋሉ ።

18 ፤ በየዳርቻቸውም ፡ የሚኼዱ ፡ ነጋዴዎች ፡ ፈቀቅ ፡ ይላሉ ፤

ወደ ፡ በረሓ ፡ ወጥተው ፡ ይጠፋሉ ።

19 ፤ የቴማን ፡ ነጋዴዎች ፡ ተመለከቱ ፥

የሳባ ፡ መንገደኛዎችም ፡ ተጠባበቋቸው ።

20 ፤ ተስፋ ፡ አድርገዋቸው ፡ ነበርና ፥ ዐፈሩ ፤

ወደዚያ ፡ ደረሱ ፥ ዕፍረትም ፡ ያዛቸው ።

21 ፤ አኹንም ፡ እናንተ ፡ እንደዚሁ ፡ ኾናችኋል ፤

መከራዬን ፡ አይታችኹ ፡ ፈራችኹ ።

22 ፤ በእውኑ ፦ አንዳች ፡ ነገር ፡ አምጡልኝ ፤

ወይስ ፦ ከብልጥግናችኹ ፡ ስጦታ ፡ አቅርቡልኝ ፤

23 ፤ ወይስ ፦ ከጠላቴ ፡ እጅ ፡ አስጥሉኝ ፤

ወይስ ፦ ካስጨናቂው ፡ እጅ ፡ አድኑኝ ፡ አልኳችኹን ፧

24 ፤ አስተምሩኝ ፥ እኔም ፡ ዝም ፡ እላለኹ ፤

የተሳሳትኹትንም ፡ ንገሩኝ ።

25 ፤ የቅንነት ፡ ቃል ፡ እንዴት ፡ ኀይለኛ ፡ ነው!

የእናንተ ፡ ሙግት ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይገሥጻል ፧

26 ፤ ተስፋ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ንግግር ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ነውና ፥

ቃሌን ፡ ትገሥጹ ፡ ዘንድ ፡ ታስባላችኹን ፧

27 ፤ በድኻ ፡ አደጉ ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡ ትጣጣላላችኹ ፤

ለወዳጆቻችኹም ፡ ጉድጓድ ፡ ትቈፍራላችኹ ።

28 ፤ አኹንም ፥ እባካችኹ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመልከቱ ፤

በፊታችኹም ፡ ሐሰት ፡ አልናገርም ።

29 ፤ እባካችኹ ፥ ተመለሱ ፤ በደል ፡ አይኹን ፤

ጽድቄ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ነውና ፥ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተመለሱ ።

30 ፤ በእውኑ ፡ በአንደበቴ ፡ በደል ፡ ይገኛልን ፧

አፌስ ፡ ተንኰልን ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ አይችልምን ፧



www.ethiopianorthodox.org

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ምዕራፍ ፡ 7 ።

1 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ ብርቱ ፡ ሰልፍ ፡ አይደለምን ፧

ወራቱም ፡ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ ወራት ፡ አይደለምን ፧

2 ፤ አገልጋይ ፡ ጥላ ፡ እንደሚመኝ ፥

ምንደኛም ፡ ደመ ፡ ወዙን ፡ እንደሚጠብቅ ፥

3 ፤ እንዲሁ ፡ ዕጣዬ ፡ የከንቱ ፡ ወራት ፡ ኾነብኝ ፥

የድካምም ፡ ሌሊት ፡ ተወሰነችልኝ ።

4 ፤ በተኛኹ ፡ ጊዜ ፦ መቼ ፡ እነሣለኹ ፧ እላለኹ ።

ሌሊቱ ፡ ግን ፡ ይረዝማል ፥

እስኪነጋ ፡ ድረስም ፡ እገለባበጣለኹ ።

5 ፤ ሥጋዬ ፡ ትልና ፡ ጓል ፡ ለብሷል ፤

ቍርበቴ ፡ ያፈከፍካል ፡ እንደ ፡ ገናም ፡ ይመግላል ።

6 ፤ ዘመኔ ፡ ከሸማኔ ፡ መወርወሪያ ፡ ይልቅ ፡ ይቸኵላል ፥

ያለ ፡ ተስፋም ፡ ያልቃል ።

7 ፤ ሕይወቴ ፡ እስትንፋስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐስብ ፤

ዐይኔ ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያይም ።

8 ፤ የሚያየኝ ፡ ሰው ፡ ዐይን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያየኝም ፤

ዐይንኽ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ እኔም ፡ አልገኝም ።

9 ፤ ደመና ፡ ተበትኖ ፡ እንደሚጠፋ ፥

እንዲሁ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ የሚወርድ ፡ ዳግመኛ ፡ አይወጣም ።

10 ፤ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ዳግመኛ ፡ አይመለስም ፥

ስፍራውም ፡ ዳግመኛ ፡ አያውቀውም ።

11 ፤ ስለዚህም ፡ አፌን ፡ አልከለክልም ፤

በመንፈሴ ፡ ጭንቀትን ፡ እናገራለኹ ፤

በነፍሴ ፡ ምሬት ፡ በሐዘን ፡ አንጐራጕራለኹ ።

12 ፤ ጠባቂ ፡ ታስነሣብኝ ፡ ዘንድ ፥

እኔ ፡ ባሕር ፡ ወይስ ፡ ዐንበሪ ፡ ነኝን ፧

13 ፤ እኔም ፦ ዐልጋዬ ፡ ያጽናናኛል ፥

መኝታዬም ፡ የሐዘን ፡ እንጕርጕሮዬን ፡ ያቀልልኛል ፡ ባልኹ ፡ ጊዜ ፥

14 ፤ አንተ ፡ በሕልም ፡ ታስፈራራኛለኽ ፥

በራእይም ፡ ታስደነግጠኛለኽ ፤

15 ፤ ነፍሴም ፡ ከዐጥንቴ ፡ ይልቅ ፡



www.ethiopianorthodox.org

መታነቅንና ፡ ሞትን ፡ መረጠች ።

16 ፤ ሕይወቴን ፡ ናቅኋት ፤ ለዘለዓለም ፡ ልኖር ፡ አልወድም ።

የሕይወቴ ፡ ዘመን ፡ እስትንፋስ ፡ ነውና ፥ ተወኝ ።

17 ፤ ሰው ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ታከብረው ፡ ዘንድ ፥

ልብኽንስ ፡ ትጥልበት ፡ ዘንድ ፥

18 ፤ ማለዳ ፡ ማለዳስ ፡ ትጐበኘው ፡ ዘንድ ፥

ኹልጊዜስ ፡ ትፈታተነው ፡ ዘንድ ፧

19 ፤ የማትተወኝ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

ምራቄንስ ፡ እስክውጥ ፡ ድረስ ፡ የማትለቅኝ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

20 ፤ ሰውን ፡ የምትጠብቅ ፡ ሆይ ፥ በድዬስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምን ፡ ላድርግልኽ ፧

ስለ ፡ ምን ፡ እኔን ፡ ለአንተ ፡ ዐላማ ፡ አደረግኸኝ ፧

ስለ ፡ ምን ፡ እኔ ፡ ሸክም ፡ ኾንኩብኽ ፧

21 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ መተላለፌን ፡ ይቅር ፡ አትልም ፧

ኀጢአቴንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አታስወግድልኝም ፧

አኹን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ እተኛለኹ ፤

ማለዳ ፡ ትፈልገኛለኽ ፥ አታገኘኝም ።

__________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 8 ።

1 ፤ ሹሐዊውም ፡ በልዳዶስ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ ይህን ፡ ትናገራለኽ ፧

የአፍኽስ ፡ ቃል ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይኾናል ፧

3 ፤ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍርድን ፡ ያጣምማልን ፧

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ጽድቅን ፡ ያጣምማልን ፧

4 ፤ ልጆችኽ ፡ በድለውት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ርሱ ፡ በበደላቸው ፡ እጅ ፡ ጥሏቸዋል ።

5 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ብትገሠግሥ ፥

ኹሉንም ፡ የሚችለውን ፡ አምላክ ፡ ብትለምን ፥

6 ፤ ንጹሕና ፡ ቅን ፡ ብትኾን ፥

በእውነት ፡ አኹን ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ይነቃል ፥

የጽድቅኽንም ፡ መኖሪያ ፡ ያከናውንልኻል ።

7 ፤ ኻፐማሬኽ ፡ ታናሽ ፡ ቢኾንም ፡ እንኳ ፡

ፍጻሜኽ ፡ እጅግ ፡ ይበዛል ።

8 ፤ 9 ፤ ዘመናችን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ነውና ፥



www.ethiopianorthodox.org

እኛ ፡ የትናንት ፡ ብቻ ፡ ነን ፤ ምንም ፡ አናውቅም ፤

ስለዚህ ፡ የቀደመውን ፡ ትውልድ ፡ ጠይቅ ፥

አባቶቻቸውም ፡ ለመረመሩት ፡ ነገር ፡ ትጋ ፤

10 ፤ እነርሱ ፡ የሚያስተምሩኽና ፡ የሚነግሩኽ ፥

ቃልንም ፡ ከልባቸው ፡ የሚያወጡ ፡ አይደሉምን ፧

11 ፤ በእውኑ ፡ ደንገል ፡ ረግረግ ፡ በሌለበት ፡ መሬት ፡ ይበቅላልን ፧

ወይስ ፡ ቄጠማ ፡ ውሃ ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ ይለመልማልን ፧

12 ፤ ገና ፡ ሲለመልም ፡ ሳይቈረጥም ፥

ከአትክልት ፡ ዅሉ ፡ በፊት ፡ ይደርቃል ።

13 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚረሱ ፡ ዅሉ ፡ ፍጻሜያቸው ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤

የዝንጉም ፡ ሰው ፡ ተስፋ ፡ ይጠፋል ።

14 ፤ ተስፋው ፡ ይቈረጣል ፥

እምነቱም ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ቤት ፡ ይኾናል ።

15 ፤ ቤቱን ፡ ይደግፈዋል ፥ አይቆምለትም ፤

ይይዘውማል ፥ አይጸናለትም ።

16 ፤ ፀሓይም ፡ ሳይተኰስ ፡ ይለመልማል ፥

ጫፉም ፡ በአታክልቱ ፡ ቦታ ፡ ይወጣል ።

17 ፤ በድንጋይ ፡ ክምር ፡ ላይ ፡ ሥሩ ፡ ይጠመጠማል ፤

የድንጋዮቹን ፡ ቦታ ፡ ይመለከታል ።

18 ፤ ከቦታው ፡ ቢጠፋ ፡

አላየኹኽም ፡ ብሎ ፡ ይክደዋል ።

19 ፤ እንሆ ፥ የመንገዱ ፡ ደስታ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤

ሌላዎችም ፡ ከመሬት ፡ ይበቅላሉ ።

20 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ፍጹሙን ፡ ሰው ፡ አይጥለውም ፥

የኀጢአተኛዎችንም ፡ እጅ ፡ አያበረታም ።

21 ፤ አፍኽን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሣቅ ፡ ይሞላል ፥

ከንፈሮችኽንም ፡ እልልታ ፡ ይሞላል ።

22 ፤ የሚጠሉኽ ፡ ዕፍረት ፡ ይለብሳሉ ፤

የኀጢአተኛዎችም ፡ ድንኳን ፡ አይገኝም ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ምዕራፍ ፡ 9 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ በእውነት ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቅኹ ፤



www.ethiopianorthodox.org

ሰውስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጻድቅ ፡ መኾን ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፧

3 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይከራከር ፡ ዘንድ ፡ ቢወድ ፥

ከሺሕ ፡ ነገር ፡ አንዱን ፡ መመለስ ፡ አይችልም ።

4 ፤ ልቡ ፡ ጠቢብ ፥ ኀይሉም ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤

ደፍሮትስ ፡ በደኅና ፡ የኼደ ፡ ማን ፡ ነው ፧

5 ፤ ተራራዎችን ፡ ይነቅላል ፤ አያውቁትም ፤

በቍጣውም ፡ ይገለብጣቸዋል ።

6 ፤ ምድርን ፡ ከስፍራው ፡ ያናውጣታል ፥

ምሰሶዎቿም ፡ ይንቀጠቀጣሉ ።

7 ፤ ፀሓይን ፡ ያዝታል ፥ አትወጣምም ፤

ከዋክብትንም ፡ ያትማል ።

8 ፤ ሰማያትን ፡ ብቻውን ፡ ይዘረጋል ፥

በባሕሩም ፡ ማዕበል ፡ ላይ ፡ ይረግጣል ።

9 ፤ ድብ ፡ የሚባለውን ፡ ኮከብና ፡ ኦሪዮን[256] ፡ የሚባለውን ፡ ኮከብ ፥ ሰባቱንም ፡ ከዋክብት ፥

በደቡብም ፡ በኩል ፡ ያሉትን ፡ የከዋክብት ፡ ማደሪያዎች ፡ ሠርቷል ።

10 ፤ የማይመረመረውን ፡ ታላላቅ ፡ ነገር ፥

የማይቈጠረውንም ፡ ተኣምራት ፡ ያደርጋል ።

11 ፤ እንሆ ፥ ቢመጣብኝ ፡ አላየውም ፤

ቢያልፍብኝም ፡ አላውቀውም ።

12 ፤ እንሆ ፥ ፈጥኖ ፡ ቢነጥቅ ፡ የሚከለክለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ርሱንስ ፦ ምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ የሚለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቍጣውን ፡ አይመልስም ፤

ከርሱ ፡ በታች ፡ ረዓብን ፡ የሚረዱ ፡ ይዋረዳሉ ።

14 ፤ ይልቁንስ ፡ እመልስለት ፡ ዘንድ ፥

ቃሌንስ ፡ በፊቱ ፡ እመርጥ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ፧

15 ፤ ጻድቅ ፡ ብኾን ፡ ኖሮ ፡ አልመልስለትም ፡ ነበር ፤

ወደ ፡ ፈራጄም ፡ እለምን ፡ ነበር ።

16 ፤ ብጠራው ፡ ርሱም ፡ ቢመልስልኝ ፡ ኖሮ ፥

ቃሌን ፡ እንደ ፡ ሰማ ፡ አላምንም ፡ ነበር ።

17 ፤ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይሰብረኛል ፥

ቍስሌንም ፡ ያለምክንያት ፡ ያበዛል ።

18 ፤ እተነፍስ ፡ ዘንድ ፡ አይተወኝም ፥

256 ጽር. ፥ ኦሬዎን ፡ (አርዮብ ፥ ጉቡኣን ፡ ከዋክብት • ታላቅ ፡ ኮከብ ፥ ካራቱ ፡ ዐበይት ፡ ከዋክብት ፡ አንዱ ፥ ከ.ወ.ክ. ፥ ገ.241) ።



www.ethiopianorthodox.org

ነገር ፡ ግን ፡ መራራን ፡ ነገር ፡ አጥግቦኛል ።

19 ፤ የኀይል ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፡ ርሱ ፡ ኀያል ፡ ነው ፤

የፍርድ ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፦ ጊዜን ፡ ወሳኙ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ይላል ።

20 ፤ ጻድቅ ፡ ብኾን ፡ አፌ ፡ ይወቅሰኛል ፤

ፍጹምም ፡ ብኾን ፡ ጠማማ ፡ ያደርገኛል ።

21 ፤ ፍጹም ፡ ነኝ ፡ ራሴንም ፡ አልመለከትም ፤

ሕይወቴንም ፡ እንቃታለኹ ።

22 ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፦

ፍጹማንንና ፡ ክፋዎችን ፡ ያጠፋል ፡ እላለኹ ።

23 ፤ መቅሠፍቱ ፡ ፈጥኖ ፡ ቢገድል ፥

በንጹሓን ፡ ፈተና ፡ ይሳለቃል ።

24 ፤ ምድር ፡ በኃጥኣን ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፤

የፈራጆቿን ፡ ፊት ፡ ሸፍኗል ፤

ርሱ ፡ ካልኾነ ፡ ማን ፡ ነው ፧

25 ፤ ዘመኔ ፡ ከሚሮጥ ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ ይፈጥናል ፤

ይሸሻል ፥ መልካምንም ፡ አያይም ።

26 ፤ የደንገል ፡ ታንኳ ፡ እንደሚፈጥን ፥

ንስርም ፡ ወደ ፡ ንጥቂያው ፡ እንደሚበር ፡ ያልፋል ።

27 ፤ እኔ ፦ የሐዘን ፡ እንጕርጕሮዬን ፡ እረሳለኹ ፤

ፊቴን ፡ መልሼ ፡ እጽናናለኹ ፡ ብል ፥

28 ፤ ንጹሕ ፡ እንደማታደርገኝ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹና ፡

ከመከራዬ ፡ ኹሉ ፡ እፈራለኹ ።

29 ፤ በደለኛ ፡ እንደሚኾን ፡ ሰው ፡ እኾናለኹ ፤

ስለ ፡ ምንስ ፡ በከንቱ ፡ እደክማለኹ ፧

30 ፤ በዐመዳይ ፡ ውስጥ ፡ ብታጠብ ፥

እጆቼንም ፡ እጅግ ፡ ባነጻ ፥

31 ፤ በዐዘቅት ፡ ውስጥ ፡ ታሰጥመኛለኽ ፥

ልብሴም ፡ ይጸየፈኛል ።

32 ፤ እንድመልስለት ፡ ዐብረን ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ እንገባ ፡ ዘንድ ፥

ርሱ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ሰው ፡ አይደለም ።

33 ፤ እጁን ፡ በኹለታችን ፡ ላይ ፡ የሚያኖር ፡ ዳኛ ፡

በመካከላችን ፡ ምነው ፡ በተገኘ!

34 ፤ በትሩን ፡ ከእኔ ፡ ላይ ፡ ያርቅ ፥



www.ethiopianorthodox.org

ግርማውም ፡ አያስፈራኝ ፤

35 ፤ እናገርም ፡ ነበር ፥ አልፈራውምም ፡ ነበር ፤

በራሴ ፡ እንዲህ ፡ አይደለኹምና ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ምዕራፍ ፡ 10 ።

1 ፤ ነፍሴ ፡ ሕይወቴን ፡ ሰለቸቻት ፤

የሐዘን ፡ እንጕርጕሮዬን ፡ እለቀዋለኹ ፤

በነፍሴም ፡ ምሬት ፡ እናገራለኹ ።

2 ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንዲህ ፡ እለዋለኹ ።

አትፍረድብኝ ፤ የምትከራከረኝ ፡ ለምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ንገረኝ ።

3 ፤ ልታስጨንቅና ፡ የእጅኽን ፡ ሥራ ፡ ልትንቅ ፡

የኃጥኣንንስ ፡ ምክር ፡ ልታበራ ፡

ባንተ ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ ነውን ፨

4 ፤ በእውኑ ፡ የሥጋ ፡ ዐይን ፡ አለኽን ፨

ወይስ ፡ ሰው ፡ እንደሚያይ ፡ ታያለኽን ፨

5 ፤ 6 ፤ ወይስ ፡ ክፋቴን ፡ ትፈላለግ ፡ ዘንድ ፥

ኀጢአቴንም ፡ ትመረምር ፡ ዘንድ ፥

ዘመንኽ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ዘመን ፡ ነውን ፨

ወይስ ፡ ዓመታትኽ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ዓመታት ፡ ናቸውን ፨

7 ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ በደለኛ ፡ እንዳልኾንኹ ፥

ከእጅኽም ፡ የሚያድን ፡ እንደሌለ ፡ አንተ ፡ታውቃለኽ ።

8 ፤ እጅኽ ፡ ለወሰችኝ ፥ ሠራችኝም ፤

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዞረኽ ፡ ታጠፋኝ ፡ ዘንድ ፡ ፈለግኽ ።

9 ፤ እንደ ፡ ጭቃ ፡ አድርገኽ ፡ እንደ ፡ ለወስኽኝ ፡ ዐስብ ፤

ወደ ፡ ትቢያም ፡ ትመልሰኛለኽን ፨

10 ፤ በእውኑ ፡ እንደ ፡ ወተት ፡ አላፈሰስኽኝምን ፨

እንደ ፡ ርጎስ ፡ አላረጋኽኝምን ፨

11 ፤ ቍርበትና ፡ ሥጋ ፡ አለበስኽኝ ፥

በዐጥንትና ፡ በኹርማትም ፡ አጠነከርኽኝ ።

12 ፤ ሕይወትና ፡ ቸርነት ፡ አደረግኽልኝ ፤

መጐብኘትኽም ፡ መንፈሴን ፡ ጠበቀች ።

13 ፤ እነዚህንም ፡ ነገሮች ፡ በልብኽ ፡ ውስጥ ፡ ሰወርኽ ።

ይህ ፡ ኹሉ ፡ በዐሳብኽ ፡ እንዳለ ፡ ዐውቃለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

14 ፤ ኀጢአት ፡ ብሠራ ፡ አንተ ፡ ትመለከተኛለኽ ፤

ከኀጢአቴም ፡ ንጹሕ ፡ አታደርገኝም ።

15 ፤ በደለኛ ፡ ብኾን ፡ ወዮልኝ ፤

ጻድቅም ፡ ብኾን ፡ ራሴን ፡ አላነሣም ፤

ጒስቊልናን ፡ ተሞልቻለኹ ፥

መከራዬንም ፡ ተመልክቻለኹ ።

16 ፤ ራሴም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ቢል ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ታድነኛለኽ ፤

ተመልሰኽም ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ታደርግብኛለኽ ፡

17 ፤ ምስክሮችኽን ፡ ታድስብኛለኽ ፤

ቍጣኽንም ፡ ታበዛብኛለኽ ፤

ጭፍራ ፡ በጭፍራ ፡ ላይ ፡ ትጨምርብኛለኽ ።

18 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ከማሕፀን ፡ አወጣኸኝ ፧

ዐይን ፡ ሳያየኝ ፡ ምነው ፡ በሞትኹ ።

19 ፤ እንዳልነበረ ፡ በኾንኹ ፤

ከማሕፀንም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ በወሰዱኝ ።

20 ፤ የሕይወቴ ፡ ዘመን ፡ ጥቂት ፡ አይደለምን ፧

21 ፤ ወደማልመለስበት ፡ ስፍራ ፥

ወደ ፡ ጨለማና ፡ ወደሞት ፡ ጥላ ፡ ምድር ፥

22 ፤ እንደ ፡ ጨለማም ፡ ወደጨለመች ፥

ሥርዐትም ፡ ወደሌለባት ፡ ወደሞት ፡ ጥላ ፥

ብርሃኗም ፡ እንደ ፡ ጨለማ ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ ምድር ፡ ሳልኼድ ፥

ጥቂት ፡ እጽናና ፡ ዘንድ ፡ ተወኝ ፥ ልቀቀኝም ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ምዕራፍ ፡ 11 ።

1 ፤ ነዕማታዊውም ፡ ሶፋር ፡ መለሰ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ በእውነ ፡ ለቃል ፡ ብዛት ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ አይገባምን ፧

ወይስ ፡ ተናጋሪ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጻድቅ ፡ ይቈጠራልን ፧

3 ፤ ትምክሕትኽስ ፡ ሰዎችን ፡ ዝም ፡ ያሠኛቸዋልን ፧

ብትሳለቅስ ፡ የሚያሳፍርኽ ፡ የለምን ፧

4 ፤ አንተ ፦ ትምህርቴ ፡ የተጣራ ፡ ነው ፥

በዐይንኽም ፡ ፊት ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ትላለኽ ።

5 ፤ ምነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢናገርኽ!

ባንተም ፡ ላይ ፡ ከንፈሩን ፡ ቢከፍት!



www.ethiopianorthodox.org

6 ፤ የጥበቡን ፡ ምስጢር ፡ ቢገልጥልኽ!

ማስተዋሉ ፡ ብዙ ፡ ነውና ።

እግዚአብሔር ፡ ለበደልኽ ፡ ከሚገባው ፡ አሳንሶ ፡ እንደሚያስከፍልኽ ፡ ዕወቅ ።

7 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ጥልቅ ፡ ነገር ፡ ልትመረምር ፡ ትችላለኽን ፧

ወይስ ፡ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ፈጽመኽ ፡ ልትመረምር ፡ ትችላለኽን ፧

8 ፤ ከሰማይ ፡ ይልቅ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፤ ምን ፡ ልታደርግ ፡ ትችላለኽ ፧

ከሲኦልም ፡ ይልቅ ፡ ይጠልቃል ፤ ምን ፡ ልታውቅ ፡ ትችላለኽ ፧

9 ፤ ርዝመቱ ፡ ከምድር ፡ ይልቅ ፡ ይረዝማል ፥

ከባሕርም ፡ ይልቅ ፡ ይሰፋል ።

10 ፤ ርሱ ፡ ቢያልፍ ፥ ቢዘጋም ፥ ጉባኤንም ፡ ቢሰበስብ ፥

የሚከለክለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

11 ፤ ምናምንቴዎችን ፡ ሰዎች ፡ ያውቃልና ፥

በደልንም ፡ ሲያይ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አይመለከትም ።

12 ፤ የሜዳ ፡ አህያ ፡ ግልገል ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ቢወለድ ፥

ያን ፡ ጊዜ ፡ ከንቱ ፡ ሰው ፡ ጥበብን ፡ ያገኛል ።

13 ፤ 14 ፤ በእጅኽ ፡ በደል ፡ ቢኖር ፡ አርቀው ፤

በድንኳንኽም ፡ ኀጢአት ፡ አይኑር ፤

አንተ ፡ ልብኽን ፡ ቅን ፡ ብታደርግ ፥

እጅኽንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ብትዘረጋ ፥

15 ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በእውነት ፡ ፊትኽን ፡ ያለነውር ፡ ታነሣለኽ ፤

ትበረታለኽ ፥ አትፈራምም ።

16 ፤ መከራኽንም ፡ ትረሳለኽ ፤

እንዳለፈ ፡ ውሃ ፡ ታስበዋለኽ ።

17 ፤ ከቀትር ፡ ይልቅ ፡ ሕይወትኽ ፡ ይበራል ፤

ጨለማም ፡ ቢኾን ፡ እንደ ፡ ጧት ፡ ይኾናል ።

18 ፤ ተስፋም ፡ ስለ ፡ አለኽ ፡ ተዘልለኽ ፡ ትቀመጣለኽ ፤

በዙሪያኽ ፡ ትመለከታለኽ ፥ በደኅንነትም ፡ ታርፋለኽ ።

19 ፤ ትተኛለኽ ፥ የሚያስፈራኽም ፡ የለም ፤

ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ልመና ፡ ያቀርቡልኻል ።

20 ፤ የክፉዎች ፡ ዐይን ፡ ግን ፡ ትጨልማለች ፤

የሚሸሹበትንም ፡ ያጣሉ ፥

ተስፋቸውም ፡ ነፍሳቸውን ፡ ማውጣት ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 12 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ በርግጥ ፡ እናንተ ፡ ዐይነተኛዎች ፡ ሰዎች ፡ ናችኹ ፤

ጥበብም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይሞታል ።

3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደናንተ ፡ ማስተዋል ፡ አለኝ ፤

ከእናንተም ፡ የማንስ ፡ አይደለኹም ፤

እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ የማያውቅ ፡ ማን ፡ ነው ፧

4 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የጠራኹ ፡ ርሱም ፡ የመለሰልኝ ፡ እኔ ፡

ለባልንጀራው ፡ መሳለቂያ ፡ እንደሚኾን ፡ ሰው ፡ ኾኛለኹ ፤

ጻድቅና ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ መሳለቂያ ፡ ኾኗል ።

5 ፤ ተዘልሎ ፡ በሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ ዐሳብ ፡ መከራ ፡ ይናቃል ፤

ነገር ፡ ግን ፡ እግሩን ፡ ሊያድጠው ፡ ተዘጋጅቷል ።

6 ፤ የቀማኞዎች ፡ ድንኳን ፡ በደኅንነት ፡ ይኖራል ፥

እግዚአብሔርንም ፡ የሚያስቈጡ ፡ ተዘልለው ፡ ተቀምጠዋል ፤

እግዚአብሔር ፡ ዅሉን ፡ በእጃቸው ፡ አምጥቶላቸዋል ።

7 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እንስሳዎችን ፡ ጠይቅ ፥ ያስተምሩኻማል ፤

የሰማይንም ፡ ወፎች ፡ ጠይቅ ፥ ይነግሩኻማል ።

8 ፤ ወይም ፡ ለምድር ፡ ተናገር ፥ ርሷም ፡ ታስተምርኻለች ፤

የባሕርም ፡ ዓሣዎች ፡ ይነግሩኻል ።

9 ፤ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ይህን ፡ እንዳደረገ ፡

ከነዚህ ፡ ዅሉ ፡ የማያውቅ ፡ ማን ፡ ነው ፧

10 ፤ የሕያዋን ፡ ዅሉ ፡ ነፍስ ፡

የሰውም ፡ ዅሉ ፡ መንፈስ ፡ በእጁ ፡ ናት ።

11 ፤ ምላስ ፡ መብልን ፡ እንደሚቀምስ ፥

ጆሮ ፡ ቃልን ፡ የሚለይ ፡ አይደለምን ፧

12 ፤ በሽምግልና ፡ ጊዜ ፡ ጥበብ ፥

በዘመንስ ፡ ርዝመት ፡ ማስተዋል ፡ ይገኛል ።

13 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጥበብና ፡ ኀይል ፡ አለ ፤

ለርሱ ፡ ምክርና ፡ ማስተዋል ፡ አለው ።

14 ፤ እንሆ ፥ ይፈርሳል ፥ የፈረሰውም ፡ ተመልሶ ፡ አይሠራም ፤

በሰውም ፡ ቢዘጋበት ፡ የሚከፍትለት ፡ የለም ።

15 ፤ እንሆ ፥ ውሃዎቹን ፡ ይከለክላል ፥ እነርሱም ፡ ይደርቃሉ ፤

እንደ ፡ ገና ፡ ይሰዳቸዋል ፥ ምድሪቱንም ፡ ይገለብጣሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

16 ፤ ኀይልና ፡ ጥበብ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ናቸው ፤

የሚስተውና ፡ የሚያስተው ፡ ለርሱ ፡ ናቸው ።

17 ፤ መካሮችንም ፡ እንደ ፡ ዘረፋ ፡ ይወስዳቸዋል ፥

ፈራጆችንም ፡ ያሳብዳል ።

18 ፤ የነገሥታትንም ፡ እስራት ፡ ይፈታል ፥

ወገባቸውንም ፡ በመታጠቂያ ፡ ያስራቸዋል ።

19 ፤ ካህናትን ፡ እንደ ፡ ዘረፋ ፡ ይወስዳቸዋል ፥

ኀያላንንም ፡ ይገለብጣቸዋል ።

20 ፤ ከታመኑ ፡ ሰዎችም ፡ ቋንቋን ፡ ያርቃል ፥

የሽማግሌዎችንም ፡ ማስተዋል ፡ ይወስድባቸዋል ።

21 ፤ በአለቃዎች ፡ ላይ ፡ ንቀትን ፡ ያፈሳል ፥

የብርቱዎችንም ፡ መታጠቂያ ፡ ያላላል ።

22 ፤ ጥልቅ ፡ ነገር ፡ ከጨለማ ፡ ይገልጣል ፥

የሞትንም ፡ ጥላ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ያወጣል ።

23 ፤ አሕዛብን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፥ እነርሱንም ፡ ያጠፋል ፤

አሕዛብንም ፡ ያሰፋል ፥ እነርሱንም ፡ ያፈልሳቸዋል ።

24 ፤ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡ አለቃዎች ፡ ዘንድ ፡ ማስተዋልን ፡ ይወስዳል ፥

መንገድም ፡ በሌለበት ፡ በረሓ ፡ ያቅበዘብዛቸዋል ።

25 ፤ ብርሃንም ፡ ሳይኖር ፡ በጨለማ ፡ ይርመሰመሳሉ ፤

እንደ ፡ ሰካራም ፡ ይቅበዘበዛሉ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ምዕራፍ ፡ 13 ።

1 ፤ እንሆ ፥ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ዐይኔ ፡ አየች ፤

ጆሮዬም ፡ ሰምታ ፡ አስተዋለችው ።

2 ፤ እናንተ ፡ የምታውቁትን ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ዐውቃለኹ ፤

ከእናንተ ፡ የማንስ ፡ አይደለኹም ።

3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉን ፡ ለሚችል ፡ አምላክ ፡ መናገር ፡ እፈልጋለኹ ፥

ከእግዚአብሔርም ፡ ጋራ ፡ ለመዋቀስ ፡ እሻለኹ ።

4 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ በሐሰት ፡ ለባጮች ፡ ናችኹ ፤

ኹላችኹ ፡ የማትጠቅሙ ፡ ባለመድኀኒቶች ፡ ናችኹ ።

5 ፤ ምነው ፡ ዝም ፡ ብላችኹ ፡ ብትኖሩ!

ይህ ፡ ጥበብ ፡ በኾነላችኹ ፡ ነበር ።

6 ፤ አኹንም ፡ ክርክሬን ፡ ስሙ ፥



www.ethiopianorthodox.org

የከንፈሬንም ፡ ሙግት ፡ አድምጡ ።

7 ፤ በእውኑ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሐሰትን ፡ ትናገራላችኹን ፧

ስለ ፡ ርሱም ፡ ሽንገላን ፡ ታወራላችኹን ፧

8 ፤ ለፊቱስ ፡ ታደላላችኹን ፧

ስለ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ ትከራከራላችኹን ፧

9 ፤ ቢመረምራችኹስ ፡ መልካም ፡ ይኾንላችኟልን ፧

ወይስ ፡ በሰው ፡ እንደምትሣለቁ ፡ ትሣለቁበታላችኹን ፧

10 ፤ በስውር ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ ብታደሉ ፡

ዘለፋ ፡ ይዘልፋችኟል ።

11 ፤ ክብሩስ ፡ አያስፈራችኹምን ፧

ግርማውስ ፡ አይወድቅባችኹምን ፧

12 ፤ ምስሌዎቻችኹ ፡ የዐመድ ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ፤

ምሽጎቻችኹ ፡ የጭቃ ፡ ምሽጎች ፡ ናቸው ።

13 ፤ ዝም ፡ በሉ ፥ እናገርም ፡ ዘንድ ፡ ተዉኝ ፤

የኾነው ፡ ነገር ፡ ይምጣብኝ ።

14 ፤ ሥጋዬን ፡ በጥርሴ ፡ እይዛለኹ ፥

ሕይወቴንም ፡ በእጄ ፡ አኖራለኹ ።

15 ፤ እንሆ ፥ ቢገድለኝ ፡ ስንኳ ፡ ርሱን ፡ በትዕግሥት ፡ እጠባበቃለኹ ፤

ነገር ፡ ግን ፡ መንገዴን ፡ በፊቱ ፡ አጸናለኹ ።

16 ፤ ዝንጉ ፡ ሰው ፡ በፊቱ ፡ አይገባምና ፡

ርሱ ፡ መድኀኒት ፡ ይኾንልኛል ።

17 ፤ ነገሬን ፡ ተግታችኹ ፡ ስሙ ፥

ምስክርነቴንም ፡ በጆሮቻችኹ ፡ አድምጡ ።

18 ፤ እንሆ ፥ ሙግቴን ፡ አዘጋጅቻለኹ ።

እንደምጸድቅም ፡ ዐውቃለኹ ።

19 ፤ ከእኔስ ፡ ጋራ ፡ የሚፋረድ ፡ ማን ፡ ነው ፧

አኹን ፡ እኔ ፡ ዝም ፡ ብል ፡ እሞታለኹ ።

20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹለት ፡ ነገር ፡ አታድርግብኝ ፤

የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከፊትኽ ፡ አልሰወርም ፤

21 ፤ እጅኽን ፡ ከእኔ ፡ አርቅ ፤

ግርማኽም ፡ አታስደንግጠኝ ።

22 ፤ ከዚያም ፡ በኺላ ፡ ጥራኝ ፥ እኔም ፡ እመልስልኻለኹ ።

ወይም ፡ እኔ ፡ ልናገር ፥ አንተም ፡ መልስልኝ ።



www.ethiopianorthodox.org

23 ፤ ያለብኝስ ፡ በደልና ፡ ኀጢአት ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ነው ፧

መተላለፌንና ፡ ኀጢአቴን ፡ አስታውቀኝ ።

24 ፤ ፊትኽን ፡ ከእኔ ፡ የሰወርኽ ፥

እንደ ፡ ጠላትኽም ፡ የቈጠርኸኝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፧

25 ፤ የረገፈውን ፡ ቅጠል ፡ ታስጨንቃለኽን ፧

ወይስ ፡ የደረቀውን ፡ ዕብቅ ፡ ታሳድዳለኽን ፧

26 ፤ የመረረ ፡ ነገር ፡ ጽፈኽብኛልና ፤

የሕፃንነቴንም ፡ ኀጢአት ፡ ታወርሰኛለኽ ።

27 ፤ እግሬንም ፡ በእግር ፡ ግንድ ፡ አግብተኻል ፥

መንገዴንም ፡ ኹሉ ፡ መርምረኻል ፤

የእግሬን ፡ ፍለጋ ፡ ወስነኻል ።

28 ፤ እኔ ፡ እንደሚጠፋ ፡ በስባሳ ፡ ነገር ፥

ብልም ፡ እንደሚበላው ፡ ልብስ ፡ ነኝ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ምዕራፍ ፡ 14 ።

1 ፤ ከሴት ፡ የተወለደ ፡ ሰው ፡

የሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ነው ፥ መከራም ፡ ይሞላዋል ።

2 ፤ እንደ ፡ አበባ ፡ ይወጣል ፥ ይረግፋልም ፤

እንደ ፡ ጥላም ፡ ይሸሻል ፥ ርሱም ፡ አይጸናም ።

3 ፤ እንደዚህስ ፡ ባለ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ዐይኖችኽን ፡ ትከፍታለኽን ፧

ከአንተስ ፡ ጋራ ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ታገባለኽን ፧

4 ፤ ከርኩስ ፡ ነገር ፡ ንጹሕን ፡ ሊያወጣ ፡ ማን ፡ ይችላል ፧

አንድ ፡ እንኳ ፡ የሚችል ፡ የለም ።

5 ፤ የሰው ፡ ዕድሜ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፥

የወሩም ፡ ቍጥር ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፥

ርሱም ፡ ሊተላለፈው ፡ የማይችለውን ፡ ዳርቻ ፡ አደረግኽለት ።

6 ፤ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ ዕድሜው ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡

ያርፍ ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ ጥቂት ፡ ዘወር ፡ በል ።

7 ፤ ዛፍ ፡ ቢቈረጥ ፡ ደግሞ ፡ ያቈጠቍጥ ፡ ዘንድ ፥

ቅርንጫፉም ፡ እንዳያልቅ ፡ ተስፋ ፡ አለው ።

8 ፤ ሥሩም ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ቢያረጅ ፥

ግንዱም ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ቢሞት ፥

9 ፤ ከውሃ ፡ ሽታ ፡ የተነሣ ፡ ያቈጠቍጣል ፤



www.ethiopianorthodox.org

እንደ ፡ አትክልት ፡ ቅርንጫፍ ፡ ያወጣል ።

10 ፤ ሰው ፡ ግን ፡ ይሞትና ፡ ይጋደማል ፤

ሰውም ፡ ነፍሱን ፡ ይሰጣል ፥ ርሱስ ፡ ወዴት ፡ አለ ፦

11 ፤ ውሃ ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ያልቃል ፤

ወንዙም ፡ ያንሳል ፡ ይደርቅማል ።

12 ፤ ሰውም ፡ ተኝቶ ፡ አይነሣም ፤

ሰማይ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ አይነቃም ፥

ከእንቅልፉም ፡ አይነሣም ።

13 ፤ በሲኦል ፡ ውስጥ ፡ ምነው ፡ በሰወርኸኝ ፡ ኖሮ!

ቍጣኽ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ በሸሸግኸኝ ፡ ኖሮ!

ቀጠሮም ፡ አድርገኽ ፡ ምነው ፡ ባሰብኸኝ ፡ ኖሮ!

14 ፤ በእውኑ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ ተመልሶ ፡ሕያው ፡ ይኾናልን ፦

መለወጤ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፥

የሰልፌን ፡ ዘመን ፡ ዅሉ ፡ በትዕግሥት ፡ በተጠባበቅኹ ፡ ነበር ።

15 ፤ በጠራኸኝና ፡ በመለስኹልኽ ፡ ነበር ፤

የእጅኽንም ፡ ሥራ ፡ በተመኘኸው ፡ ነበር ።

16 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ርምጃዬን ፡ ቈጥረኸዋል ፤

ኀጢአቴንም ፡ ትጠባበቃለኽ ።

17 ፤ መተላለፌ ፡ በከረጢት ፡ ውስጥ ፡ ታትሟል ፥

ኀጢአቴንም ፡ ለብጠኽበታል ።

18 ፤ ተራራ ፡ ሲወድቅ ፡ ይጠፋል ፥

አለቱም ፡ ከስፍራው ፡ ይፈልሳል ፤

19 ፤ ውሃዎች ፡ ድንጋዮቹን ፡ ይፍቃሉ ፤

ፈሳሾቹም ፡ የምድሩን ፡ ዐፈር ፡ ይወስዳሉ ፤

እንዲሁ ፡ የሰውን ፡ ተስፋ ፡ ታጠፋዋለኽ ።

20 ፤ ለዘለዓለም ፡ ታሸንፈዋለኽ ፥ ርሱም ፡ ያልፋል ፤

ፊቱን ፡ ትለውጣለኽ ፥ ርሱንም ፡ ትሰደዋለኽ ።

21 ፤ ልጆቹ ፡ ቢከብሩ ፡ አያውቅም ፤

ቢዋረዱም ፡ አያይም ።

22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የገዛ ፡ ሥጋው ፡ ሕመም ፡ ብቻ ፡ ይሰማዋል ፥

ለራሱም ፡ ብቻ ፡ ያለቅሳል ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ምዕራፍ ፡ 15 ።



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ ቴማናዊው ፡ ኤልፋዝ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ በእውኑ ፡ ጠቢብ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ በኾነ ፡ ዕውቀት ፡ ይመልሳልን ፧

በሆዱስ ፡ የምሥራቅን ፡ ነፋስ ፡ ይሞላልን ፧

3 ፤ ከማይረባ ፡ ነገር ፥

ወይስ ፡ ከማይጠቅም ፡ ንግግር ፡ ጋራ ፡ ይዋቀሳልን ፧

4 ፤ አንተም ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ታፈርሳለኽ ፤

በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አምልኮን ፡ ታስቀራለኽ ።

5 ፤ በደልኽ ፡ አፍኽን ፡ ያስተምረዋል ፥

የተንኰለኞዎችንም ፡ አንደበት ፡ ትመርጣለኽ ።

6 ፤ የሚፈርድብኽ ፡ አፍኽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ።

ከንፈሮችኽም ፡ ይመሰክሩብኻል ።

7 ፤ በእውኑ ፡ መዠመሪያ ፡ የተወለድኽ ፡ ሰው ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧

ወይስ ፡ ከተራራዎች ፡ በፊት ፡ ተፀነስኽን ፧

8 ፤ የእግዚአብሔርንስ ፡ ምስጢር ፡ ሰምተኻልን ፧

ወይስ ፡ ጥበብን ፡ ለብቻኽ ፡ አድርገኻልን ፧

9 ፤ እኛ ፡ የማናውቀውን ፡ አንተ ፡ የምታወቀው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ከእኛ ፡ ዘንድስ ፡ የሌለው ፡ የምታስተውለው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

10 ፤ በዕድሜ ፡ ከአባትኽ ፡ የሚበልጡ ፡

ሽበትም ፡ ያላቸው ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ አሉ ።

11 ፤ በእውኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማጽናናት ፥

በየውሀትም ፡ የተነገረኽ ፡ ቃል ፡ ጥቂት ፡ ነውን ፧

12 ፤ ልብኽስ ፡ ለምን ፡ ይወስድኻል ፧

ዐይኖችኽስ ፡ ለምን ፡ ይገለምጣሉ ፧

13 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ መንፈስኽን ፡ እስከ ፡ ማንሣት ፡ ደርሰኽ ፤

ይህንም ፡ ቃል ፡ ከአፍኽ ፡ እስከ ፡ ማውጣት ፡ ደርሰኽ ።

14 ፤ ንጹሕ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ጻድቅስ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ከሴት ፡ የተወለደ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

15 ፤ እንሆ ፥ በቅዱሳኑ ፡ ስንኳ ፡ አይታመንም ፤

ሰማያትም ፡ በፊቱ ፡ ንጹሓን ፡ አይደሉም ።

16 ፤ ይልቁንስ ፡ አስጸያፊና ፡ የረከሰ ፥

ኀጢአትንም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ የሚጠጣ ፡ ሰው ፡ ምንኛ ፡ ያንስ ፧

17 ፤ 18 ፤ ምድሪቱ ፡ ለብቻቸው ፡ ተሰጥታ ፡ የነበር ፥

19 ፤ በመካከላቸውም ፡ እንግዳ ፡ ያልገባባቸው ፡ ጠቢባን ።



www.ethiopianorthodox.org

ከአባቶቻቸው ፡ ተቀብለው ፡ የተናገሩትን ፡ ያልሸሸጉትንም ፥
እገልጥልኻለኹ ፥ ስማኝ ፤ ያየኹትንም ፡ እነግርኻለኹ ።
20 ፤ ክፉ ፡ ሰው ፡ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፥
ከግፈኛ ፡ በተመደቡለት ፡ በዓመታት ፡ ኹሉ ፡ በሕመም ፡ ይጣጣራል ።
21 ፤ የሚያስደነግጥ ፡ ድምፅ ፡ በገሮው ፡ ነው ፤
በደኅንነቱም ፡ ሳለ ፡ ቀማኛ ፡ ይመጣበታል ።
22 ፤ ከጨለማ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲወጣ ፡ አያምንም ፥
ሰይፍም ፡ ይሸምቅበታል ።
23 ፤ ተቅበዝብዞም ፡— ወዴት ፡ አለ ፡፡ እያለ ፡ እንጀራ ፡ ይለምናል ፤
የጨለማ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ቀረበበት ፡ ያውቃል ።
24 ፤ መከራና ፡ ጭንቀት ፡ ያስፈራሩታል ፤
ለሰልፍ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ንጉሥ ፡ ያሸንፉታል ፤
25 ፤ እጁን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ዘርግቷልና ፥
ኹሉንም ፡ በሚችል ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ደፍሯልና ፥
26 ፤ በደንዳና ፡ ዐንገቱና ፡ በወፍራሙ ፡ በጋሻው ፡
ጉብጉብ ፡ እየሰገገ ፡ ይመጣበታልና ፥
27 ፤ በስብም ፡ ፊቱን ፡ ከድኗልና ፥
ስቡንም ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ አድርጓልና ፥
28 ፤ በተፈቱም ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፥
ሰውም ፡ በሌለባቸው ፥
ክምር ፡ ለመኾን ፡ በተመደቡ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጧልና ፥
29 ፤ ባለጠጋ ፡ አይኾንም ፥ ሀብቱም ፡ አይጸናም ፤
ጥላውንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይጥልም ፤
30 ፤ ከጨለማ ፡ አይወጣም ፤
ነበልባሉም ፡ ቅርንጫፎቹን ፡ ያደርቃቸዋል ፥
አበባዎቹም ፡ ይረግፋሉ ።
31 ፤ ዋጋው ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ይኾናልና ፥
ራሱን ፡ እያሳተ ፡ በከንቱ ፡ ነገር ፡ አይታመን ።
32 ፤ ቀኑ ፡ ሳይደርስ ፡ ጊዜው ፡ ይፈጸማል ፥
ቅርንጫፉም ፡ አይለመልምም ።
33 ፤ እንደ ፡ ወይን ፡ ያልበሰለውን ፡ ዘለላ ፡ ያረግፋል ፤
እንደ ፡ ወይራ ፡ አበባውን ፡ ይጥላል ።
34 ፤ የዝንጉዎች ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ ለጥፋት ፡ ይኾናል ፥



www.ethiopianorthodox.org

የጉቦ ፡ ተቀባዮችንም ፡ ድንኳን ፡ እሳት ፡ ትበላለች ።

35 ፤ ጉዳትን ፡ ይፀንሳሉ ፥ በደልንም ፡ ይወልዳሉ ፥

ሆዳቸውም ፡ ተንኰልን ፡ ያዘጋጃል ።

______________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። ______________________

ምዕራፍ ፡ 16 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ ሰማኹ ፤

እናንተ ፡ ኹላችኹ ፡ የምታደክሙ ፡ አጽናኞች ፡ ናችኹ ።

3 ፤ በእውኑ ፡ ከንቱ ፡ ቃል ፡ ይፈጸማልን ፨

ወይስ ፡ ትመልስ ፡ ዘንድ ፡ ያነሣሣኽ ፡ ምንድር ፡ ነው ፨

4 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደናንተ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ይቻለኝ ፡ ነበር ፤

ነፍሳችኹ ፡ በነፍሴ ፡ ፋንታ ፡ ቢኾን ፡ኖሮ ፥

እኔ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ ማሳካት ፥

ራሴንም ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ መነቅነቅ ፡ በተቻለኝ ፡ ነበር ።

5 ፤ በአፌም ፡ ነገር ፡ ባበረታኋችኹ ፡ ነበር ፤

የከንፈሬን ፡ ማጽናናት ፡ ባልከለከልኹም ፡ ነበር ።

6 ፤ እኔ ፡ ብናገር ፡ ሕማሜ ፡ አይቀነስም ፤

ዝምም ፡ ብል ፡ ከእኔ ፡ አይወገድም ።

7 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ አደክሞኛል ፤

ወገኔንም ፡ ኹሉ ፡ አፍርሰኻል ።

8 ፤ መጨማተሬ ፡ ይመሰክርብኛል ፤

ክሳቴም ፡ ተነሥቶብኛል ፤

በፊቴም ፡ ይመሰክርብኛል ።

9 ፤ በቍጣው ፡ ቀደደኝ ፥ ርሱም ፡ ጠላኝ ፤

ጥርሶቹንም ፡ አፋጨብኝ ፤

ጠላቴ ፡ ዐይኑን ፡ አፈጠጠብኝ ፤

10 ፤ እነርሱም ፡ አፋቸውን ፡ ከፈቱብኝ ፤

እያላገጡ ፡ ጕንጨን ፡ ጠፈጠፉኝ ፤

በአንድነትም ፡ ተሰበሰቡብኝ ።

11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለጠማማ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠኝ ፥

በክፉዎችም ፡ እጅ ፡ ጣለኝ ።

12 ፤ ተዘልዬ ፡ ተቀምጬ ፡ ነበር ፥ ርሱም ፡ሰበረኝ ፤

ዐንገቴንም ፡ ይዞ ፡ ቀጠቀጠኝ ፤



www.ethiopianorthodox.org

እንደ ፡ ዐላማ ፡ አድርጎ ፡ አቆመኝ ።

13 ፤ ቀስተኛዎቹ ፡ ከበቡኝ ፤

ኵላሊቴንም ፡ ቈራረጠ ፥ ርሱም ፡ አልራራም ፤

ሐሞቴን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አፈሰሰ ።

14 ፤ በቍስል ፡ ላይ ፡ ቍስል ፡ ጨመረብኝ ፤

እንደ ፡ ኀያል ፡ እየሰገገ ፡ ይሮጥብኛል ።

15 ፤ በቍርበቴ ፡ ላይ ፡ ማቅ ፡ ሰፋኹ ፥

ቀንዴንም ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ አኖርኹ ።

16 ፤ ፊቴ ፡ ከልቅሶ ፡ የተነሣ ፡ ቀላ ፤

የሞት ፡ ጥላ ፡ በዐይኖቼ ፡ ቆብ ፡ ላይ ፡ አለ ፤

17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእጄ ፡ ዐመፅ ፡ የለም ፤

ጸሎቴም ፡ ንጹሕ ፡ ነው ።

18 ፤ ምድር ፡ ሆይ ፥ ደሜን ፡ አትክደኚ ፥

ለጩኸቴም ፡ ማረፊያ ፡ አይኹን ።

19 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ ምስክሬ ፡ በሰማይ ፡ አለ ፥

የሚመሰክርልኝም ፡ በአርያም ፡ ነው ።

20 ፤ ጸሎቴ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይድረስ ፥

ዐይኔም ፡ በፊቱ ፡ እንባ ፡ ታፍስ ።

21 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከባልንጀራው ፡ ጋራ ፡ እንደሚሟገት ፥

ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመሟገት ፡ ምነው ፡ በቻለ!

22 ፤ ጥቂቶች ፡ ዓመታት ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡

እኔ ፡ ወደማልመለስበት ፡ መንገድ ፡ እኼዳለኹ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ምዕራፍ ፡ 17 ።

1 ፤ መንፈሴ ፡ ደከመ ፥ ዘመኔ ፡ አለቀ ፥

መቃብርም ፡ ተዘጋጅቶልኛል ።

2 ፤ አላጋጮች ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ አሉ ፥

ዐይኔም ፡ በማስቈጣታቸው ፡ ዐደረች ።

3 ፤ አኹንም ፡ አንተ ፡ መያዣ ፡ ኹነኽ ፡ ተዋሰኝ ፤

ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አጋና ፡ የሚመታ ፡ ማን ፡ ነው ፧

4 ፤ ልባቸውም ፡ እንዳያስተውል ፡ ከልክለኸዋል ፤

ስለዚህ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አታደርጋቸውም ።

5 ፤ ለብዝበዛ ፡ ባልንጀራዎቹን ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፥



www.ethiopianorthodox.org

የልጆቹ ፡ ዐይን ፡ ይጨልማል ።

6 ፤ ለሕዝብም ፡ ምሳሌ ፡ አደረገኝ ፤

በፊቱ ፡ ላይ ፡ ጺቅ ፡ እንደሚሉበት ፡ ሰው ፡ ኾንኹ ።

7 ፤ ዐይኔም ፡ ከሐዘን ፡ የተነሣ ፡ ፈዘዘች ፤

ብልቶቼም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ኾኑ ።

8 ፤ ቅኖች ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ይደነቃሉ ፤

ንጹሕም ፡ በዝንጉው ፡ ላይ ፡ ይበሳጫል ።

9 ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ መንገዱን ፡ ያጠነክራል ፤

እጁም ፡ ንጹሕ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ኀይልን ፡ እየጨመረ ፡ ይኼዳል ።

10 ፤ ነገር ፡ ግን ፤ እናንተ ፡ ኹሉ ፡ ተመልሳችኹ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ኑ ፤

በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ብልኀተኛ ፡ አላገኝም ።

11 ፤ ዕድሜዬ ፡ ዐለፈች ፤

ዐሳቤና ፡ የልቤ ፡ መሣሪያ ፡ ተቈረጠ ።

12 ፤ ሌሊቱን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ ይለውጣሉ ፤

ብርሃኑም ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ የቀረበ ፡ ይመስላቸዋል ።

13 ፤ ተስፋ ፡ ባደርግ ፡ ሲኦል ፡ ቤቴ ፡ ናት ፤

ምንጣፌንም ፡ በጨለማ ፡ ዘርግቻለኹ ።

14 ፤ መበስበስን ፦ አንተ ፡ አባቴ ፡ ነኽ ፤

ትልንም ፦ አንቺ ፡ እናቴ ፣ እኅቴም ፡ ነሽ ፡ ብያለኹ ።

15 ፤ እንግዲህ ፡ ተስፋዬ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡፡

ተስፋዬንስ ፡ የሚያይ ፡ ማን ፡ ነው ፡፡

16 ፤ ዐብረን ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ስናርፍ ፤

ወደ ፡ ሲኦል ፡ ይወርዳል ።

__________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፤ ምዕራፍ ፡ 18 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 18 ።

1 ፤ ሹሐዊውም ፡ በልዳዶስ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ ቃልን ፡ ታጠምዳለኽ ፡፡

አስተውል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንናገራለን ።

3 ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ እንደ ፡ እንስሳዎች ፡ ተቈጠርን ፡፡

ስለ ፡ ምንስ ፡ በዐይንኽ ፡ ፊት ፡ ረከስን ፡፡

4 ፤ ቍጣ ፡ ወርሶኻል ፤ አንተስ ፡ የሞትኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ምድር ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ባድማ ፡ ትኾናለችን ፡፡

ወይስ ፡ አለት ፡ ከስፍራው ፡ ይነቀላልን ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

5 ፤ የኀጢአተኛ ፡ መብራት ፡ ይጠፋል ፥

የእሳቱም ፡ ነበልባል ፡ ብልጭ ፡ አይልም ።

6 ፤ ብርሃን ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ይጨልማል ፥

መብራቱም ፡ በላዩ ፡ ይጠፋል ።

7 ፤ የኀይሉም ፡ ርምጃ ፡ ትጠባለች ፥

ምክሩም ፡ ትጥለዋለች ።

8 ፤ እግሩ ፡ በወጥመድ ፡ ትያዛለች ፥

በመረብም ፡ ላይ ፡ ይኼዳል ።

9 ፤ አሽክላ ፡ ሰኰናውን ፡ ይይዛል ፥

ወስፈንጠርም ፡ ይበረታበታል ።

10 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ የሽምቀቆ ፡ ገመድ ፥

በመንገዱም ፡ ላይ ፡ ወጥመድ ፡ ለርሱ ፡ ተሰውራለች ።

11 ፤ ድንጋጤ ፡ በዙሪያው ፡ ታስፈራዋለች ፥

በስተ ኋላውም ፡ ኾና ፡ ታባርራቸዋለች ።

12 ፤ ኀይሉ ፡ በራብ ፡ ትደክማለች ፥

መቅሠፍትም ፡ እስኪሰናከል ፡ ተዘጋጅቶለታል ።

13 ፤ የሰውነቱ ፡ ብልቶች ፡ ይጠፋሉ ፤

የሞትም ፡ በኵር ፡ ልጅ ፡ ብልቶቹን ፡ ይበላል ።

14 ፤ ከሚታመንበት ፡ ድንኳን ፡ ይነቀላል ፤

ወደ ፡ ድንጋጤም ፡ ንጉሥ ፡ ያስቸኵሉታል ።

15 ፤ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ለርሱ ፡ የማይኾነው ፡ ይኖራል ፤

በመኖሪያውም ፡ ላይ ፡ ዲን ፡ ይበተናል ።

16 ፤ ሥሩ ፡ ከበታቹ ፡ ይደርቃል ፥

ጫፉም ፡ ከበላይ ፡ ይረግፋል ።

17 ፤ መታሰቢያው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ይጠፋል ፥

በሜዳም ፡ ስም ፡ አይቀርለትም ።

18 ፤ ከብርሃን ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ያፈልሱታል ፥

ከዓለምም ፡ ያሳድዱታል ።

19 ፤ ዘርም ፡ ትውልድም ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ አይኾንለትም ፤

በመኖሪያውም ፡ ውስጥ ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ አይቀርለትም ።

20 ፤ የፊተኛዎች ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ደነገጡ ፥

እንዲሁ ፡ የኋለኛዎች ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ዘመኑ ፡ ይደነቃሉ ።

21 ፤ በእውነት ፡ የኀጢአተኛዎች ፡ ቤት ፡ እንዲሁ ፡ ናት ፥



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርንም ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡ስፍራ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ምዕራፍ ፡ 19 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ ነፍሴን ፡ የምትነዘንዙ ፥

በቃልስ ፡ የምታደቁኝ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

3 ፤ ይኸው ፡ ስትሰድቡኝ ፡ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤

ስታሻክሩኝም ፡ አላፈራችኹም ።

4 ፤ በእውነትም ፡ የሳትኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ስሕተቴ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ትኖራለች ።

5 ፤ በእውነትም ፡ ብትጓደዱብኝ ፥

መዋረዴን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ብትከራከሩ ፥

6 ፤ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ገለበጠኝ ፥

በመረቡም ፡ እንደ ፡ ከበበኝ ፡ ዕወቁ ።

7 ፤ እነሆ ፥ ስለተደረገብኝ ፡ ግፍ ፡ ብጮኽ ፡ ማንም ፡ አይመልስልኝም ፤

አሰምቼም ፡ ብጠራ ፡ ፍርድ ፡ የለኝም ።

8 ፤ እንዳላልፍ ፡ መንገዴን ፡ ዘግቶታል ፥

በጐዳናዬም ፡ ጨለማ ፡ አኑሮበታል ።

9 ፤ ክብሬን ፡ ገፈፈኝ ፥

ዘውዴንም ፡ ከራሴ ፡ ላይ ፡ ወሰደ ።

10 ፤ በዚህና ፡ በዚያም ፡ አፈረሰኝ ፥ እኔም ፡ ኼድኹ ፤

ተስፋዬንም ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ነቀለው ፤

11 ፤ ቍጣውንም ፡ አነደደብኝ ፥

እንደ ፡ ጠላቱም ፡ ቈጠረኝ ።

12 ፤ ሰራዊቱ ፡ ዐብረው ፡ መጡ ፥

መንገዳቸውንም ፡ በላዬ ፡ አዘጋጁ ፥

በድንኳኔም ፡ ዙሪያ ፡ ሰፈሩ ።

13 ፤ ወንድሞቼን ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አራቀ ፥

የሚያውቁኝም ፡ አጥብቀው ፡ ተለዩኝ ።

14 ፤ ዘመዶቼ ፡ ተቋረጡ ፥

ወዳጆቼም ፡ ረሱኝ ።

15 ፤ ቤተ ፡ ሰቦቼና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎቼ ፡ እንደ ፡ መጻተኛ ፡ ቈጠሩኝ ፤

በዐይናቸውም ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ኾንኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

16 ፤ ባሪያዬን ፡ ብጠራ ፥ በአፌም ፡ ባቈላምጥ ፡ አይመልስልኝም ።

17 ፤ ሚስቴ ፡ እስትንፋሴን ፡ ጠላች ፥

የእናቴም ፡ ማሕፀን ፡ ልጆች ፡ ልመናዬን ፡ ጠሉ ።

18 ፤ ሕፃናት ፡ እንኳ ፡ አጠቁኝ ፤

ብነሣም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ይናገራሉ ።

19 ፤ አማካሪዎቼ ፡ ኹሉ ፡ ተጸየፉኝ ፤

እኔ ፡ የምወዳቸው ፡ በላዬ ፡ ተገለበጡ ።

20 ፤ ዐጥንቴ ፡ ከቍርበቴና ፡ ከሥጋዬ ፡ ጋራ ፡ ተጣበቀ ፤

ድድ ፡ ብቻ ፡ ቀርቶልኝ ፡ አመለጥኹ ።

21 ፤ እናንተ ፡ ወዳጆቼ ፡ ሆይ ፥ ማሩኝ ፤

የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መትታኛለችና ፡ ማሩኝ ።

22 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታሳድዱኛላችኹ ፧

ከሥጋዬስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አትጠግቡም ፧

23 ፤ ምነው ፡ አኹን ፡ ቃሌ ፡ ቢጻፍ!

ምነው ፡ በመጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ቢታተም!

24 ፤ ምነው ፡ በብረት ፡ ብርና ፡ በርሳስ ፡

በአለቱ ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ ቢቀረጽ!

25 ፤ እኔን ፡ ግን ፡ የሚቤዠኝ ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

በመጨረሻም ፡ ዘመን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንዲቆም ፥

26 ፤ ይህ ፡ ቍርበቴም ፡ ከጠፋ ፡ በኋላ ፥

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከሥጋዬ ፡ ተለይቼ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳይ ፡ ዐውቃለኹ ።

27 ፤ እኔ ፡ ራሴ ፡ አየዋለኹ ፥

ዐይኖቼም ፡ ይመለከቱታል ፥

ከእኔም ፡ ሌላ ፡ አይደለም ።

ልቤ ፡ በመናፈቅ ፡ ዝሏል ።

28 ፤ በእውነት ፡— እንዴት ፡ እናሳድደዋለን ፧

የነገሩ ፡ ሥር ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተገኝቷል ፡ ብትሉ ፥

29 ፤ ፍርድ ፡ እንዳለ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡

ቍጣ ፡ የሰይፍን ፡ ቅጣት ፡ ያመጣልና ፥

ከሰይፍ ፡ ፍሩ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ምዕራፍ ፡ 20 ።

1 ፤ ናዕማታዊውም ፡ ሶፋር ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡—



www.ethiopianorthodox.org

2 ፤ ስለዚህ ፥ በውስጤ ፡ ስላለው ፡ ችኰላ ፡ ዐሳቤ ፡ ትመልስልኛለች ።

3 ፤ የሚያሳፍረኝንም ፡ ተግሣጽ ፡ ሰምቻለኹ ፥

የማስተዋሌም ፡ መንፈስ ፡ ይመልስልኛል ።

4 ፤ ሰው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከተቀመጠ ፥ ከዱሮ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፥

5 ፤ የኀጢአተኛ ፡ ፉከራ ፡ ዐጪር ፡ መኾኑን ፡

የዝንጉዎችም ፡ ደስታ ፡ ቅጽበት ፡ መኾኑን ፡ አታውቁምን ፧

6 ፤ ከፍታው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ቢወጣ ፥

ራሱም ፡ እስከ ፡ ደመና ፡ ቢደርስ ፥

7 ፤ እንደ ፡ ፋንድያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጠፋል ፤

ያዩትም ፦ ወዴት ፡ ነው ፧ ይላሉ ።

8 ፤ እንደ ፡ ሕልም ፡ ይበራል ፥ ርሱም ፡ አይገኝም ፤

እንደ ፡ ሌሊትም ፡ ራእይ ፡ ይሰደዳል ።

9 ፤ ያየችውም ፡ ዐይን ፡ ዳግመኛ ፡ አታየውም ፤

ስፍራውም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይመለከተውም ።

10 ፤ ልጆቹ ፡ ድኻዎቹን ፡ ያቈላምጣሉ ፤

እጁ ፡ ሀብቱን ፡ ይመልሳል ።

11 ፤ ዐጥንቶቹ ፡ ብላቴንነቱን ፡ ሞልተዋል ፤

ነገር ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ይተኛል ።

12 ፤ ክፋት ፡ በአፉ ፡ ውስጥ ፡ ቢጣፍጥ ፥

ከምላሱም ፡ በታች ፡ ቢሰውረው ፥

13 ፤ ቢጠብቀውም ፡ ባይተወውም ፥

በጕረሮውም ፡ ቢይዘው ፥

14 ፤ መብሉ ፡ በአንዠቱ ፡ ውስጥ ፡ ይገላበጣል ፤

እንደ ፡ እፍኝትም ፡ ሐሞት ፡ በውስጡ ፡ ይኾናል ።

15 ፤ የዋጠውን ፡ ሀብት ፡ ይተፋዋል ፤

እግዚአብሔርም ፡ ከሆዱ ፡ ውስጥ ፡ ያወጣዋል ።

16 ፤ የእፍኝትን ፡ መርዝ ፡ ይጠባል ፤

የእባብም ፡ ምላስ ፡ ይገድለዋል ።

17 ፤ የማሩንና ፡ የቅቤውን ፡ ፈሳሽ ፡

ወንዞቹንም ፡ አይመለከትም ።

18 ፤ የድካሙን ፡ ፍሬ ፡ ሳይውጠው ፡ ይመልሰዋል ፤

እንደ ፡ ንግዱም ፡ ትርፍ ፡ አይደሰትም ።

19 ፤ ድኻውን ፡ አስጨንቋል ፥ ትቶታልም ፤



www.ethiopianorthodox.org

ያልሠራውንም ፡ ቤት ፡ በዝብዟል ።

20 ፤ ሆዱ ፡ ዕረፍትን ፡ አላወቀምና ፡

የወደደው ፡ ነገር ፡ አላዳነውም ።

21 ፤ ርሱ ፡ ከበላ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ አልተረፈም ፤

ስለዚህ ፡ በረከቱ ፡ አይከናወንለትም ።

22 ፤ በጠገበ ፡ ጊዜ ፡ ይጨነቃል ፤

የችግረኛዎችም ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ ታገኝዋለች ።

23 ፤ ሆዱን ፡ ሳያጠግብ ፡

እግዚአብሔር ፡ የቍጣውን ፡ ትኵሳት ፡ ይሰድበታል ፥

ሲበላም ፡ ያዘንብበታል ።

24 ፤ ከብረት ፡ መሣሪያም ፡ ይሸሻል ፥

የናስም ፡ ቀስት ፡ ይወጋዋል ።

25 ፤ ርሱም ፡ ይመዝዋል ፥ ከሥጋውም ፡ ይወጣል ፤

ከሐሞቱም ፡ ብልጭ ፡ ብሎ ፡ ይሠርጻል ፤

ፍርሀትም ፡ ይወድቅበታል ።

26 ፤ ጨለማ ፡ ኹሉ ፡ ስለከበረው ፡ ዕቃ ፡ ተዘጋጅቷል ፤

በሰው ፡ አፍ ፡ እፍ ፡ የማትባል ፡ እሳት ፡ ትበላዋለች ፤

በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ የቀረው ፡ ይጨነቅባታል ።

27 ፤ ሰማይ ፡ ኀጢአቱን ፡ ይገልጥበታል ፥

ምድርም ፡ ትነሣበታለች ።

28 ፤ የቤቱም ፡ ባለጠግነት ፡ ይኼዳል ፤

በቍጣው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ያልፋል ።

29 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የበደለኛ ፡ ሰው ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፥

ከእግዚአብሔርም ፡ የተመደበ ፡ ርስቱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ምዕራፍ ፡ 21 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ ስሙ ፥ ቃሌን ፡ ስሙ ፤

ይህም ፡ መጽናናታችኹ ፡ ይኹን ።

3 ፤ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ተዉኝ ፤

ከተናገርኹም ፡ በኋላ ፡ ተሣለቁ ።

4 ፤ በእውኑ ፡ የሐዘን ፡ እንጕርጕሮዬ ፡ ለሰው ፡ እናገራለኹን ፧

አለመታገሥ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አይገባኝም ፧



www.ethiopianorthodox.org

5 ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመልከቱ ፥ ተደነቁም ፤

እጃችኹንም ፡ በአፋችኹ ፡ ላይ ፡ አኑሩ ።

6 ፤ እኔ ፡ ባሰብኹ ፡ ቍጥር ፡ እጨነቃለኹ ፥

ጻዕርም ፡ ሥጋዬን ፡ ይይዛል ።

7 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ኀጢአተኛዎች ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉ ፧

ስለ ፡ ምንስ ፡ ያረጃሉ ፧ በባለጠግነትስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይበረታሉ ፧

8 ፤ ዘራቸው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፥

ልጆቻቸውም ፡ በዐይናቸው ፡ ፊት ፡ ናቸው ።

9 ፤ ቤታቸው ፡ ከፍርሀት ፡ ወጥቶ ፡ የታመነ ፡ ነው ፥

የእግዚአብሔርም ፡ በትር ፡ የለባቸውም ።

10 ፤ ኰርማቸው ፡ ይወልዳል ፥ ዘሩንም ፡ አይጥለውም ፤

ላማቸውም ፡ ትወልዳለች ፥ አትጨነግፍም ።

11 ፤ ሕፃናታቸውን ፡ እንደ ፡ መንጋ ፡ ያወጣሉ ፥

ልጆቻቸውም ፡ ይዘፍናሉ ።

12 ፤ ከበሮና ፡ መሰንቆ ፡ ወስደው ፡ ይዘምራሉ ፥

በእንቢልታ ፡ ድምፅ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

13 ፤ ዕድሜያቸውንም ፡ በተድላ ፡ ይፈጽማሉ ፤

ድንገትም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ይወርዳሉ ።

14 ፤ እግዚአብሔርንም ፦ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ራቅ ፤

መንገድኽን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ አንወድም ።

15 ፤ እናመልከውስ ፡ ዘንድ ፡ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ወይስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ብንጸልይ ፡ ምን ፡ ይጠቅመናል ፧ ይላሉ ።

16 ፤ እንሆ ፥ ሀብታቸው ፡ በእጃቸው ፡ ውስጥ ፡ አይደለምን ፧

የኃጥኣን ፡ ምክር ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ የራቀች ፡ ናት ።

17 ፤ የኃጥኣን ፡ መብራት ፡ የጠፋው ፥

መቅሠፍትም ፡ የመጣባቸው ፥

እግዚአብሔርም ፡ በቍጣው ፡ መከራ ፡ የከፈላቸው ፥

18 ፤ በነፋስ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ገለባ ፥

ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ እንደሚወስደው ፡ ትቢያ ፡ የኾኑ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፧

19 ፤ እናንተ ፦ እግዚአብሔር ፡ በደላቸውን ፡ ለልጆቻቸው ፡ ይጠብቃል ፡ ብላችኋል ።

እነርሱ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ፍዳን ፡ ለራሳቸው ፡ ይክፈል ።

20 ፤ ዐይኖቻቸው ፡ ጥፋታቸውን ፡ ይዩ ፥

ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ቍጣ ፡ ይጠጡ ።



www.ethiopianorthodox.org

21 ፤ የወራታቸውስ ፡ ቍጥር ፡ ቢቈረጥ ፥

ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ የቤታቸው ፡ ደስታ ፡ ምን ፡ ይኾናቸዋል ፧

22 ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ባሉትስ ፡ ላይ ፡ ለሚፈርድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

በእውኑ ፡ ሰው ፡ ዕውቀትን ፡ ያስተምራልን ፧

23 ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ በሰላም ፡ ተዘልሎ ፡ ሲቀመጥ ፡

በሙሉ ፡ ኀይሉ ፡ ሳለ ፡ ይሞታል ።

24 ፤ በአንገቱ ፡ ውስጥ ፡ ስብ ፡ሞልቷል ፥

የዐጥንቶቹም ፡ ቅልጥም ፡ ረጥቧል ።

25 ፤ ሌላውም ፡ ሰው ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ ሳይቀምስ ፡

በተመረረች ፡ ነፍስ ፡ ይሞታል ።

26 ፤ በዐፈር ፡ ውስጥ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ይተኛሉ ፥

ትልም ፡ ይከድናቸዋል ።

27 ፤ እንሆ ፥ ዐሳባችኹን ፥

የመከራችኹብኝንም ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ ዐውቄዋለኹ ።

28 ፤ እናንተ ፦ የከበርቴው ፡ ቤት ፡ የት ፡ ነው ፧

ኀጢአተኛውም ፡ ያደረበት ፡ ድንኳን ፡ የት ፡ ነው ፧ ብላችኋል ።

29 ፤ መንገድ ፡ ዐላፊዎችን ፡ አልጠየቃችኹምን ፧

ምልክታቸውን ፡ አታውቁምን ፧

30 ፤ ኀጢአተኛው ፡ በመቅሠፍት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፥

በቍጣው ፡ ቀን ፡ እንደሚድን ።

31 ፤ መንገዱን ፡ በፊቱ ፡ የሚናገር ፡ ማን ፡ ነው ፧

የሠራውንስ ፡ የሚመልስበት ፡ ማን ፡ ነው ፧

32 ፤ ርሱን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ይሸከሙታል ፥

ሰዎቹም ፡ በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ይጠብቃሉ ።

33 ፤ የሸለቆው ፡ ጓል ፡ ይጣፍጥለታል ፤

በኋላውም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ይሳባል ፥

በፊቱም ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ጉባኤ ፡ አለ ።

34 ፤ የምትመልሱልኝ ፡ ውስልትና ፡ ነውና ፥

በከንቱ ፡ እንዴት ፡ ታጽናኑኛላችኹ ፧

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ምዕራፍ ፡ 22 ።

1 ፤ ቴማናዊውም ፡ ኤልፋዝ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ በእውኑ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይጠቅመዋልን ፧



www.ethiopianorthodox.org

በእውነት ፡ ጥበበኛ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ይጠቅማል ።

3 ፤ ጻድቅ ፡ መኾንኽስ ፡ ኹሉን ፡ የሚችለውን ፡ አምላክ ፡ ደስ ፡ ያሠኘዋልን ፥

መንገድኽን ፡ ማቅናትኽስ ፡ ይጠቅመዋልን ፥

4 ፤ ርሱንስ ፡ ስለ ፡ ፈራኽ ፡ ይዘልፍኻልን ፥

ወደ ፡ ፍርድስ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይገባልን ፥

5 ፤ ክፋትኽስ ፡ የበዛ ፡ አይደለምን ፥

ለኀጢአትኽም ፡ ፍጻሜ ፡ የላትም ።

6 ፤ የወንድሞችኽን ፡ መያዣ ፡ በከንቱ ፡ ወስደኻል ፤

የዕርዝተኛዎቹንም ፡ ልብስ ፡ ዘርፈኻል ።

7 ፤ ለደካማ ፡ ውሃ ፡ አላጠጣኽም ፤

ለራብተኛም ፡ እንጀራን ፡ ከልክለኻል ።

8 ፤ በክንድ ፡ የበረታ ፡ ምድርን ፡ ገዛ ፤

ከበርቴውም ፡ ሰው ፡ ተቀመጠባት ።

9 ፤ መበለቲቱን ፡ አንዳች ፡ አልባ ፡ ሰደኻታል ፤

የድኻ ፡ አደጎችም ፡ ክንድ ፡ ተሰብሯል ።

10 ፤ ስለዚህ ፤ አሽክላ ፡ ከቦኻል ፤

ድንገተኛ ፡ ፍርሀትም ፡ አናውጦኻል ።

11 ፤ እንዳታይ ፡ ብርሃን ፡ ጨለማ ፡ ኾነችብኽ ፤

የውሃዎችም ፡ ብዛት ፡ አሰጠመኽ ።

12 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አይልምን ፥

ከዋክብትም ፡ እንዴት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እንዳሉ ፡ ተመልከት ።

13 ፤ አንተም ፦ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ያውቃል ፥

በድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ሊፈርድ ፡ ይችላልን ፥

14 ፤ እንዳያይ ፡ የጠቈረ ፡ ደመና ፡ ጋርዶታል ፤

በሰማይ ፡ ክበብ ፡ ላይ ፡ ይራመዳል ፡ ብለኻል ።

15 ፤ በእውኑ ፡ ኀጢአተኛዎች ፡ ሰዎች ፡ የረገጧትን ፡

የዱሮዪቱን ፡ መንገድ ፡ ትጠብቃለኽን ፥

16 ፤ ጊዜያቸው ፡ ሳይደርስ ፡ ተነጠቁ ፤

መሠረታቸውም ፡ እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ፈሰሰ ።

17 ፤ እግዚአብሔርንም ፦ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ራቅ ፤

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ምን ፡ ሊያደርግልን ፡ ይችላል ፥ አሉት ።

18 ፤ ነገር ፡ ግን ፤ ቤታቸውን ፡ በመልካም ፡ ነገር ፡ ሞላ ፤

የኃጥኣን ፡ ምክር ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ የራቀች ፡ ናት ።



www.ethiopianorthodox.org

19 ፤ ጻድቃን ፡ ያዩታል ፥ ደስም ፡ ይላቸዋል ፤

ንጹሓንም ፡ በንቀት ፡ ይሥቁባቸዋል ።

20 ፤ በእውነት ፡ ሀብታቸው ፡ ጠፋ ፥

የቀረውንም ፡ እሳት ፡ በላች ።

21 ፤ አኹንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተስማማ ፥ ሰላምም ፡ ይኑርኽ ፤

በዚያም ፡ በጎነት ፡ ታገኛለኽ ።

22 ፤ ከአፉም ፡ ሕጉን ፡ ተቀበል ፥

በልብኽም ፡ ቃሉን ፡ አኑር ፤

23 ፤ ኹሉን ፡ ወደሚችል ፡ አምላክ ፡ ብትመለስ ፥ ብትዋረድም ፥

ኀጢአትንም ፡ ከድንኳንኽ ፡ ብታርቅ ፥

24 ፤ የወርቅን ፡ ዕቃ ፡ በዐፈር ፡ ውስጥ ፥

የኦፊርንም ፡ ወርቅ ፡ በጅረት ፡ ድንጋይ ፡ መካከል ፡ ብትጥል ፥

25 ፤ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ወርቅና ፡ የሚብለጨለጭ ፡ ብር ፡ ይኾንልኻል ።

26 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኹሉን ፡ በሚችል ፡ አምላክ ፡ ደስ ፡ ይልኻል ፥

ፊትኽንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታነሣለኽ ።

27 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ትጸልያለኽ ፥ ርሱም ፡ ይሰማኻል ፤

ስእለትኽንም ፡ ትሰጣለኽ ።

28 ፤ ነገርንም ፡ ትመክራለኽ ፥ ርሱም ፡ ይሳካልኻል ፤

ብርሃንም ፡ በመንገድኽ ፡ ላይ ፡ ይበራል ።

29 ፤ ቢያዋርዱኽ ፡ አንተ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ትላለኽ ፤

ትሑቱንም ፡ ሰው ፡ ያድነዋል ።

30 ፤ ንጹሑን ፡ ሰው ፡ ያድነዋል ፤

በእጅኽም ፡ ንጽሕና ፡ ትድናለኽ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ምዕራፍ ፡ 23 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ ዛሬም ፡ ደግሞ ፡ የሐዘን ፡ እንጕርጕሮዬ ፡ ገና ፡ መራራ ፡ ነው ፤

እጁ ፡ በልቅሶ ፡ ጩኸቴ ፡ ላይ ፡ ከብዷለች ።

3 ፤ ርሱን ፡ ወዴት ፡ እንዳገኘው ፡ ምነው ፡ ባወቅኹ!

ወደተቀመጠበትስ ፡ ስፍራ ፡ ምነው ፡ በደረስኹ!

4 ፤ በፊቱ ፡ ሙግቴን ፡ አዘጋጅ ፡ ነበር ፥

አፌንም ፡ በማስረጃ ፡ እሞላው ፡ ነበር ።

5 ፤ የሚመልስልኝም ፡ ቃል ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቅ ፡ ነበር ፥



www.ethiopianorthodox.org

የሚለኝንም ፡ አስተውል ፡ ነበር ።

6 ፤ በኀይሉ ፡ ብዛት ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይሟገት ፡ ነበርን ፧

እንኳን! ያደምጠኝ ፡ ነበር ።

7 ፤ ቅን ፡ ሰው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በዚያ ፡ ይከራከር ፡ ነበር ፤

እኔም ፡ ከፈራጄ ፡ ለዘለዓለም ፡ አድን ፡ ነበር ።

8 ፤ እንሆ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ እኼዳለኹ ፥ ርሱም ፡ የለም ፤

ወደ ፡ ኋላም ፡ እኼዳለኹ ፥ እኔም ፡ አላስተውለውም ፤

9 ፤ ወደሚሠራበት ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ብኼድ ፡ አልመለከተውም ፤

በቀኙም ፡ ይሰወራል ፥ አላየውምም ፤

10 ፤ የምኼድበትን ፡ መንገድ ፡ ያውቃል ፤

ከፈተነኝም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ እወጣለኹ ።

11 ፤ እግሬ ፡ ወደ ፡ ርምጃው ፡ ተጣብቋል ፤

መንገዱንም ፡ ጠብቄያለኹ ፥ ፈቀቅም ፡ አላልኹም ።

12 ፤ ከከንፈሩ ፡ ትእዛዝ ፡ አልተመለስኹም ፤

የአፉን ፡ ቃል ፡ በልቤ ፡ ሰውሬያለኹ ።

13 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ብቻውን ፡ ነው ፤ ርሱንስ ፡ የሚመስለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ነፍሱም ፡ የወደደችውን ፡ ያደርጋል ።

14 ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ የተወሰነውን ፡ ይፈጽማል ፤

እንደዚህም ፡ ያለ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ አለ ።

15 ፤ ስለዚህ ፥ በፊቱ ፡ ደነገጥኹ ፤

ባሰብኹም ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ፈራኹ ።

16 ፤ እግዚአብሔር ፡ ልቤን ፡ አባብቶታልና ፥

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ አስደንግጦኛል ።

17 ፤ ከጨለማው ፡ የተነሣ ፥

ድቅድቁም ፡ ጨለማ ፡ ፊቴን ፡ ከመክደኑ ፡ የተነሣ ፡ አልደነገጥኹም ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ምዕራፍ ፡ 24 ።

1 ፤ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ዘንድ ፡ ዘመናት ፡ አልተሰወረምና ፡

ርሱን ፡ የሚያውቁ ፡ ለምን ፡ ወራቱን ፡ አያዩም ፧

2 ፤ የድንበሩን ፡ ምልክት ፡ የሚያፈርሱ ፡ አሉ ፤

መንጋዎቹን ፡ በዝብዘው ፡ ያሰማራሉ ።

3 ፤ የድኻ ፡ አደጎቹን ፡ አህያ ፡ ይነዳሉ ፤

የመበለቲቱን ፡ በሬ ፡ ስለ ፡ መያዣ ፡ ይወስዳሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

4 ፤ ድኻዎቹን ፡ ከመንገዱ ፡ ያወጣሉ ፤

የምድርም ፡ ችግረኛዎች ፡ ኹሉ ፡ ይሸሸጋሉ ።

5 ፤ እንሆ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳሉ ፡ እንደ ፡ ሜዳ ፡ አህያዎች ፥

መብልን ፡ ፈልገው ፡ ወደ ፡ ሥራቸው ፡ ይወጣሉ ፤

ምድረ ፡ በዳውም ፡ ለልጆቻቸው ፡ መብልን ፡ ይሰጣቸዋል ።

6 ፤ እነዚያ ፡ በዕርሻ ፡ ውስጥ ፡ እኽላቸውን ፡ ያጭዳሉ ፤

የበደለኛውንም ፡ ወይን ፡ ይቃርማሉ ።

7 ፤ ዕራቍታቸውን ፡ ያለልብስ ፡ ያድራሉ ፥

በብርድ ፡ ጊዜ ፡ መጐናጸፊያ ፡ የላቸውም ።

8 ፤ ከተራራዎች ፡ በሚወርድ ፡ ዝናብ ፡ ይረጥባሉ ፤

መጠጊያም ፡ ዐጥተው ፡ ቋጥኙን ፡ ያቅፋሉ ።

9 ፤ ድኻ ፡ አደጉን ፡ ልጅ ፡ ከጡቱ ፡ የሚነጥሉ ፡ አሉ ፡

ከችግረኛውም ፡ መያዣ ፡ ይወስዳሉ ።

10 ፤ ያለ ፡ ልብስ ፡ ዕራቍታቸውን ፡ ይኼዳሉ ፤

ተርበውም ፡ ነዶዎችን ፡ ይሸከማሉ ፤

11 ፤ በእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ዐጥር ፡ ውስጥ ፡ ዘይት ፡ ያደርጋሉ ፤

ወይንም ፡ ይጠምቃሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ይጠማሉ ።

12 ፤ ከከተማውና ፡ ከገዛ ፡ ቤቶቻቸው ፡ ይባረራሉ ፤

የልጆችም ፡ ነፍስ ፡ ለርዳታ ፡ ትጮኻለች ፤

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ስንፍናቸውን ፡ አይመለከትም ።

13 ፤ እነዚህ ፡ በብርሃን ፡ ላይ ፡ የሚያምፁ ፡ ናቸው ፤

መንገዱን ፡ አያውቁም ፥ በጐዳናውም ፡ አይጸኑም ።

14 ፤ ነፍሰ ፡ ገዳዩም ፡ ሳይነጋ ፡ ማልዶ ፡ ይነሣል ፤

ችግረኛዎችንና ፡ ድኻዎችን ፡ ይገድላል ፤

በሌሊትም ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ ነው ።

15 ፤ የአመንዝራም ፡ ዐይን ፡ ድግዝግዝታን ፡ ይጠብቃል ።

የማንም ፡ ዐይን ፡ አያየኝም ፡ ይላል ፥

ፊቱንም ፡ ይሸፍናል ።

16 ፤ ቤቶቹን ፡ በጨለማ ፡ ይነድላሉ ፤

በቀን ፡ ይሸሸጋሉ ፤

ብርሃንም ፡ አያውቁም ።

17 ፤ የጧት ፡ ብርሃን ፡ ለእነርሱ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሞት ፡ ጥላ ፡ ነው ፤

የሞትን ፡ ጥላ ፡ ድንጋጤ ፡ ያውቃሉና ።



www.ethiopianorthodox.org

18 ፤ እነርሱ ፡ በውሃ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ በረው ፡ ያልፋሉ ፤

ዕድል ፡ ፈንታቸውም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የተረገመች ፡ ናት ፤

ወደ ፡ ወይኑ ፡ ቦታ ፡ መንገድ ፡ አይዞሩም ።

19 ፤ ድርቅና ፡ ሙቀት ፡ የዐመዳዩን ፡ ውሃ ፡ ያጠፋሉ ፤

እንዲሁ ፡ ሲኦል ፡ በደለኛዎችን ፡ ታጠፋለች ።

20 ፤ ማሕፀን ፡ ትረሳዋለች ፤

ትልም ፡ በደስታ ፡ ይጠባዋል ፤

ዳግመኛም ፡ አይታሰብም ፤

ክፋትም ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ይሰበራል ።

21 ፤ የማትወልደውን ፡ መካኒቱን ፡ ይበድላታል ፤

ለመበለቲቱም ፡ በጎነት ፡ አያደርግም ።

22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኀይሉ ፡ ኀያላንን ፡ ይስባል ፤

ርሱም ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ አይታመንም ።

23 ፤ እግዚአብሔር ፡ በደኅና ፡ አኑሯቸዋል ፥

በዚያም ፡ ይታመናሉ ፤

ዐይኖቹ ፡ ግን ፡ በመንገዳቸው ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

24 ፤ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላሉ ፤

ይኼዳሉ ፥ ይጠወልጋሉም ፤

እንደ ፡ ሌላዎች ፡ ኹሉ ፡ ይከማቻሉ ፤

እንደ ፡ እሸትም ፡ ራስ ፡ ይቈረጣሉ ።

25 ፤ እንዲህስ ፡ ባይኾን ፡ ሐሰተኛ ፡ የሚያደርገኝ ፥

ነገሬንስ ፡ እንደ ፡ ምናምን ፡ የሚያደርገው ፡ ማን ፡ ነው ፨

## ____________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 25 ።

1 ፤ ሹሐዊውም ፡ በልዳዶስ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ ገዢነትና ፡ መፈራት ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ናቸው ፤

በከፍታውም ፡ ሰላም ፡ አድራጊ ፡ ነው ።

3 ፤ በእውኑ ፡ ለሰራዊቶቹ ፡ ቍጥር ፡ አላቸውን ፨

ብርሃኑስ ፡ የማይወጣው ፡ በማን ፡ ላይ ፡ ነው ፨

4 ፤ ሰውስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጻድቅ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥

ከሴትስ ፡ የተወለደ ፡ ንጹሕ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፨

5 ፤ እንሆ ፥ ጨረቃ ፡ እንኳ ፡ ብሩህ ፡ አይደለም ፥

ከዋክብትም ፡ በፊቱ ፡ ንጹሓን ፡ አይደሉም ።



www.ethiopianorthodox.org

6 ፤ ይልቁንስ ፡ ብስብስ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፥
ትልም ፡ የኾነ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምንኛ ፡ ያንስ!

______________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 26 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦
2 ፤ ኀይል ፡ የሌለውን ፡ ምንኛ ፡ ረዳኸው!
ብርታት ፡ የሌለውን ፡ ክንድ ፡ ምንኛ ፡ አዳንኸው!
3 ፤ ጥበብስ ፡ የሌለውን ፡ ምንኛ ፡ መከርኸው!
ብዙ ፡ ዕውቀትንስ ፡ ምንኛ ፡ ገለጥኸለት!
4 ፤ ይህንስ ፡ ቃል ፡ በማን ፡ ርዳታ ፡ ተናገርኸ ፧
የማንስ ፡ መንፈስ ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፧
5 ፤ ሙታን ፡ ሰዎች ፡ ከውሃዎች ፡ በታች ፥
በውሃዎችም ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩ ፡ በታች ፡ ይንቀጠቀጣሉ ።
6 ፤ ሲኦል ፡ በፊቱ ፡ ዕራቍቷን ፡ ናት ፥
ለጥፋትም ፡ መጋረጃ ፡ የለውም ።
7 ፤ ሰሜንን ፡ በባዶ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ይዘረጋል ፥
ምድሪቱንም ፡ በታቿ ፡ አንዳች ፡ አልባ ፡ ያንጠለጥላል ።
8 ፤ ውሃዎችን ፡ በደመናዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ያስራል ፥
ደመናዪቱም ፡ ከታች ፡ አልተቀደደችም ።
9 ፤ የዙፋኑን ፡ ፊት ፡ ይከድናል ፥
ደመናውንም ፡ ይዘረጋበታል ።
10 ፤ ብርሃንና ፡ ጨለማ ፡ እስከሚለያዩበት ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፥
በውሃዎች ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ድንበርን ፡ አደረገ ።
11 ፤ የሰማይ ፡ አዕማድ ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፥
ከተግሣጹም ፡ የተነሣ ፡ ይደነግጣሉ ።
12 ፤ በኀይሉ ፡ ባሕርን ፡ ጸጥ ፡ ያደርጋል ፥
በማስተዋሉም ፡ ረዓብን ፡ ይመታል ።
13 ፤ በመንፈሱ ፡ ሰማያት ፡ ውበትን ፡ አገኙ ፥
እጁም ፡ በራሪዪቱን ፡ እባብ ፡ ወጋች ።
14 ፤ እንሆ ፥ ይህ ፡ የመንገዱ ፡ ዳርቻ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
ይህም ፡ የሰማነው ፡ ነገር ፡ ምንኛ ፡ ጥቂት ፡ ነው!
የኀይሉንስ ፡ ነጐድጓድ ፡ ያስተውል ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ ይችላል ፧

______________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ። ____________________



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 27 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ ምሳሌውን ፡ ይመስል ፡ ዘንድ ፡ ደገመ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ ፍርዴን ፡ ያስወገደ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን!

ነፍሴንም ፡ መራራ ፡ ያደረገ ፡ ሁሉን ፡ የሚችል ፡ ሕያው ፡ አምላክን!

3 ፤ እስትንፋሴ ፡ በእኔ ፡ ውስጥ ፥

የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ ባፍንጫዬ ፡ ውስጥ ፡ ገና ፡ ሳለ ፥

4 ፤ ከንፈሬ ፡ ኀጢአትን ፡ አትናገርም ፥

አንደበቴም ፡ ሽንገላን ፡ አያወጣም ።

5 ፤ እናንተን ፡ ማጽደቅ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ይራቅ ፤

እስክሞት ፡ ድረስ ፡ ፍጹምነቴን ፡ ከእኔ ፡ አላርቅም ።

6 ፤ ጽድቄን ፡ እይዛለኹ ፡ ርሱንም ፡ አልተውም ፤

ከቀኖቼም ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ አንዱ ፡ ልቤ ፡ አይዘልፈኝም ።

7 ፤ ጠላቴ ፡ እንደ ፡ በደለኛ ፥

በእኔ ፡ ላይም ፡ የሚነሣ ፡ እንደ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ይኹን ።

8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ባጠፋውና ፡ ነፍሱን ፡ በለየ ፡ ጊዜ ፥

የዝንጉ ፡ ሰው ፡ ተስፋው ፡ ምንድር ፡ ነው ፨

9 ፤ በእውኑ ፡ መከራ ፡ በመጣበት ፡ ጊዜ ፥

እግዚአብሔር ፡ ጩኸቱን ፡ ይሰማልን ፨

10 ፤ ሁሉንስ ፡ በሚችል ፡ አምላክ ፡ ደስ ፡ ይለዋልን ፨

እግዚአብሔርንስ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይጠራልን ፨

11 ፤ እኔ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ አስተምራችኋለኹ ፤

ሁሉን ፡ በሚችል ፡ አምላክ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ አልሸሽግም ።

12 ፤ እንሆ ፥ ሁላችኹ ፡ አይታችኋል ፤

ስለ ፡ ምን ፡ ከንቱ ፡ ኾናችኹ ፨

13 ፤ ይህች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የበደለኛ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፥

ግፈኛም ፡ ሁሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ዘንድ ፡ የሚቀበላት ፡ ርስት ፡ ናት ፤

14 ፤ ልጆቹ ፡ ቢበዙ ፡ ለሰይፍ ፡ ይኾናሉ ፤

ዘሩም ፡ እንጀራን ፡ አይጠግብም ።

15 ፤ ለርሱም ፡ የቀሩት ፡ በቸነፈር ፡ ይቀበራሉ ፤

መበለቶቻቸውም ፡ አያለቅሱም ።

16 ፤ ርሱ ፡ ብርን ፡ እንደ ፡ ዐፈር ፡ ቢከምር ፥

ልብስንም ፡ እንደ ፡ ጭቃ ፡ ቢያዘጋጅ ፥

17 ፤ ርሱ ፡ ያዘጋጀው ፡ ይኾናል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ጻድቅ ፡ ይለብሰዋል ፤



www.ethiopianorthodox.org

ብሩንም ፡ ንጹሓን ፡ ይከፋፈሉታል ።

18 ፤ የሚሠራው ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ድር ፡ ይሠራል ፥

ጠባቂም ፡ እንደሚሠራው ፡ ጐጆ ፡ ነው ።

19 ፤ ባለጠጋ ፡ ኾኖ ፡ ይተኛል ፥ ዳግመኛም ፡ አይተኛም ፤

ዐይኑን ፡ ይከፍታል ፥ ርሱም ፡ የለም ።

20 ፤ ድንጋጤ ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ታገኘዋለች ፤

በሌሊትም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ትነጥቀዋለች ።

21 ፤ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ ያነሣዋል ፥ ርሱም ፡ ይኼዳል ፤

ከቦታውም ፡ ይጠርገዋል ።

22 ፤ ርሱ ፡ ይጥልበታል ፥ አይራራለትም ፤

ከእጁ ፡ ፈጥኖ ፡ መሸሽ ፡ ይወዳል ።

23 ፤ ሰው ፡ በእጁ ፡ ያጨበጭብበታል ፤

ከስፍራውም ፡ በፉጨት ፡ ያስወጡታል ።

______________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 28 ።

1 ፤ በእውነት ፡ ብር ፡ የሚወጣበት ፥

ወርቅም ፡ የሚነጠርበት ፡ ስፍራ ፡ አለ ።

2 ፤ ብረት ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ ይወሰዳል ፤

መዳብም ፡ ከድንጋይ ፡ ይቀለጣል ።

3 ፤ ሰው ፡ ለጨለማ ፡ ፍጻሜን ፡ ያደርጋል ፤

የጨለማውንና ፡ የሞት ፡ ጥላን ፡ ድንጋይ ፡ እስከ ፡ ወሰኑ ፡ ድረስ ፡ ይፈላልጋል ።

4 ፤ ሰው ፡ ከሚኖርበት ፡ ርቀው ፡ መውረጃ ፡ ይቈፍራሉ ፤

ከሰውም ፡ እግር ፡ ተረሱ ፥

ከሰዎችም ፡ ርቀው ፡ እየተንጠለጠሉ ፡ ይወዛወዛሉ ።

5 ፤ እንጀራ ፡ ከምድር ፡ ውስጥ ፡ ይወጣል ፤

በእሳትም ፡ እንደሚኾን ፡ ታችኛው ፡ ይገለበጣል ።

6 ፤ ድንጋይዋ ፡ የሰንፔር ፡ ስፍራ ፡ ነው ፥

የወርቅም ፡ ድቃቂ ፡ አለው ።

7 ፤ መንገዷን ፡ ጭልፊት ፡ አያውቀውም ፥

የአሞራም ፡ ዐይን ፡ አላየውም ።

8 ፤ የትዕቢት ፡ ልጆች ፡ አልረገጧትም ፥

ደቦል ፡ አንበሳ ፡ አላለፈባትም ።

9 ፤ ሰው ፡ ወደ ፡ ቡላድ ፡ ድንጋይ ፡ እጁን ፡ ይዘረጋል ፥



www.ethiopianorthodox.org

ተራራውንም ፡ ከመሠረቱ ፡ ይገለብጣል ።

10 ፤ ከድንጋይ ፡ ውስጥ ፡ መንዶልዶያ ፡ ይወቅራል ፤

ዐይኑም ፡ ዕንቍን ፡ ኹሉ ፡ ታያለች ።

11 ፤ ፈሳሹም ፡ እንዳይንጠባጠብ ፡ ይገድባል ፤

የተሰወረውንም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ያወጣል ።

12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጥበብ ፡ የምትገኘው ፡ ወዴት ፡ ነው ፧

የማስተዋልስ ፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧

13 ፤ ሰው ፡ መንገዷን ፡ አያውቅም ፤

በሕያዋን ፡ ምድር ፡ አትገኝም ።

14 ፤ ቀላይ ፦ በእኔ ፡ ውስጥ ፡ የለችም ፡ ይላል ፤

ባሕርም ፦ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ የለችም ፡ ይላል ።

15 ፤ በምዝምዝ ፡ ወርቅ ፡ አትገኝም ፥

ብርም ፡ ስለ ፡ ዋጋዋ ፡ አይመዘንም ።

16 ፤ በኦፊር ፡ ወርቅ ፥

በከበረም ፡ መረግድና ፡ በሰንፔር ፡ አትገመትም ።

17 ፤ ወርቅና ፡ ብርጭቆ ፡ አይወዳደሯትም ፥

በጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ዕቃ ፡ አትለወጥም ።

18 ፤ ስለ ፡ ዛጐልና ፡ ስለ ፡ አልማዝ ፡ አይነገርም ።

የጥበብ ፡ ዋጋ ፡ ከቀይ ፡ ዕንቍ ፡ ይልቅ ፡ ይበልጣል ።

19 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ቶጳዝዮን ፡ አይተካከላትም ፥

በጥሩም ፡ ወርቅ ፡ አትገመትም ።

20 ፤ እንግዲያሳ ፡ ጥበብ ፡ ከወዴት ፡ ትመጣለች ፧

የማስተዋልስ ፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧

21 ፤ ከሕያዋን ፡ ኹሉ ፡ ዐይን ፡ ተሰውራለች ፥

ከሰማይ ፡ ወፎች ፡ ተሸሽጋለች ።

22 ፤ ጥፋትና ፡ ሞት ፦ ወሬዋን ፡ በጕሮዎቻችን ፡ ሰማን ፡ ብለዋል ።

23 ፤ እግዚአብሔር ፡ መንገዷን ፡ ያስተውላል ፥

ርሱም ፡ ስፍራዋን ፡ ያውቃል ።

24 ፤ ርሱም ፡ የምድርን ፡ ዳርቻ ፡ ይመለከታል ፥

ከሰማይም ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ያያል ።

25 ፤ ለነፋስ ፡ሚዛንን ፡ ባደረገለት ፡ ጊዜ ፥

ውሃዎችንም ፡ በስፍር ፡ በሰፈረ ፡ ጊዜ ፥

26 ፤ ለዝናብም ፡ሥርዐትን ፥



www.ethiopianorthodox.org

ለነጐድጓድ ፡ መብረቅም ፡ መንገድን ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፥

27 ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አያት ፥ ገለጣትም ፤

አዘጋጃትም ፥ ደግሞም ፡ መረመራት ።

28 ፤ ሰውንም ፦ እንሆ ፥ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ጥበብ ፡ ነው ፤

ከነጢአትም ፡ መራቅ ፡ ማስተዋል ፡ ነው ፡ አለው ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ምዕራፍ ፡ 29 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ ምሳሌውን ፡ ይመስል ፡ ዘንድ ፡ ደገመ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቀኝ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ጊዜ ፥

እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ወራት ፡ ምነው ፡ በኾንኹ!

3 ፤ በራሴ ፡ ላይ ፡ መብራቱ ፡ በበራ ፡ ጊዜ ፥

እኔም ፡ ጨለማውን ፡ ዐልፌ ፡ በብርሃኑ ፡ በኼድኹ ፡ ጊዜ ፥

4 ፤ በሙሉ ፡ ሰውነቴ ፡ እንደ ፡ ነበርኹ ፡ ጊዜ ፥

እግዚአብሔር ፡ ድንኳኔን ፡ በጋረደ ፡ ጊዜ ፥

5 ፤ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ገና ፡ ሳለ ፥

ልጆቼም ፡ በዙሪያዬ ፡ ሳሉ ፥

6 ፤ መንገዴ ፡ በቅቤ ፡ ይታጠብ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፥

ድንጋዩ ፡ የዘይት ፡ ፈሳሽ ፡ ያፈስልኝ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ።

7 ፤ ወደከተማዪቱ ፡ በር ፡ በወጣኹ ፡ ጊዜ ፥

በአደባባዩም ፡ ወንበሬን ፡ ባኖርኹ ፡ ጊዜ ፥

8 ፤ ጐበዛዝት ፡ እኔን ፡ አይተው ፡ ተሸሸጉ ፥

ሽማግሌዎችም ፡ ተነሥተው ፡ ቆሙ ።

9 ፤ አለቃዎቹ ፡ ከመናገር ፡ ዝም ፡ አሉ ፥

እጃቸውንም ፡ በአፋቸው ፡ ላይ ፡ ጫኑ ።

10 ፤ የታላላቆቹም ፡ ድምፅ ፡ አረመመ ፤

ምላሳቸውም ፡ በትናጋቸው ፡ ተጣጋ ።

11 ፤ የሰማችኝ ፡ ዦሮ ፡ አሞገሰችኝ ፥

ያየችኝም ፡ ዐይን ፡ መሰከረችልኝ ፤

12 ፤ የሚጮኸውን ፡ ችግረኛ ፥

ድኻ ፡ አደጉንና ፡ ረጂ ፡ የሌለውን ፡ አድኜ ፡ ነበርና ።

13 ፤ ለጥፋት ፡ የቀረበው ፡ በረከት ፡ በላዬ ፡ መጣ ፤

የባልቴቲቱንም ፡ ልብ ፡ እልል ፡ አሠኘኹ ።

14 ፤ ጽድቅን ፡ ለበስኹ ፡ ርሷም ፡ ለበሰችኝ ፤



www.ethiopianorthodox.org

ፍርዴም ፡ እንደ ፡ መጐናጸፊያና ፡ እንደ ፡ ኵፋር ፡ ነበረ ።

15 ፤ ለዕውር ፡ ዐይን ፥

ለዐንካሳ ፡ እግር ፡ ነበርኹ ።

16 ፤ ለድኻው ፡ አባት ፡ ነበርኹ ፤

የማላውቀውንም ፡ ሰው ፡ ሙግት ፡ መረመርኹ ።

17 ፤ የኀጢአተኛውን ፡ መንጋጋ ፡ ሰበርኹ ፥

የነጠቀውንም ፡ ከጥርሱ ፡ ውስጥ ፡ አስጣልኹ ።

18 ፤ እኔም ፡ አልኹ ፦ በልጆቼ ፡ መካከል ፡ እሞታለኹ ፥

ዕድሜዬንም ፡ እንደ ፡ አሸዋ ፡ አበዛለኹ ፤

19 ፤ ሥሬ ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ተዘርግቷል ፥

ጠልም ፡ በቅርንጫፌ ፡ ላይ ፡ ያድራል ፤

20 ፤ ክብሬ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ታድሷል ፥

ቀስቴም ፡ በእጄ ፡ ውስጥ ፡ ለምልሟል ።

21 ፤ ሰዎች ፡ እኔን ፡ ሰምተው ፡ በትዕግሥት ፡ ተጠባበቁ ፥

ምክሬንም ፡ ለማዳመጥ ፡ ዝም ፡ አሉ ።

22 ፤ ከቃሌ ፡ በኋላ ፡ አንዳች ፡ አልመለሱም ፤

ንግግሬም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተንጠባጠበ ።

23 ፤ ዝናብን ፡ እንደሚጠብቁ ፡ በትዕግሥት ፡ ጠበቁኝ ፤

የጥቢን ፡ ዝናብ ፡ እንደሚሹ ፡ አፋቸውን ፡ ከፈቱ ።

24 ፤ እነርሱ ፡ ባልታመኑ ፡ ጊዜ ፡ ሣቅኹላቸው ፤

የፊቴንም ፡ ብርሃን ፡ አላወረዱም ።

25 ፤ መንገዳቸውን ፡ መረጥኹ ፤

እንደ ፡ አለቃ ፡ ኾኜ ፡ ተቀመጥኹ ፤

ንጉሥ ፡ በሰራዊቱ ፡ መካከል ፡ እንደሚኖር ፥

ሐዘነተኛዎችን ፡ እንደሚያጽናና ፡ኖርኹ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ።

ምዕራፍ ፡ 30 ።

1 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በዕድሜ ፡ ከእኔ ፡ የሚያንሱ ፥

አባቶቻቸውን ፡ ከመንጋዬ ፡ ውሻዎች ፡ ጋራ ፡ ለማኖር ፡ የናቅኺቸው ፥

በእኔ ፡ ላይ ፡ ተሣለቁብኝ ።

2 ፤ ሙሉ ፡ ሰው ፡ መኾናቸው ፡ ጠፍቶባቸው ፡ ነበርና ፥

የእጃቸው ፡ ብርታት ፡ ለእኔ ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ፨

3 ፤ በራብና ፡ በቀጠና ፡ የመነመኑ ፡ ናቸው ፤



www.ethiopianorthodox.org

የመፍረስና ፡ የመፈታት ፡ ጨለማ ፡ ወዳለበት ፡

ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይሸሻሉ ።

4 ፤ በቍጥቋጦ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡

ጨው ፡ ጨው ፡ የሚለውን ፡ አትክልት ፡ ይለቅማሉ ፤

የክትክታ ፡ ሥር ፡ ደግሞ ፡ መብላቸው ፡ ነው ።

5 ፤ ከሰዎች ፡ ተለይተው ፡ ተሰደዱ ፤

በሌባ ፡ ላይ ፡ እንደሚጮኽ ፡ ይጮኹባቸዋል ።

6 ፤ በሸለቆ ፡ ፈረፈርና ፡ በምድር ፡ ጕድጓድ ፡

በድንጋይም ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ ።

7 ፤ በቍጥቋጦ ፡ መካከል ፡ ይጮኻሉ ፤

ከሳማ ፡ በታች ፡ ተሰብስበዋል ።

8 ፤ የሰነፎችና ፡ የነውረኞዎች ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፤

ከምድርም ፡ በግርፋት ፡ የተባረሩ ፡ ናቸው ።

9 ፤ አኹንም ፡ እኔ ፡ መዝፈኛና ፡ መተረቻ ፡ ኾንኋቸው ።

10 ፤ ተጸየፉኝ ፥ ከእኔም ፡ ራቁ ፤

አክታቸውንም ፡ በፊቴ ፡ መትፋትን ፡ አልተዉም ።

11 ፤ የቀስቴን ፡ አውታር ፡ አላልቶብኛል ፥ አዋርዶኝማል ፤

እነርሱም ፡ በፊቴ ፡ ልጓማቸውን ፡ ፈትዋል ።

12 ፤ በቀኜ ፡ በኩል ፡ ዱርዬዎች ፡ ተነሥተዋል ፥

እግሬንም ፡ ይገለብጣሉ ፤

የጥፋታቸውን ፡ መንገድ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ይጐድባሉ ።

13 ፤ ጐዳናዬን ፡ ያበላሻሉ ፤

ረዳት ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ መከራዬን ፡ ያበዛሉ ።

14 ፤ በሰፊ ፡ ፍራሽ ፡ እንደሚመጡ ፡ ይመጡብኛል ፤

በባድማ ፡ ውስጥ ፡ ይንከባለሉብኛል ።

15 ፤ ድንጋጤ ፡ በላዬ ፡ ተመለሰችብኝ ፥

ክብሬንም ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ያሳድዷታል ፤

ደኅንነቴም ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ ዐልፋለች ።

16 ፤ አኹንም ፡ ነፍሴ ፡ በውስጤ ፡ ፈሰሰች ፤

የመከራም ፡ ዘመን ፡ ያዘችኝ ።

17 ፤ በሌሊት ፡ ዐጥንቴ ፡ በደዌ ፡ ተነደለች ፥

ኸርማቶቼም ፡ አያርፉም ።

18 ፤ ከታላቁ ፡ ደዌ ፡ ኀይል ፡ የተነሣ ፡ ልብሴ ፡ ተበላሸች ፤



www.ethiopianorthodox.org

እንደ ፡ ቀሚስ ፡ ክሳድ ፡ ዐነቀችኝ ።

19 ፤ ርሱ ፡ በጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ጣለኝ ፥

ዐፈርና ፡ ዐመድም ፡ መሰልኹ ።

20 ፤ ወዳንተ ፡ ጮኽኹ ፥ አልመለስኽልኝም ፤

ተነሣኹ ፥ አልተመለከትኽኝም ።

21 ፤ ተመልሰኽ ፡ ጨካኝ ፡ ኾንኽብኝ ፤

በእጅኽም ፡ ብረታት ፡ አስጨነቅኽኝ ።

22 ፤ በነፋስ ፡ አነሣኽኝ ፥ በላዩም ፡ አስቀመጥኽኝ ፤

በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ አቀለጥኽኝ ።

23 ፤ ለሞት ፡ ሕያዋንም ፡ ኹሉ ፡ ለሚሰበሰቡበት ፡ ቤት ፡ አሳልፈኽ ፡ እንደምትሰጠኝ ፡ ዐውቄያለኹና ።

24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰው ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ እጁን ፡ አይዘረጋምን ፧

በጥፋቱስ ፡ ጊዜ ፡ አይጮኽምን ፧

25 ፤ ጭንቅ ፡ ቀን ፡ ላገኘው ፡ ሰው ፡ አላለቀስኹምን ፧

ለችግረኛስ ፡ ነፍሴ ፡ አላዘነችምን ፧

26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጎነትን ፡ በተጠባበቅኹ ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ መጣችብኝ ፤

ብርሃንን ፡ በትዕግሥት ፡ ጠበቅኹ ፥ ጨለማም ፡ መጣ ።

27 ፤ አንዠቴ ፡ ፈላች ፥ አላረፈችም ፤

የመከራም ፡ ዘመን ፡ መጣችብኝ ።

28 ፤ ያለፀሓይ ፡ በትካዜ ፡ ኼድኹ ፤

በጉባኤም ፡ መካከል ፡ ቆሜ ፡ ጮኽኹ ።

29 ፤ ለቀበሮ ፡ ወንድም ፥

ለሰጐንም ፡ ባልንጀራ ፡ ኾንኹ ።

30 ፤ ቍርበቴ ፡ ጠቈረ ፥ ከእኔም ፡ ተለይቶ ፡ ርግፍግፍ ፡ አለ ፤

ዐጥንቴም ፡ ከትኵሳት ፡ የተነሣ ፡ ተቃጠለች ።

31 ፤ ስለዚህ ፥ መሰንቆዬ ፡ ለሐዘን ፥

እንቢልታዬም ፡ ለሚያለቅሱ ፡ ቃል ፡ ኾነ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ምዕራፍ ፡ 31 ።

1 ፤ ከዐይኔ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባኹ ፤

እንግዲህስ ፡ ቈንዦዪቱን ፡ እንዴት ፡ እመለከታለኹ ፧

2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ከላይ ፥

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ርስት ፡ ከአርያም ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

3 ፤ መዓትስ ፡ ለኀጢአተኛ ፥



www.ethiopianorthodox.org

መለየትስ ፡ ለሚበድሉ ፡ አይደለችምን ፨

4 ፤ መንገዴን ፡ አያይምን ፨

ርምጃዬንስ ፡ ኹሉ ፡ አይቈጥርምን ፨

5 ፤ 6 ፤ በእውነተኛ ፡ ሚዛን ፡ ልመዘን ፥

እግዚአብሔርም ፡ ቅንነቴን ፡ ይወቅ ።

በሐሰት ፡ ኼጄ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡

እግሬም ፡ ለሽንገላ ፡ ቸኵላ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

7 ፤ ርምጃዬ ፡ ከመንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፥

ልቤም ፡ ዐይኔን ፡ ተከትሎ ፥

ነውርም ፡ ከእጄ ፡ ጋራ ፡ ተጣብቆ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

8 ፤ እኔ ፡ ልዝራ ፥ ሌላ ፡ ሰውም ፡ ይብላው ፤

የሚበቅለውም ፡ ኹሉ ፡ ይነቀል ።

9 ፤ ልቤ ፡ ወደ ፡ ሌላዪቱ ፡ ሴት ፡ ጐምዥቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

በባልንጀራዬም ፡ ደጅ ፡ አድብቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

10 ፤ ሚስቴ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ትፍጭ ፥

ሌላዎችም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ይጐንበሱ ።

11 ፤ ይህ ፡ ክፉ ፡ አበሳ ፥

ፈራጆችም ፡ የሚቀጡበት ፡ በደል ፡ ነውና ፤

12 ፤ ይህ ፡ እስከ ፡ ጥፋት ፡ ድረስ ፡ የሚበላ ፡ እሳት ፥

ቡቃያዬንም ፡ ኹሉ ፡ የሚነቅል ፡ ነውና ።

13 ፤ ወንድ ፡ ባሪያዬ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ባሪያዬ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ በተሟገቱ ፡ ጊዜ ፥

ሙግታቸውን ፡ ንቄ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

14 ፤ እግዚአብሔር ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አደርጋለኹ ፨

በጐበኘኝ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ እመልስለታለኹ ፨

15 ፤ እኔን ፡ በማሕፀን ፡ የፈጠረ ፡ ርሱንስ ፡ የፈጠረው ፡ አይደለምን ፨

በማሕፀንስ ፡ ውስጥ ፡ የሠራን ፡ አንድ ፡ አይደለንምን ፨

16 ፤ ድኻውን ፡ ከልመናው ፡ ከልክዬ ፥

የመበለቲቱን ፡ ዐይን ፡ አጨልሜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

17 ፤ እንጀራዬን ፡ ለብቻዬ ፡ በልቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ድኻ ፡ አደጉም ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ሳይበላ ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

18 ፤ ርሱን ፡ ግን ፡ ከታናሽነቴ ፡ ዠምሬ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አሳድጌው ፡ ነበር ፥

ርሷንም ፡ ከእናቴ ፡ ማሕፀን ፡ ዠምሬ ፡ መራኋት ፤

19 ፤ ዕራቍቱን ፡ የኾነው ፡ ሰው ፡ ሲጠፋ ፥



www.ethiopianorthodox.org

ወይም ፡ ድኻ ፡ ያለልብስ ፡ ሲኾን ፡ አይቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

20 ፤ ጐንና ፡ ጐኑ ፡ ያልባረከችኝ ፥

በበጎቼም ፡ ጠጕር ፡ ያልሞቀ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

21 ፤ በበሩ ፡ ረዳት ፡ ስላየኹ ፥

በድኻ ፡ አደግ ፡ ላይ ፡ እጄን ፡ አንሥቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

22 ፤ ትከሻዬ ፡ ከመሠረቷ ፡ ትውደቅ ፥

ክንዴም ፡ ከመገናኛዋ ፡ ትሰበር ።

23 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መዓት ፡ አስደንግጦኛልና ፤

በክብሩም ፡ ፊት ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ አልቻልኹም ።

24 ፤ ወርቅን ፡ ተስፋ ፡ አድርጌ ፥

ጥሩውንም ፡ ወርቅ ፦ ባንተ ፡ እታመናለኹ ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

25 ፤ ሀብቴ ፡ ስለ ፡ በዛ ፥

እጄም ፡ ብዙ ፡ ስላገኘች ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

26 ፤ ፀሓይ ፡ ሲበራ ፡

ጨረቃ ፡ በክብር ፡ ስትኼድ ፡ አይቼ ፥

27 ፤ ልቤ ፡ በስውር ፡ ተታሎ ፥

አፌም ፡ እጄን ፡ ስሞ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

28 ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ በካድኹ ፡ ነበርና ፥

ይህ ፡ ደግሞ ፡ ፈራጆች ፡ የሚቀጡበት ፡ በደል ፡ በኾነ ፡ ነበር ።

29 ፤ በሚጠላኝ ፡ መጥፋት ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡

ክፉ ፡ ነገርም ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ሐሤት ፡ አድርጌ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመርገም ፡ ነፍሱን ፡ በመሻት ፡

አንደበቴን ፡ ኀጢአት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ አልሰጠኹም ፤

31 ፤ በድንኳኔ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፦

በከብቱ ፡ ሥጋ ፡ ያልጠገበ ፡ ማን ፡ ይገኛል ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

32 ፤ መጻተኛው ፡ ግን ፡ በሜዳ ፡ አያድርም ፡ ነበር ፥

ደጄንም ፡ ለመንገደኛ ፡ እከፍት ፡ ነበር ፤

33 ፤ በደሌንም ፡ በብብቴ ፡ በመሸሸግ ፡

ኀጢአቴን ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሰውሬ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

34 ፤ ከሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ፈርቼ ፥

የዘመዶቼም ፡ ንቀት ፡ አስደንግጦኝ ፥

ዝም ፡ ብዬ ፡ ከደጅ ፡ ያልወጣኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

35 ፤ የሚያዳምጠኝ ፡ ምነው ፡ በኖረልኝ!



www.ethiopianorthodox.org

እንሆ ፥ የእጄ ፡ ምልክት ፡

ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ይመልስልኝ ፤

ከባላጋራዬ ፡ የተጻፈው ፡ የክስ ፡ ጽሑፍ ፡ ምነው ፡ በተገኘልኝ!

36 ፤ በትከሻዬ ፡ ላይ ፡ እሸከመው ፥

አክሊልም ፡ አድርጌ ፡ በራሴ ፡ አስረው ፡ ነበር ፤

37 ፤ የርምጃዬን ፡ ቍጥር ፡ አስታውቀው ፥

እንደ ፡ አለቃም ፡ ኾኜ ፡ አቀርብለት ፡ ነበር ።

38 ፤ ዕርሻዬ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ጮኻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ትልሞቿም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ አልቅሰው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

39 ፤ ፍሬዋን ፡ ያለዋጋ ፡ በልቼ ፥

የባለቤቶችንም ፡ ነፍስ ፡ አሳዝኜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

40 ፤ በስንዴ ፡ ፋንታ ፡ አሜከላ ፥

በገብስም ፡ ፋንታ ፡ ኵርንችት ፡ ይውጣብኝ ። የኢዮብ ፡ ቃል ፡ ተፈጸመ ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ።

ምዕራፍ ፡ 32 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ ራሱን ፡ ጻድቅ ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፥ እነዚያ ፡ ሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ መመለስን ፡ ተዉ ።

2 ፤ ከራም ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ የቡዛዊው ፡ የባርክኤል ፡ ልጅ ፡ የኤሊሁ ፡ ቍጣ ፡ ነደደ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ይልቅ ፡ ራሱን ፡
ጻድቅ ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፥ ኢዮብን ፡ ተቈጣው ።

3 ፤ ደግሞም ፡ በኢዮብ ፡ ፈረዱበት ፡ እንጂ ፡ የሚገባ ፡ መልስ ፡ ስላላገኙ ፥ በሦስቱ ፡ ባልንጀራዎቹ ፡ ላይ ፡ ተቈጣ ።

4 ፤ ኤሊሁ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ሽማግሌዎች ፡ ነበሩና ፥ ከኢዮብ ፡ ጋራ ፡ መናገርን ፡ ጠብቆ ፡ ነበር ።

5 ፤ ኤሊሁም ፡ በነዚህ ፡ በሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ አፍ ፡ መልስ ፡ እንደሌለ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ቍጣው ፡ ነደደ ።

6 ፤ የቡዛዊውም ፡ የባርክኤል ፡ ልጅ ፡ ኤሊሁ ፡ ተናገረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

እኔ ፡ በዕድሜ ፡ ታናሽ ፡ ነኝ ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ናችኹ ፤

ስለዚህም ፡ ሠጋኹ ፤ ዕውቀቴን ፡ እገልጥላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ፈራኹ ።

7 ፤ እንደዚህም ፡ አልኹ ፦ ዓመታት ፡ በተናገሩ ፡ ነበር ፥

የዓመታትም ፡ ብዛት ፡ ጥበብን ፡ ባስተማረች ፡ ነበር ።

8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሰው ፡ ውስጥ ፡ መንፈስ ፡ አለ ፥

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ የአምላክ ፡ እስትንፋስ ፡ ማስተዋልን ፡ ይሰጣል ።

9 ፤ በዕድሜ ፡ ያረጁ ፡ ጠቢባን ፡ አይደሉም ፥

ሽማግሌዎችም ፡ ፍርድን ፡ አያስተውሉም ።

10 ፤ ስለዚህም ፦ ስሙኝ ፤

እኔ ፡ ደግሞ ፡ ዕውቀቴን ፡ እገልጥላችኋለኹ ፡ አልኹ ።

11 ፤ እንሆ ፥ ቃላችኹን ፡ በትዕግሥት ፡ ጠበቅኹ ፤



www.ethiopianorthodox.org

የምትናገሩትን ፡ ነገር ፡ እስክትመረምሩ ፡ ድረስ ፤

ብልኀታችኹን ፡ አዳመጥኹ ።

12 ፤ እንዲሁም ፡ ልብ ፡ አደረግኹ ፤

እንሆም ፥ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ኢዮብን ፡ ያስረዳ ፥

ወይም ፡ ለቃሉ ፡ የመለሰ ፡ የለም ።

13 ፤ እናንተም ፦ ጥበብን ፡ አግኝተናል ፤

እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ አያሸንፈውም ፡ እንዳትሉ ፡ ተጠንቀቁ ።

14 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ቃሉን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አልተናገረም ፤

እኔም ፡ በንግግራችኹ ፡ አልመልስለትም ።

15 ፤ እነርሱ ፡ ደነገጡ ፥ ዳግመኛም ፡ አልመለሱም ፤

የሚናገሩትንም ፡ ዐጡ ።

16 ፤ እነርሱ ፡ አልተናገሩምና ፥

ቆመው ፡ ዳግመኛ ፡ አልመለሱምና ፡ እኔ ፡ በትዕግሥት ፡ እጠብቃለኹን ፧

17 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ፈንታዬን ፡ እመልሳለኹ ፥

ዕውቀቴንም ፡ እገልጣለኹ ፤

18 ፤ እኔ ፡ ቃል ፡ ተሞልቻለኹና ፥

በውስጤም ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ አስገድዶኛልና ።

19 ፤ በተሓ ፡ ጠጅ ፡ እንደ ፡ ተሞላና ፡ ሊቀደድ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ አቍማዳ ፥

ሊፈነዳ ፡ እንደማይችል ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡

አቍማዳ ፥ እንሆ ፥ አንገቴ ፡ ኾነ ።

20 ፤ ጥቂት ፡ እንድተነፍስ ፡ እናገራለኹ ፤

ከንፈሬን ፡ ገልጬ ፡ እመልሳለኹ ።

21 ፤ ለሰው ፡ ፊት ፡ ግን ፡ አላደላም ፤

ሰውንም ፡ አላቈላምጥም ።

22 ፤ በማቈላመጥ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ አላውቅምና ፤

ያለዚያስ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ፈጥኖ ፡ ከሕይወቴ ፡ ይለየኝ ፡ ነበር ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ።

ምዕራፍ ፡ 33 ።

1 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኢዮብ ፡ ሆይ ፥ ንግግሬን ፡ እንድትሰማ ፥

ቃሌንም ፡ ኹሉ ፡ እንድታደምጥ ፡ እለምንኻለኹ ።

2 ፤ እንሆ ፥ አፌን ፡ ከፍቻለኹ ፥

አንደበቴም ፡ በትናጋዬ ፡ ተናግሯል ።

3 ፤ ቃሌ ፡ የልቤን ፡ ቅንነት ፡ ያወጣል ፤



www.ethiopianorthodox.org

ከንፈሮቼም ፡ የሚያውቁትን ፡ በቅንነት ፡ ይናገራሉ ።

4 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ፈጠረኝ ፥

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ የአምላክ ፡ እስትንፋስ ፡ ሕይወት ፡ ሰጠኝ ።

5 ፤ ይቻልኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መልስልኝ ፤

ቃልኽንም ፡ አዘጋጅተኽ ፡ በፊቴ ፡ ቁም ።

6 ፤ እንሆ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ነኝ ፤

እኔ ፡ ደግሞ ፡ ከጭቃ ፡ የተፈጠርኹ ፡ ነኝ ።

7 ፤ እንሆ ፥ ግርማዬ ፡ አታስፈራኽም ፡

እጄም ፡ አትከብድብኽም ።

8 ፤ በዡሮዬ ፡ ተናግረኻል ፥

የቃልኽንም ፡ ድምፅ ፡ ሰምቻለኹ ፥ እንዲህም ፡ ብለኻል ።

9 ፤ እኔ ፡ ያለመተላለፍ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፤

ያለነውር ፡ ነኝ ፥ ኀጢአትም ፡ የለብኝም ፤

10 ፤ እንሆ ፥ ምክንያት ፡ አግኝቶብኛል ፥

እንደ ፡ ጠላቱም ፡ ቈጥሮኛል ፤

11 ፤ እግሬን ፡ በግንድ ፡ አጣበቀ ፥

መንገዴንም ፡ ኹሉ ፡ ተመለከተ ።

12 ፤ እንሆ ፥ አንተ ፡ በዚህ ፡ ጻድቅ ፡ አይደለኽም ፤

እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ይበልጣል ፡ ብዬ ፡ እመልስልኻለኹ ።

13 ፤ አንተ ፦ ለቃሌ ፡ ኹሉ ፡ አይመልስልኝም ፡ ብለኽ ፥

ስለ ፡ ምን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ትከራከራለኽ ፧

14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ባንድ ፡ መንገድ ፡ በሌላም ፡ ይናገራል ፤

ሰው ፡ ግን ፡ አያስተውለውም ።

15 ፤ በሕልም ፥ በሌሊት ፡ ራእይ ፥

ዐፍላ ፡ እንቅልፍ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፥

በዐልጋ ፡ ላይ ፡ ተኝተው ፡ ሳሉ ፥

16 ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሰዎችን ፡ ዡሮ ፡ ይከፍታል ፥

በተግሣጹም ፡ ያስደነግጣቸዋል ፥

17 ፤ ሰውን ፡ ከክፉ ፡ ሥራው ፡ ይመልሰው ፡ ዘንድ ፡

ከሰውም ፡ ትዕቢትን ፡ ይሰውር ፡ ዘንድ ፤

18 ፤ ነፍሱን ፡ ከጕድጓድ ፥

በሰይፍም ፡ እንዳይጠፋ ፡ ሕይወቱን ፡ ይጠብቃል ።

19 ፤ ደግሞ ፡ በዐልጋ ፡ ላይ ፡ በደዌ ፡ ይገሥጻዋል ፥



www.ethiopianorthodox.org

ዐጥንቱንም ፡ ኹሉ ፡ ያደነዝዛል ።

20 ፤ ሕይወቱም ፡ እንጀራን ፥

ነፍሱም ፡ ጣፋጭ ፡ መብልን ፡ ትጠላለች ።

21 ፤ ሥጋው ፡ እስከማይታይ ፡ ድረስ ፡ ይሰለስላል ፤

ተሸፍኖ ፡ የነበረውም ፡ ዐጥንት ፡ ይገለጣል ።

22 ፤ ነፍሱ ፡ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፥

ሕይወቱም ፡ ወደሚገድሏት ፡ ቀርባለች ።

23 ፤ የቀናውን ፡ መንገድ ፡ ለሰው ፡ ያስታውቀው ፡ ዘንድ ፥

ከሺሕ ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ የሚተረጕም ፡ መልአክ ፡ ቢገኝለት ፥

24 ፤ እየራራለት ።

ቤዛ ፡ አግኝቻለኹና ፡

ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ እንዳይወርድ ፡ አድነው ፡ ቢለው ፥

25 ፤ ሥጋው ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ሥጋ ፡ ይለመልማል ፤

ወደጕብዝናውም ፡ ዘመን ፡ ይመለሳል ።

26 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጸልያል ፥

ርሱም ፡ ሞገስን ፡ ይሰጠዋል ፡

ፊቱንም ፡ በደስታ ፡ ያሳየዋል ፤

ለሰውም ፡ ጽድቁን ፡ ይመልስለታል ።

27 ፤ ርሱም ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ እየዘመረ ፦

እኔ ፡ በድያለኹ ፥ ቅኑንም ፡ አጣምሜያለኹ ፤

የሚገባኝንም ፡ ብድራት ፡ አልተቀበልኹም ፤

28 ፤ ነፍሴ ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ እንዳትወርድ ፡ አድኗታል ፥

ሕይወቴም ፡ ብርሃንን ፡ ታያለች ፡ ይላል ።

29 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡

ኹለት ፡ ጊዜና ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ ያደርጋል ፤

30 ፤ ይህም ፡ ነፍሱን ፡ ከጕድጓድ ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፥

በሕያዋንም ፡ ብርሃን ፡ ያበራ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

31 ፤ ኢዮብ ፡ ሆይ ፥ አድምጥ ፥ እኔንም ፡ ስማ ፤

ዝም ፡ በል ፥ እኔም ፡ እናገራለኹ ።

32 ፤ ነገር ፡ ቢኖርኽ ፡ መልስልኝ ፤

ትጸድቅ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለኹና ፡ ተናገር ።

33 ፤ ያለዚያም ፡ እኔን ፡ ስማ ፤

ዝም ፡ በል ፥ እኔም ፡ ጥበብን ፡ አስተምርኻለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ።

ምዕራፍ ፡ 34 ።

1 ፤ ኤሊሁም ፡ ደግሞ ፡ መለሰ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ እናንተ ፡ ጥበበኛዎች ፥ ቃሌን ፡ ስሙ ፤

እናንተም ፡ ዐዋቂዎች ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ አድምጡ ።

3 ፤ ትናጋ ፡ መብልን ፡ እንደሚቀምስ ፥

ጆሮ ፡ ቃልን ፡ ትለያለችና ።

4 ፤ ቅን ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ እንምረጥ ፤

መልካሙንም ፡ ነገር ፡ በመካከላችን ፡ እንወቅ ።

5 ፤ ኢዮብ ፦ እኔ ፡ ጻድቅ ፡ ነኝ ፥

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ፍርዴን ፡ አስወገደ ፤

6 ፤ ምንም ፡ እውነተኛ ፡ ብኾን ፡ እንደ ፡ ውሸተኛ ፡ ተቈጠርኹ ፤

ምንም ፡ ባልበድል ፡ ቍስሌ ፡ የማይፈወስ ፡ ነው ፡ ብሏል ።

7 ፤ 8 ፤ 9 ፤ ኢዮብም ፦ በእግዚአብሔር ፡ መደሰት ፡

ለሰው ፡ ምንም ፡ አይጠቅምም ፡ ብሏልና ፥

ከበደለኛዎች ፡ ጋራ ፡ የሚተባበር ፥

ክፉ ፡ ከሚያደርጉትስ ፡ ጋራ ፡ የሚኼድ ፥

መሳለቅን ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ የሚጠጣት ፡

እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧

10 ፤ ስለዚህ ፥ እናንተ ፡ አእምሮ ፡ ያላችኹ ፡ ሰዎች ፥ ስሙኝ ፤

ክፋትን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፥

በደልንም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ይራቅ ።

11 ፤ ለሰው ፡ ሥራውን ፡ ይመልስለታል ፥

ሰውም ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ያደርጋል ።

12 ፤ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ክፉ ፡ አይሠራም ፥

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ፍርድን ፡ ጠማማ ፡ አያደርግም ።

13 ፤ ምድርን ፡ ዐደራ ፡ የሰጠው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዓለምንስ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ያኖረ ፡ ማን ፡ ነው ፧

14 ፤ ርሱ ፡ ልቡን ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ቢመልስ ፥

መንፈሱንና ፡ እስትንፋሱን ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ቢሰበስብ ፥

15 ፤ ሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ይጠፋል ፥

ሰውም ፡ ወደ ፡ ዐፈር ፡ ይመለሳል ።

16 ፤ አስተዋይ ፡ ብትኾን ፡ ይህን ፡ ስማ ፤



www.ethiopianorthodox.org

የንግግሬንም ፡ ቃል ፡ አድምጥ ።

17 ፤ በእውኑ ፡ ጽድቅን ፡ የሚጠላ ፡ ይሠለጥናልን ፧

ጻድቅና ፡ ኀያል ፡ የኾነውስ ፡ በደለኛ ፡ ታደርገዋለኽን ፧

18 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ንጉሡን ፦ በደለኛ ፡ ነኽ ፤

መኳንንቱንም ፦ ክፉዎች ፡ ናችኹ ፡ ይላልን ፧

19 ፤ እነርሱ ፡ ኹሉ ፡ የእጁ ፡ ሥራ ፡ ናቸውና ፤

በአለቃዎች ፡ ፊት ፡ አያደላም ፤

ባለጠጋውንም ፡ ሰው ፡ ከድኻው ፡ ይበልጥ ፡ አይመለከትም ።

20 ፤ እነርሱ ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ በድንገት ፡ ይሞታሉ ፤

ሕዝቡ ፡ ተንቀጥቅጦ ፡ ያልፋል ፤

ኀያላንም ፡ ያለእጅ ፡ ይነጠቃሉ ።

21 ፤ ዐይኖቹ ፡ በሰው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ናቸው ፤

ርምጃውንም ፡ ኹሉ ፡ ያያል ።

22 ፤ ኀጢአትን ፡ የሚሠሩ ፡ ይሰወሩበት ፡ ዘንድ ፡

ጨለማ ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ጥላ ፡ የለም ።

23 ፤ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመፈራረድ ፡ እንዲመጣ ፡

ጊዜ ፡ አይወሰንለትም ።

24 ፤ ታላላቆችን ፡ ያለምርመራ ፡ ይሰባብራል ፤

በእነርሱም ፡ ፋንታ ፡ ሌላዎችን ፡ ያቆማል ።

25 ፤ ሥራቸውን ፡ ያውቃል ፤

እንዲደቁም ፡ በሌሊት ፡ ይገለባብጣቸዋል ።

26 ፤ ሰዎች ፡ እያዩ ፡ እንደ ፡ ክፉዎች ፡ ይመታቸዋል ፤

27 ፤ 28 ፤ የድኻውን ፡ ልቅሶ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ያደርሱ ፡ ዘንድ ፤

ርሱም ፡ የችግረኛውን ፡ ድምፅ ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፤

ርሱን ፡ ከመከተል ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋልና ፤

ከመንገዱም ፡ ኹሉ ፡ አንዱን ፡ አልተመለከቱምና ።

29 ፤ በሕዝብ ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ቢኾን ፤

ርሱ ፡ ቢያሳርፍ ፡ የሚፈርድ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ፊቱንስ ፡ ቢሰውር ፡ የሚያየው ፡ ማን ፡ ነው ፧

30 ፤ ይህም ፡ ዝንጉ ፡ ሰው ፡ እንዳይነግሥ ፤

ሕዝቡም ፡ የሚያጠምድ ፡ እንዳይኖር ፡ ነው ።

31 ፤ እግዚአብሔርን ፦ እኔ ፡ ሳልበድል ፡ ቅጣት ፡ ተቀበልኹ ፤

32 ፤ የማላየውን ፡ ነገር ፡ አንተ ፡ አስተምረኝ ፤



www.ethiopianorthodox.org

ኀጢአትንም ፡ ሠርቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥
ደግሜ ፡ አልሠራም ፡ የሚለው ፡ ማን ፡ ነው ፨
33 ፤ በእውኑ ፡ አንተ ፡ ጥለኸዋልና ፥
ፍዳው ፡ አንተ ፡ እንደምትወደው ፡ ይኾናልን ፨
አንተ ፡ ትመርጣለኽ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ፤
ስለዚህ ፡ የምታውቀውን ፡ ተናገር ።
34 ፤ የሚሰሙኝ ፡ ጥበበኛዎች ፡ ኹሉ ፥
አስተዋዮችም ፡ እንዲህ ፡ ይሉኛል ።
35 ፤ ኢዮብ ፡ ያለዕውቀት ፡ ተናግሯል ፥
ቃሉም ፡ በአእምሮ ፡ አይደለችም ።
36 ፤ ኢዮብ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ምነው ፡ በተፈተነ ፡ ኖሮ!
ርሱ ፡ እንደ ፡ ክፉዎች ፡ መልሷልና ፤
37 ፤ በኀጢአቱም ፡ ላይ ፡ ዐመፅን ፡ ጨምሯልና ፥
በእኛም ፡ መካከል ፡ በእጁ ፡ ያጨበጭባልና ፥
ቃልንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ያበዛልና ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ።

ምዕራፍ ፡ 35 ።
1 ፤ ኤሊሁም ፡ ደግሞ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦
2 ፤ ይህ ፡ ጽድቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታስባለኽን ፨
ወይስ ፦ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እኔ ፡ ጻድቅ ፡ ነኝ ፡ ትላለኽን ፨
3 ፤ አንተ ፦ ምን ፡ ጥቅም ፡ አለኽ ፨
ኀጢአት ፡ ሠርቼ ፡ ከማገኘው ፡ ይልቅ ፡ ኀጢአት ፡ ባልሠራ ፡ ኖሮ ፡ ምን ፡ እጠቀማለኹ ፨ ብለኽ ፡ ጠይቀኻልና ።
4 ፤ እኔ ፡ ለአንተና ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ላሉ ፡ ለባልንጀራዎችኽ ፡ እመልሳለኹ ።
5 ፤ ዐይኖችኽን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አቅንተኽ ፡ እይ ፤
ከአንተም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያሉትን ፡ ደመናት ፡ ተመልከት ።
6 ፤ ኀጢአት ፡ ብትሠራ ፡ ምን ፡ ትጐዳዋለኽ ፨
መተላለፍኽስ ፡ ቢበዛ ፡ ምን ፡ ታደርገዋለኽ ፨
7 ፤ ጻድቅስ ፡ ብትኾን ፡ ምን ፡ ትሰጠዋለኽ ፨
ወይስ ፡ ከእጅኽ ፡ ምንን ፡ ይቀበላል ፨
8 ፤ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ክፋትኽ ፡ ይጐዳዋል ፤
ለሰውም ፡ ልጅ ፡ ጽድቅኽ ፡ ይጠቅመዋል ።
9 ፤ ከግፍ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሰዎች ፡ ይጮኻሉ ፤
ከኀያላንም ፡ ክንድ ፡ የተነሣ ፡ ለርዳታ ፡ ይጠራሉ ።


www.ethiopianorthodox.org

10 ፤ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ በሌሊት ፡ መዝሙርን ፡ የሚሰጥ ፥
ከምድርም ፡ እንስሳዎች ፡ ይልቅ ፡ የሚያስተምረን ፡
ከሰማይም ፡ ወፎች ፡ ይልቅ ፡ ጥበበኛዎች ፡ የሚያደርገን ፤
ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ የለም ።
12 ፤ በዚያ ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሰዎች ፡ ትዕቢት ፡ ይጮኻሉ ፥
ርሱ ፡ ግን ፡ አይመልስላቸውም ።
13 ፤ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ አይሰማም ፥
ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክም ፡ አይመለከተውም ፤
14 ፤ ይልቁንም ፦ አላየውም ፤
ነገሩ ፡ በርሱ ፡ ፊት ፡ ነው ፥ እኔም ፡ አጠብቀዋለኹ ፡ ስትል ።
15 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በቍጣው ፡ አልጐበኘምና ።
በኀጢአት ፡ እጅግ ፡ አያስብም ፡ ትላለኽ ።
16 ፤ ስለዚህ ፥ ኢዮብ ፡ አፉን ፡ በከንቱ ፡ ይከፍታል ፥
ያለዕውቀትም ፡ ቃሉን ፡ ያበዛል ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 36 ።

ምዕራፍ ፡ 36 ።

1 ፤ ኤሊሁም ፡ ደግሞ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦
2 ፤ ገና ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚነገር ፡ አለኝና ፡
ጥቂት ፡ ቈየኝ ፥ እኔም ፡ አስታውቅኻለኹ ።
3 ፤ ዕውቀቴን ፡ ከሩቅ ፡ አመጣለኹ ፥
ፈጣሪዬንም ፦ ጻድቅ ፡ ነው ፡ እላለኹ ።
4 ፤ ቃሌ ፡ በእውነት ፡ ያለሐሰት ፡ ነው ፤
በዕውቀትም ፡ ፍጹም ፡ የኾነ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አለ ።
5 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ኀያል ፡ ነው ፥ ማንንም ፡ አይንቅም ፤
ርሱም ፡ በማስተዋል ፡ ብርታት ፡ ኀያል ፡ ነው ።
6 ፤ ርሱ ፡ የበደለኛዎችን ፡ ሕይወት ፡ አያድንም ፤
ለችግረኛዎች ፡ ግን ፡ ፍርዱን ፡ ይሰጣል ።
7 ፤ ዐይኑን ፡ ከጻድቃን ፡ ላይ ፡ አያርቅም ፤
ለዘለዓለምም ፡ ከነገሥታት ፡ ጋራ ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ ያስቀምጣቸዋል ፥
እነርሱም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላሉ ።
8 ፤ በሰንሰለት ፡ቢታሰሩ ፥
ወይም ፡ በችግር ፡ ገመድ ፡ ቢጠመዱ ፥
9 ፤ ሥራቸውንና ፡ መተላለፋቸውን ፡



www.ethiopianorthodox.org

በትዕቢትም ፡ እንዳደረጉ ፡ ይናገራቸዋል ።

10 ፤ ጆሯቸውን ፡ ለተግሣጽ ፡ ይከፍተዋል ፥

ከኀጢአትም ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ያዛቸዋል ።

11 ፤ ቢሰሙ ፡ ቢያገለግሉትም ፥

ዕድሜያቸውን ፡ በልማት ፥

ዘመናቸውንም ፡ በተድላ ፡ ይፈጽማሉ ።

12 ፤ ባይሰሙ ፡ ግን ፡ በሰይፍ ፡ ይጠፋሉ ፥

ያለዕውቀትም ፡ ይሞታሉ ።

13 ፤ ዝንጉዎች ፡ ግን ፡ ቍጣን ፡ ያዘጋጃሉ ፤

ርሱም ፡ ባሰራቸው ፡ ጊዜ ፡ አይጮኹም ።

14 ፤ በሕፃንነታቸው ፡ ሳሉ ፡ ይሞታሉ ፥

ሕይወታቸውም ፡ በሰዶማውያን ፡ መካከል ፡ ይጠፋል ።

15 ፤ የተቸገረውን ፡ በችግሩ ፡ ያድነዋል ፤

በመከራም ፡ ጆሯቸውን ፡ ይገልጣል ።

16 ፤ እንዲሁም ፡ አንተን ፡ ከመከራ ፡

ችግር ፡ ወደሌለበት ፡ ወደ ፡ ሰፊ ፡ ስፍራ ፡ በወሰደኽ ፡ ነበር ፥

በማእድኽ ፡ ላይ ፡ የተዘጋጀውም ፡ ስብ ፡ በሞላበት ፡ ነበር ።

17 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ በበደለኛዎች ፡ ፍርድ ፡ የተሞላኽ ፡ ነኽ ፤

ስለዚህ ፡ ፍርድና ፡ ብይን ፡ ይይዝኻል ።

18 ፤ ቍጣ ፡ ለስድብ ፡ አያታልኽ ፤

የማማለጃም ፡ ብዛት ፡ ፈቀቅ ፡ አያድርግኽ ።

19 ፤ ባለጠግነትኽ ፡ የኀይልኽም ፡ ብርታት ፡ ኹሉ ፡

ያለችግር ፡ እንድትኾን ፡ ሊረዳኽ ፡ ይችላልን ፧

20 ፤ ወገኖች ፡ ከስፍራቸው ፡ የሚወጡበትን ፡ ሌሊት ፡ አትመኝ ።

21 ፤ ከመከራ ፡ ይልቅ ፡ ይህን ፡ መርጠኻልና ፥

ኀጢአትን ፡ እንዳትመለከት ፡ ተጠንቀቅ ።

22 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በኀይሉ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ያደርጋል ፤

እንደ ፡ ርሱስ ፡ ያለ ፡ አስተማሪ ፡ ማን ፡ ነው ፧

23 ፤ መንገዱን ፡ ማን ፡ አዘዘለት ፧

ወይስ ፦ ኀጢአትን ፡ ሠርተኻል ፡ የሚለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

24 ፤ ሰዎች ፡ የዘመሩትን ፡ ሥራውን ፡ ታከብር ፡ ዘንድ ፡ ዐስብ ።

25 ፤ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ተመልክተውታል ፤

ሰውም ፡ ከሩቅ ፡ ያየዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

26 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ነው ፥ እኛም ፡ አናውቀውም ።

የዘመኑም ፡ ቍጥር ፡ አይመረመርም ።

27 ፤ የውሃውን ፡ ነጠብጣብ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ይስባል ፥

ዝናብም ፡ ከጉም ፡ ይንጠባጠባል ፤

28 ፤ ደመናት ፡ ያዘንባሉ ፥

በሰዎችም ፡ ላይ ፡ በብዙ ፡ ያንጠባጥባሉ ።

29 ፤ የደመናውንም ፡ መዘርጋት ፥

የማደሪያውንም ፡ ነጐድጓድ ፡ የሚያስተውል ፡ ማን ፡ ነው ፧

30 ፤ እንሆ ፥ በዙሪያው ፡ ብርሃኑን ፡ ይዘረጋል ፤

የባሕሩንም ፡ ጥልቀት ፡ ይከድናል ።

31 ፤ በእነዚህ ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ይፈርዳል ፤

ብዙም ፡ ምግብ ፡ ይሰጣል ።

32 ፤ እጆቹን ፡ በብርሃን ፡ ይሰውራል ፥

በጠላቱም ፡ ላይ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ያዝዋል ፤

33 ፤ የነጐድጓድ ፡ ድምፅ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ይናገራል ፤

እንስሳዎችም ፡ ደግሞ ፡ ስለሚመጣው ፡ ውሽንፍር ፡ ይጮኻሉ ።

____________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 37 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 37 ።

1 ፤ ስለዚህም ፡ ልቤ ፡ ተንቀጠቀጠ ፥

ከስፍራውም ፡ ተንቀሳቀሰ ።

2 ፤ የድምፁን ፡ መትመም ፡ ስሙ ፥

ከአፉም ፡ የሚወጣውን ፡ ጕርምርምታ ፡ አድምጡ ።

3 ፤ ርሱን ፡ ወደ ፡ ሰማያት ፡ ዅሉ ፡ ታች ፥

ብርሃኑንም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይሰዳል ።

4 ፤ በስተኋላው ፡ ድምፅ ፡ ይጮኻል ፤

በግርማውም ፡ ድምፅ ፡ ያንጐደጕዳል ፤

ድምፁም ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡

መብረቁን ፡ አይከለክልም ።

5 ፤ እግዚአብሔር ፡ በድምፁ ፡ ድንቅኛ ፡ ያንጐደጕዳል ፤

እኛም ፡ የማናስተውለውን ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ያደርጋል ።

6 ፤ በረዶውንና ፡ ውሽንፍሩን ፡ ብርቱንም ፡ ዝናብ ፡—

በምድር ፡ ላይ ፡ ውደቁ ፡ ይላል ።

7 ፤ ሰው ፡ ዅሉ ፡ ሥራውን ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡



www.ethiopianorthodox.org

የሰውን ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ ያትማል ።

8 ፤ አውሬዎቹም ፡ ወደ ፡ ጫካው ፡ ይገባሉ ፥

በዋሻቻቸውም ፡ ይቀመጣሉ ።

9 ፤ ከተሰወረ ፡ ማደሪያውም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፥

ከሰሜንም ፡ ብርድ ፡ ይወጣል ።

10 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ እስትንፋስ ፡ ውርጭ ፡ ተሰጥቷል ፤

የውሃዎችም ፡ ስፋት ፡ ይጠባል ።

11 ፤ የውሃውንም ፡ ሙላት ፡ በደመና ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፤

የብርሃኑንም ፡ ደመና ፡ ይበታትናል ፤

12 ፤ 13 ፤ ለተግሣጽ ፡ ወይም ፡ ለምድሩ ፡ ወይም ፡ ለምሕረት ፡ ቢኾን ፥

ሰው ፡ በሚኖርበት ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡

ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡

ፈቃዱ ፡ ወደ ፡ መራቸው ፡ ይዞራል ።

14 ፤ ኢዮብ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ስማ ፤

ቁም ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ተኣምራት ፡ ዐስብ ።

15 ፤ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡ እንደሚያዛቸው ፥

የደመናውንም ፡ ብርሃን ፡ እንዴት ፡ እንደሚያበራ ፡ ዐውቀኻልን ፨

16 ፤ ወይስ ፡ የደመናውን ፡ ሚዛን ፥

ወይስ ፡ በዕውቀት ፡ ፍጹም ፡ የኾነውን ፡ ተኣምራት ፡ ዐውቀኻልን ፨

17 ፤ በደቡብ ፡ ነፋስ ፡ ምድር ፡ ጸጥ ፡ ባለች ፡ ጊዜ ፥

ልብስኽ ፡ የሞቀች ፡ አንተ ፡ ሆይ ፥

18 ፤ እንደ ፡ ቀለጠ ፡ መስተዋት ፡

ብርቱ ፡ የኾኑትን ፡ ሰማያት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ልትዘረጋ ፡ ትችላለኽን ፨

19 ፤ እኛ ፡ ከጨለማ ፡ የተነሣ ፡ በሥርዐት ፡ መናገር ፡ አንችልምና ፥

የምንለውን ፡ አስታውቀን ።

20 ፤ ማንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ቢናገር ፡ ፈጽሞ ፡ ይዋጣልና ፥

እኔ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ብወድ ፡ ሰው ፡ ይነግረዋልን ፨

21 ፤ አኹንም ፡ ነፋስ ፡ ዐልፎ ፡ ካጠራቸው ፡ በኋላ ፥

ሰው ፡ በሰማያት ፡ የሚበራውን ፡ ብርሃን ፡ ሊመለከት ፡ አይችልም ።

22 ፤ ከሰሜን ፡ ወርቅ ፡ የሚመስል ፡ ጌጠኛ ፡ ብርሃን ፡ ይወጣል ፤

በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚያስፈራ ፡ ግርማ ፡ አለ ።

23 ፤ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክን ፡ እናገኝ ፡ ዘንድ ፡ አንችልም ፤

በኀይል ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤



www.ethiopianorthodox.org

በፍርድና ፡ በጽድቅም ፡ አያስጨንቅም ።

24 ፤ ስለዚህ ፥ ሰዎች ፡ ይፈሩታል ፤

በልባቸውም ፡ ጠቢባን ፡ የኾኑትን ፡ ኹሉ ፡ አይመለከትም ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 38 ።

ምዕራፍ ፡ 38 ።

1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ለኢዮብ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

2 ፤ ያለዕውቀት ፡ በሚነገር ፡ ቃል ፡

ምክርን ፡ የሚያጨልም ፡ ይህ ፡ ማነው ፧

3 ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ወገብኽን ፡ ታጠቅ ፤

እጠይቅኻለኹ ፥ አንተም ፡ ተናገረኝ ።

4 ፤ ምድርን ፡ በመሠረትኹ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ወዴት ፡ ነበርኽ ፧

ታስተውል ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ተናገር ።

5 ፤ ብታውቅስ ፡ መሠፈሪያዋን ፡ የወሰነ ፥

በላይዋስ ፡ የመለኪያ ፡ ገመድ ፡ የዘረጋ ፡ ማን ፡ ነው ፧

6 ፤ 7 ፤ አጥቢያ ፡ ኮከቦች ፡ በአንድነት ፡ሲዘምሩ ፥

የእግዚአብሔርም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ እልል ፡ ሲሉ ፥

መሠረቶቿ ፡ በምን ፡ ላይ ፡ ተተክለው ፡ ነበር ፧

የማእዘኗንስ ፡ ድንጋይ ፡ ያቆመ ፡ ማን ፡ ነው ፧

8 ፤ ከማሕፀን ፡ እንደሚወጣ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡

ባሕርን ፡ በመዝጊያዎች ፡ የዘጋ ፡ ማን ፡ ነው ፧

9 ፤ ደመናውን ፡ ለልብሱ ፥

ጨለማንም ፡ ለመጠቅለያው ፡ አደረግኹ ፤

10 ፤ ድንበሩን ፡ በዙሪያው ፡ አድርጌ ፥

መወርወሪያዎቹንና ፡ መዝጊያዎቹን ፡ አኑሬ ።

11 ፤ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ድረሺ ፥ አትለፊ ፤

በዚህም ፡ ለትዕቢተኛው ፡ ማዕበልሽ ፡ ገደብ ፡ ይኹን ፡ አልኹ ።

12 ፤ 13 ፤ የምድርን ፡ ዳርቻ ፡ ይይዝ ፡ ዘንድ ፥

ክርሷም ፡ በደለኛዎች ፡ ይናወጡ ፡ ዘንድ ፥

በእውኑ ፡ ከተወለድኽ ፡ ዠምሮ ፡ ማለዳን ፡ አዘኻልን ፧

ለወገግታም ፡ስፍራውን ፡ አስታወቀኸዋልን ፧

14 ፤ ጭቃ ፡ ከማኅተም ፡ በታች ፡ እንደሚለወጥ ፡ እንዲሁ ፡ ርሷ ፡ ትለወጣለች ፤

ነገርም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ተቀልሟል ።

15 ፤ ከበደለኛዎች ፡ ብርሃናቸው ፡ ተከልክሏል ፥



www.ethiopianorthodox.org

ከፍ ፡ ያለውም ፡ ክንድ ፡ ተሰብሯል ።

16 ፤ ወደባሕር ፡ ምንጭስ ፡ ውስጥ ፡ ገብተኻልን ፥

በቀላዩስ ፡ መሠረት ፡ ውስጥ ፡ ተመላልሰኻልን ፥

17 ፤ የሞት ፡ በሮች ፡ ተገልጠውልኻልን ፥

የሞትንስ ፡ ጥላ ፡ ደጆች ፡ አይተኻልን ፥

18 ፤ ምድርንስ ፡ በስፋቷ ፡ አስተውለኻታልን ፥

ኹሉን ፡ ዐውቀኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተናገር ።

19 ፤ 20 ፤ ወደ ፡ ዳርቻው ፡ ትነዳው ፡ ዘንድ ፥

ወደ ፡ ቤቱም ፡ የሚያደርሰውን ፡ ጐዳና ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፥

የብርሃን ፡ መኖሪያ ፡ መንገድ ፡ የት ፡ ነው ፥

የጨለማውስ ፡ ቦታ ፡ ወዴት ፡ አለ ፥

21 ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተወልደኽ ፡ ነበርና ፥

የዕድሜኽም ፡ ቍጥር ፡ ብዙ ፡ ነውና ፤

በእውነት ፡ አንተ ፡ ሳታውቅ ፡ አትቀርም ።

22 ፤ በእውኑ ፡ ወደበረዶው ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ገብተኻልን ፥

የበረዶውንስ ፡ ቅንጣት ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ አይተኻልን ፥

23 ፤ ይኸውም ፡ ለመከራ ፡ ጊዜ ፡ ለሰልፍና ፡ ለጦርነት ፡ ቀን ፡ የጠበቅኹት ፡ ነው ።

24 ፤ ብርሃንስ ፡ በምን ፡ መንገድ ፡ ይከፈላል ፥

የምሥራቅስ ፡ ነፋስ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ይበተናል ፥

25 ፤ 26 ፤ ባድማውንና ፡ ውድማውን ፡ እንዲያጠግብ ፥

27 ፤ ሣሩንም ፡ እንዲያበቅል ፥

ማንም ፡ በሌለባት ፡ ምድር ፡ ላይ ፥

ሰውም ፡ በሌለባት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ላይ ፡ ዝናብን ፡ ያዘንብ ፡ ዘንድ ፥

ለፈሳሹ ፡ ውሃ ፡ መንዶልዶያውን ፥

ወይስ ፡ ለሚያንጐደጕድ ፡ መብረቅ ፡ መንገድን ፡ ያበጀ ፡ ማን ፡ ነው ፥

28 ፤ በእውኑ ፡ ለዝናብ ፡ አባት ፡ አለውን ፥

ወይስ ፡ የጠልን ፡ ነጠብጣብ ፡ የወለደ ፡ ማን ፡ ነው ፥

29 ፤ በረዶስ ፡ ከማን ፡ ማሕፀን ፡ ወጣ ፥

የሰማዩንስ ፡ ዐመዳይ ፡ ማን ፡ ወለደው ፥

30 ፤ ውሃዎች ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ጠነከሩ ፥

የቀላዩም ፡ ፊት ፡ ረግቷል ።

31 ፤ በእውኑ ፡ የሰባቱን ፡ ከዋክብት ፡ ዘለላ ፡ ታስር ፡ ዘንድ ፥

ወይስ ፡ ኦሪዮን ፡ የሚባለውን ፡ ኮከብ ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለኽን ፥



www.ethiopianorthodox.org

32 ፤ ወይስ ፡ ማዛሮት ፡ የሚባሉትን ፡ ከዋክብት ፡ በጊዜያቸው ፡ ታወጣ ፡ ዘንድ ፥

ወይስ ፡ ድብ ፡ የሚባለውን ፡ ኮከብ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ትመራ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለኽን ፧

33 ፤ የሰማይን ፡ ሥርዐት ፡ ታውቃለኽን ፧

በምድርስ ፡ ለይ ፡ እንዲሠለጥን ፡ ልታደርግ ፡ ትችላለኽን ፧

34 ፤ የውሃዎች ፡ ብዛት ፡ ይሸፍንኽ ፡ ዘንድ ፡

ቃልኽን ፡ ወደ ፡ ደመናት ፡ ታነሣ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለኽን ፧

35 ፤ መብረቆች ፡ ኼደው ፦ እንሆ ፥ እዚህ ፡ አለን ፡ ይሉኽ ፡ ዘንድ ፡

ልትልካቸው ፡ ትችላለኽን ፧

36 ፤ በውስጡስ ፡ ጥበብን ፡ ያኖረ ፥

ለሰውስ ፡ ልብ ፡ ማስተዋልን ፡ የሰጠ ፡ ማን ፡ ነው ፧

37 ፤ 38 ፤ የሰማይን ፡ ደመና ፡ በጥበቡ ፡ ሊቈጥር ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፧

ትቢያ ፡ በተበጠበጠ ፡ ጊዜ ፥

ኳሎቹም ፡ በተጣበቁ ፡ ጊዜ ፥

የሰማይን ፡ ረዋት ፡ ሊያዘነብል ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፧

39 ፤ 40 ፤ በዋሾቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ተጋድመው ፥

በጫካም ፡ ውስጥ ፡ አድብተው ፡ ሳሉ ፥

ለአንበሳዪቱ ፡ አደን ፡ ታድናለኽን ፧

የልጆቿንስ ፡ ነፍስ ፡ ታጠግብ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለኽን ፧

41 ፤ ልጆቹ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲጮኹ ፥

የሚበሉትም ፡ ዐጥተው ፡ ሲቅበዘበዙ ፥

ለቍራ ፡ መብልን ፡ የሚሰጠው ፡ ማን ፡ ነው ፧

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 39 ።

ምዕራፍ ፡ 39 ።

1 ፤ የበረሓ ፡ ፍየል ፡ የምትወልድበትን ፡ ጊዜ ፡ ታውቃለኽን ፧

ዋላዪቱስ ፡ የምታምጥበትን ፡ ጊዜ ፡ ትመለከታለኽን ፧

2 ፤ ርኋ ፡ የምትፈጽመውንስ ፡ ወራት ፡ ትቈጥራለኽን ፧

የምትወልድበትንስ ፡ ጊዜ ፡ ታውቃለኽን ፧

3 ፤ ይንበረከካሉ ፥ ልጆቻቸውንም ፡ ይወልዳሉ ፥

ከምጣቸውም ፡ ያርፋሉ ።

4 ፤ ልጆቻቸው ፡ ይጠነክራሉ ፥

በሜዳም ፡ ያድጋሉ ፤

ይወጣሉ ፥ ወደ ፡ እነርሱም ፡ አይመለሱም ።

5 ፤ የሜዳውስ ፡ አህያ ፡ ሐራነት ፡ ማን ፡ አወጣው ፧



www.ethiopianorthodox.org

የበረሓውንስ ፡ አህያ ፡ ከእስራቱ ፡ ማን ፡ ፈታው ፨

6 ፤ በረሓውን ፡ ለርሱ ፡ ቤት ፡ አድርጌ ፡ ሰጠኹት ፤

መኖሪያውም ፡ በጨው ፡ ምድር ፡ ነው ።

7 ፤ በከተማ ፡ ውካታ ፡ ይዘብታል ፤

የነጂውን ፡ ጩኸት ፡ አይሰማም ።

8 ፤ ተራራውን ፡ እንደ ፡ መሰምሪያው ፡ ይመለከተዋል ፥

ለምለሙንም ፡ ዅሉ ፡ ይፈልጋል ።

9 ፤ ጐሽ ፡ ያገለግልኽ ፡ ዘንድ ፡ ይታዘዛልን ፨

ወይስ ፡ በግርግምኽ ፡ አጠገብ ፡ ያድራልን ፨

10 ፤ ጐሽ ፡ ይተልምልኽ ፡ ዘንድ ፡ ትጠምደዋለኽን ፨

ወይስ ፡ ከአንተ ፡ በዃላ ፡ በዕርሻ ፡ ላይ ፡ ይጐለጕላልን ፨

11 ፤ ጕልበቱስ ፡ ብርቱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ትታመነዋለኽን ፨

ተግባርኽንስ ፡ ለርሱ ፡ ትተዋለኽን ፨

12 ፤ ዘርኽንስ ፡ ይመልስልኽ ፡ ዘንድ ፥

በዐውድማኽስ ፡ ያከማችልኽ ፡ ዘንድ ፡ ትታመነዋለኽን ፨

13 ፤ የሰጐን ፡ ክንፍ ፡ በደስታ ፡ ይንቀሳቀሳል ፤

ነገር ፡ ግን ፡ ክንፉና ፡ ላባው ፡ ጭምተኛ ፡ ነውን ፨

14 ፤ ዕንቍላሏን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ትተዋለች ፥

በዐፈርም ፡ ውስጥ ፡ ታሞቀዋለች ፤

15 ፤ እግር ፡ ይሰብረው ፡ ዘንድ ፥

የምድረ ፡ በዳም ፡ አውሬ ፡ ይረግጠው ፡ ዘንድ ፡ ትረሳለች ።

16 ፤ የርሷ ፡ እንዳልኾኑ ፡ በልጆቿ ፡ ትጨክናለች ።

በከንቱም ፡ ብትሠራ ፡ አትፈራም ፤

17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጥበብን ፡ ከርሷ ፡ ከልክሏልና ፥

ማስተዋልንም ፡ አልሰጣትምና ።

18 ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ስትል ፡

በፈረስና ፡ በፈረሰኛው ፡ ትሳለቃለች ።

19 ፤ ለፈረስ ፡ ጕልበቱን ፡ ሰጥተኸዋልን ፨

ዐንገቱንስ ፡ ጋማ ፡ አልብሰኸዋልን ፨

20 ፤ እንደ ፡ አንበጣስ ፡ አፈናጠርኸውን ፨

የማንኰራፋቱ ፡ ክብር ፡ የሚያስፈራ ፡ ነው ።

21 ፤ በኰቴው ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ይጐደፍራል ፥

በጕልበቱም ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤



www.ethiopianorthodox.org

ሰይፍም ፡ የታጠቁትን ፡ ለመገናኘት ፡ ይወጣል ።

22 ፤ በፍርሀት ፡ ላይ ፡ ይሥቃል ፥

ርሱም ፡ አይደነግጥም ፤

ከሰይፍም ፡ ፊት ፡ አይመለስም ።

23 ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ የፍላጻ ፡ ኰረጆና ፡ ብልጭልጭ ፡ የሚል ፡ ጦር ፡

ሠላጢንም ፡ ያንኳኳሉ ።

24 ፤ በጭካኔና ፡ በቍጣ ፡ መሬትን ፡ ይውጣል ፤

የመለከትም ፡ ድምፅ ፡ ቢሰማ ፡ አይቆምም ።

25 ፤ የመለከትም ፡ ድምፅ ፡ሲሰማ ፡— ዕሠይ! ይላል ፤

ከሩቅ ፡ ኾኖ ፡ ሰልፍንና ፡ የአለቃዎቹን ፡ ጩኸት ፥

የሰራዊቱንም ፡ ውካታ ፡ ያሸታል ።

26 ፤ በእውኑ ፡ ከጥበብኽ ፡ የተነሣ ፡ ጭልፊት ፡ ያንገፍብባልን ፡ ክንፎቹን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይዘረጋልን ፧

ወይስ ፡ ክንፎቹን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይዘረጋልን ፧

27 ፤ በአፍኽ ፡ ትእዛዝ ፡ ንስር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላልን ፧

ቤቱንስ ፡ በአርያም ፡ ላይ ፡ ያደርጋልን ፧

28 ፤ በገደል ፡ ላይ ፡ ይኖራል ፤

በገደሉ ፡ ገመገምና ፡ በጥጉ ፡ ያድራል ።

29 ፤ በዚያም ፡ ኾኖ ፡ የሚነጥቀውን ፡ ይጐበኛል ፤

ዐይኑም ፡ በሩቅ ፡ ትመለከታለች ።

30 ፤ ጫጩቶቹም ፡ ደም ፡ ይጠጣሉ ፤

በድን ፡ ባለባትም ፡ ስፍራ ፡ ርሱ ፡ በዚያ ፡ አለ ።

____________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 40 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 40 ።

1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መለሰ ፡ ኢዮብንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡—

2 ፤ በእውኑ ፡ የሚከራከር ፡ ሰው ፡ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ጋራ ፡ ይከራከራልን ፧

ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ የሚዋቀስ ፡ ርሱ ፡ ይመልስለት ።

3 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡—

4 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ወራዳ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፤ የምመልስልኽ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

እጄን ፡ በአፌ ፡ ላይ ፡ እጭናለኹ ።

5 ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተናገርኹ ፥ አልመልስምም ፤

ኹለተኛ ፡ ጊዜም ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አልናገርም ።

6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ለኢዮብ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡—

7 ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ ወገብኽን ፡ ታጠቅ ፤



www.ethiopianorthodox.org

እጠይቅኻለኹ ፥ አንተም ፡ ተናገረኝ ።

8 ፤ በእውኑ ፡ ፍርዴን ፡ ታፈርሳለኽን ፧

አንተስ ፡ ጻድቅ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ በእኔ ፡ ትፈርዳለኽን ፧

9 ፤ እንደእግዚአብሔር ፡ ክንድ ፡ ያለ ፡ ክንድ ፡ አለኽን ፧

ወይስ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ታንጐደጕዳለኽን ፧

10 ፤ በታላቅነትና ፡ በልዕልና ፡ ተላበስ ፤

በክብርና ፡ በግርማም ፡ ተጐናጸፍ ።

11 ፤ የቍጣኽን ፡ ፈሳሽ ፡ አፍስስ ፤

ትዕቢተኛውንም ፡ ኹሉ ፡ ተመልክተኽ ፡ አዋርደው ።

12 ፤ ትዕቢተኛውንም ፡ ኹሉ ፡ ተመልከት ፥ ዝቅ ፡ ዝቅም ፡ አድርገው ፤

በደለኛዎችንም ፡ ወዲያውኑ ፡ ርገጣቸው ።

13 ፤ በዐፈር ፡ ውስጥ ፡ በአንድነት ፡ ሰውራቸው ፤

በተሸሸገም ፡ ስፍራ ፡ ፊታቸውን ፡ ሸፍን ።

14 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ቀኝ ፡ እጅኽ ፡ ታድንኽ ፡ ዘንድ ፡ እንድትችል ፡

እኔ ፡ ደግሞ ፡ እመሰክርልኻለኹ ።

15 ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ የሠራኹትን ፡ ጕማሬ ፥ እስኪ ፥ ተመልከት ፤

እንደ ፡ በሬ ፡ ሣር ፡ ይበላል ።

16 ፤ እንሆ ፥ ብርታቱ ፡ በወገቡ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤

ኀይሉም ፡ በሆዱ ፡ ሽርማት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

17 ፤ ዥራቱን ፡ እንደ ፡ ጥድ ፡ ዛፍ ፡ ያወዛውዛል ፤

የወርቹ ፡ ሽርማት ፡ የተጐነጐነ ፡ ነው ።

18 ፤ ዐጥንቱ ፡ እንደ ፡ ናስ ፡ አገዳ ፡ ነው ፤

አካላቱ ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ዘንጎች ፡ ናቸው ።

19 ፤ ርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍጥረት ፡ አውራ ፡ ነው ፤

ሠሪውም ፡ ሰይፉን ፡ ሰጠው ።

20 ፤ የሜዳ ፡ እንስሳዎች ፡ ኹሉ ፡ የሚጫወቱበት ፡ ተራራ ፡

ምግብን ፡ ያበቅልለታል ።

21 ፤ ጥላ ፡ ካለው ፡ ዛፍ ፡ በታች ፥

በደንገልና ፡ በረግረግ ፡ ውስጥ ፡ ይተኛል ።

22 ፤ ጥላ ፡ ያለው ፡ ዛፍ ፡ በጥላው ፡ ይሰውረዋል ፤

የወንዝ ፡ አሓያ ፡ ዛፎች ፡ ይከቡታል ።

23 ፤ እንሆ ፥ ወንዙ ፡ ቢጐርፍ ፡ አይደነግጥም ፤

ዮርዳኖስም ፡ እስከ ፡ አፉ ፡ ድረስ ፡ ቢፈስ ፡ ርሱ ፡ ይተማመናል ።



www.ethiopianorthodox.org

24 ፤ ዐይኖቹ ፡ እያዩ ፡ ይያዛልን ፧

አፍንጫውስ ፡ በወጥመድ ፡ ይበሳልን ፧

25 ፤ በእውኑ ፡ አዞውን ፡ በመቃጥን ፡ ታወጣለኸን ፧

ምላሱንስ ፡ በገመድ ፡ ታስረዋለኸን ፧

26 ፤ ወይስ ፡ ስናጋ ፡ በአፍንጫው ፡ ታደርጋለኸን ፧

ወይስ ፡ በችንካር ፡ ጕንጩን ፡ ትበሳለኸን ፧

27 ፤ በእውኑ ፡ ወዳንተ ፡ እጅግ ፡ ይለምናልን ፧

በጣፈጠስ ፡ ቃል ፡ ይናገርኻልን ፧

28 ፤ በእውኑ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይገባልን ፧

ወይስ ፡ ለዘለዓለም ፡ ባሪያ ፡ ታደርገዋለኸን ፧

29 ፤ ከወፍ ፡ ጋራ ፡ እንደምትጫወት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ትጫወታለኸን ፧

ወይስ ፡ ለሴት ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ታስረዋለኸን ፧

30 ፤ አጥማጆች ፡ በርሱ ፡ ይከራከራሉን ፧

ወይስ ፡ ነጋዴዎች ፡ ያካፍሉታልን ፧

31 ፤ በእውኑ ፡ ቍርበቱን ፡ በጭሬ ፥

ራሱንስ ፡ በዓሣ ፡ ጦር ፡ ትሞላዋለኸን ፧

32 ፤ እጅኽን ፡ በላዩ ፡ ጫን ፤

ሰልፉን ፡ ዐስብ ፥ እንግዲህም ፡ አትድገም ።

______________________መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 41 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 41 ።

1 ፤ እንሆ ፥ ተስፋው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤

ያየው ፡ ኹሉ ፡ ስንኳ ፡ በፊቱ ፡ ይዋረዳል ።

2 ፤ ያንቀሳቅሰውም ፡ ዘንድ ፡ የሚደፍር ፡ የለም ፤

እንግዲህ ፡ በፊቴ ፡ መቆም ፡ የሚችል ፡ማን ፡ ነው ፧

3 ፤ እመልስለትስ ፡ ዘንድ ፡ መዠመሪያ ፡ የሰጠኝ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ከሰማይ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ገንዘቤ ፡ ነው ።

4 ፤ ስለ ፡ አካላቱና ፡ ስለ ፡ ብርቱ ፡ ኀይሉ ፥

ስለ ፡ መልካም ፡ ሰውነቱ ፡ ዝም ፡ አልልም ።

5 ፤ የውጪ ፡ ልብሱን ፡ ማን ፡ ይገፋል ፧

በጥንድ ፡ መንጋጋውስ ፡ ውስጥ ፡ ማን ፡ ይገባል ፧

6 ፤ የፊቱንስ ፡ ደጆች ፡ የሚከፍት ፡ ማን ፡ ነው ፧

በጥርሶቹ ፡ ዙሪያ ፡ ግርማ ፡ አለ ።

7 ፤ ቅርፊቶቹ ፡ ጠንካራ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ርሱ ፡ ትዕቢተኛ ፡ ነው ፤



www.ethiopianorthodox.org

በጠባብ ፡ ማተሚያ ፡ እንደ ፡ ታተሙ ፡ ናቸው ።

8 ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተቀራረቡ ፡ ናቸውና ፥

ነፋስ ፡ በመካከላቸው ፡ መግባት ፡ አይችልም ።

9 ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተገጣጠሙ ፡ ናቸው ፤

እስከማይለያዩም ፡ ድረስ ፡ ተያይዘዋል ።

10 ፤ እንጥሽታው ፡ ብልጭታ ፡ ያወጣል ፥

ዐይኖቹም ፡ እንደ ፡ ወገግታ ፡ ናቸው ።

11 ፤ ከአፉ ፡ ፋናዎች ፡ ይወጣሉ ፥

የእሳትም ፡ ፍንጣሪ ፡ ይረጫል ።

12 ፤ እንደ ፡ ፈላ ፡ ድስትና ፡ እንደሚቃጠል ፡ ሸምበቆ ፡

ከአንፍንጫው ፡ ጢስ ፡ ይወጣል ።

13 ፤ እስትንፋሱ ፡ ከሰልን ፡ ታቃጥላለች ፥

ነበልባልም ፡ ከአፉ ፡ ይወጣል ።

14 ፤ በዐንገቱ ፡ ኀይል ፡ ታድራለች ፤

ግርማ ፡ በፊቱ ፡ ይዘፍናል ።

15 ፤ የሥጋውም ፡ ቅርፊት ፡ የተጣበቀ ፡ ነው ፤

እስከማይንቀሳቀሱም ፡ ድረስ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ጸንተዋል ።

16 ፤ ልቡ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ የደነደነ ፡ ነው ፤

እንደ ፡ ወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ የጸና ፡ ነው ።

17 ፤ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ኀያላን ፡ ይፈራሉ ፤

ከድንጋጤም ፡ የተነሣ ፡ ያብዳሉ ።

18 ፤ ሰይፍና ፡ ጦር ፥ ፍላጻና ፡ መውጊያም ፡ ቢያገኙት ፡ አያሸንፉትም ።

19 ፤ ብረትን ፡ እንደ ፡ ገለባ ፥

ናስንም ፡ እንደ ፡ ነቀዘ ፡ ዕንጨት ፡ ይቈጥራቸዋል ።

20 ፤ ፍላጻ ፡ ሊያባርረው ፡ አይችልም ፤

የወንጭፍም ፡ ድንጋዮች ፡ እንደ ፡ ገለባ ፡ ይኾኑለታል ።

21 ፤ በሎታውን ፡ እንደ ፡ ገለባ ፡ ይቈጥረዋል ፤

ሦላጢኑም ፡ ሲሰበቅ ፡ ይሥቃል ።

22 ፤ ታቹ ፡ እንደ ፡ ስለታም ፡ ገል ፡ ነው ፤

እንደ ፡ መዳመጫም ፡ በጭቃ ፡ ላይ ፡ ያልፋል ።

23 ፤ ቀላዩን ፡ እንደ ፡ ድስት ፡ ያፈላዋል ፤

ባሕሩንም ፡ እንደ ፡ ሽቱ ፡ ምንቸት ፡ ያደርገዋል ።

24 ፤ በስተኋላው ፡ ብሩህ ፡ መንገድን ፡ ያበራል ፤



www.ethiopianorthodox.org

ቀላዩም ፡ ሽበት ፡ ይመስላል ።

25 ፤ ያለፍርሀት ፡ የተፈጠረ ፥

እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የለም ።

26 ፤ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ይመለከታል ፤

በትዕቢተኞዎችም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ።

## መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 42 ።

ምዕራፍ ፡ 42 ።

1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦

2 ፤ ኹሉን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ቻይ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፥

ዐሳብኽም ፡ ይከለከል ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ እንደማይቻል ፡ ዐወቅኹ ።

3 ፤ ያለዕውቀት ፡ ምክርን ፡ የሚሰውር ፡ ማን ፡ ነው ፨

ስለዚህ ፡ እኔ ፡ የማላስተውለውን ፥

የማላውቀውንም ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ተናግሬያለኹ ።

4 ፤ እባክኽ ፥ ስማኝ ፡ እኔም ፡ ልናገር ፤

እጠይቅኽማለኹ ፥ አንተም ፡ ተናገረኝ ።

5 ፤ መስማትንስ ፡ በጆሮ ፡ በመስማት ፡ ሰምቼ ፡ ነበር ፤

አኹን ፡ ግን ፡ ዐይኔ ፡ አየችኽ ፤

6 ፤ ስለዚህ ፥ ራሴን ፡ እንቃለኹ ፤

በዐፈርና ፡ በዐመድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጬ ፡ እጸጸታለኹ ።

7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለኢዮብ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቴማናዊውን ፡ ኤልፋዝን ፦ እንደ ፡
ባሪያዬ ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ቅንን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ አልተናገራችኹምና ፡ ቍጣዬ ፡ በአንተና ፡ በኹለቱ ፡ ባልንጀራዎችኽ ፡
ላይ ፡ ነዷል ።

8 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ሰባት ፡ ወይፈኖችና ፡ ሰባት ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ይዛችኹ ፡ ወደ ፡ ባሪያዬ ፡ ወደ ፡ ኢዮብ ፡ ዘንድ ፡
ኺዱ ፥ የሚቃጠልንም ፡ መሥዋዕት ፡ ስለ ፡ ራሳችኹ ፡ አሳርጉ ፤ ባሪያዬም ፡ ኢዮብ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ይጸልያል ፥ እኔም ፡
እንደ ፡ ስንፍናችኹ ፡ እንዳላደርግባችኹ ፡ ፊቱን ፡ እቀበላለኹ ፤ እንደ ፡ ባሪያዬ ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ እኔ ፡
አልተናገራችኹምና ።

9 ፤ ቴማናዊውም ፡ ኤልፋዝ ፡ ሹሐዊውም ፡ በልዳዶስ ፡ ናዕማታዊውም ፡ ሶፋር ፡ ኼደው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዛቸው ፡
አደረጉ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የኢዮብን ፡ ፊት ፡ ተቀበለ ።

10 ፤ ኢዮብም ፡ ስለ ፡ ወዳጆቹ ፡ በጸለየ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ምርኮውን ፡ መለሰለት ፤ እግዚአብሔርም ፡ ቀድሞ ፡
በነበረው ፡ ፋንታ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጎ ፡ ለኢዮብ ፡ ሰጠው ።

11 ፤ ወንድሞቹና ፡ እኅቶቹ ፡ ቀድሞም ፡ ያውቁት ፡ የነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጡ ፥ በቤቱም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡
እንጀራ ፡ በሉ ፤ ስለ ፡ ርሱም ፡ ዐዘኑለት ፥ እግዚአብሔርም ፡ ካመጣበት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡
አጽናኑት ፤ እያንዳንዳቸውም ፡ ብርና ፡ የወርቅ ፡ ቀለበት ፡ ሰጡት ።

12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ የኋለኛውን ፡ ለኢዮብ ፡ ባረከ ፤ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ሺሕም ፡ በጎች ፥ ስድስት ፡
ሺሕም ፡ ግመሎች ፥ አንድ ፡ ሺሕም ፡ ጥማድ ፡ በሬዎች ፥ አንድ ፡ ሺሕም ፡ እንስት ፡ አህያዎች ፡ ነበሩት ።

13 ፤ ደግሞም ፡ ሰባት ፡ ወንዶችና ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ኾኑለት ።



www.ethiopianorthodox.org

14 ፤ የመዠመሪያዪቱንም ፡ ስም ፡ ይሚማ ፥ የኹለተኛዪቱንም ፡ ስም ፡ ቃስያ ፥ የሦስተኛዪቱንም ፡ ስም ፡ አማልቶያስ ፡
ቂራስ ፡ ብሎ ፡ ሰየማቸው ።

15 ፤ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ ያሉ ፡ የተዋቡ ፡ ሴቶች ፡ በአገሩ ፡ ዅሉ ፡ አልተገኙም ፤ አባታቸውም ፡
ከወንድሞቻቸው ፡ ጋራ ፡ ርስት ፡ ሰጣቸው ።

16 ፤ ከዚህም ፡ በዃላ ፡ ኢዮብ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ልጆቹንና ፡ የልጅ ፡ ልጆቹንም ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡
ድረስ ፡ አየ ።

17 ፤ ኢዮብም ፡ ሸምግሎ ፥ ዕድሜም ፡ ጠግቦ ፡ ሞተ ፨



www.ethiopianorthodox.org